አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ክዋኔ በሀድያ ብሔር

በ

ካሳሁን አባይነህ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓተ ክዋኔ በሀድያ ብሔር

በ

ካሳሁን አባይነህ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ፡- ዘሪሁን አስፋው

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ክዋኔ በሀድያ ብሔር

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዘሪሁን አስፋው ____________ ____________

አማካሪ ፊርማ

ሰለሞን ሰቦ ____________ ____________

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

ሀብታሙ ወንድሙ ____________ ____________

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

# ምስጋና

ይህ ጥናት አሁን ያለውን ቅርፅ ይዞ እንዲገኝ አቅጣጫ በማሳየት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረም፣ የፊደል ግድፈቶችን ሳይቀር በማስተካከል ትልቅ ድጋፍ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚሆኑ በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ለተባበራችሁኝ መረጃ ሰጪዎቼ እክሌ እክሌ ብዬ ሳልጠቅስ በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መጀመሪያ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

የሀድያን ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ ባለሞያዎች ምስጋና ይገባችሁዋል፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ከሄድኩበት ጊዜ አንስቶ ከጎኔ ሳትለዩ ጥናቱ የሚደረግበት ስርዓት የሚፈፀምበት አካባቢን በማፈላለግ፣ በቦታው ተገኝቼ መረጃ እንድሰበስብ፣ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ትልቅ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ለአቶ አበበ ጊቻሞ፣ ለአቶ አበበ አቡኔ እንዲሁም ለጓደኛዬ ተስፋዬ እንድሪያስና ማሚ ደጄኔ ብድሩ ይድረሳችሁ፣ ፀጋ ይብዛላችሁ እላለሁ፡፡

ፎቶ ካሜራሽን ላዋሽኝ ለወ/ሮ መዘነች ታከለ፣ ቪዲዮ ካሜራሽን ይዠው ላልሽኝ ወ/ት ፋሲካ አለሙ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በመተርጎም ለተባበራችሁኝ አቶ ተስፋዬ ወ/መስቀል፣ አቶ ታምራት ቂንጣሞ፣ አቶ አበበ ሞሻጎ እና አቶ ታደሰ ሀምባሞ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ጥናትህ ምን ላይ ደረሰ በማለት ላበረታታችሁኝ ወዳጆቼ እንዲሁም ለጥናቱ መሳካት፣ የተለያዩ ሃሳቦችን በመሰንዘርና በመመልከት ሀሳባችሁን ላልነፈጋችሁኝ የክፍል ጓደኞቼ ውቤ ታደገ እና ዳዊት ብርሃኑ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ................................................................................................ i

ማውጫ ................................................................................................ ii

አጠቃሎ ................................................................................................ iv

1.መግቢያ ................................................................................................ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ................................................................................................ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................................................ 2

1.3 የጥናቱ አላማዎች ................................................................................................ 3

1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ ................................................................................................ 3

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ................................................................................................ 3

1.4.የምርምር ጥያቄዎች ................................................................................................ 3

1.5.የጥናቱ ወሰን ................................................................................................ 4

1.6.የጥናቱ አስፈላጊነት ................................................................................................ 4

1.7. የጥናቱ ዘዴ እና የመረጃ መሰብሰቢያ ................................................................................................ 4

1.7.1 የጥናቱ ዘዴ ................................................................................................ 4

1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ................................................................................................ 5

1.8 የመስክ ተሞክሮ ................................................................................................ 7

1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ................................................................................................ 10

2. ክለሳ ድርሳን ................................................................................................ 11

2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ................................................................................................ 11

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ................................................................................................ 17

2.2.1 ባህላዊ ስርዓቶች ........ 17

2.2.2 ክዋኔ ........ 20

3. የጥናቱ አካባቢ ........ 23

3.1 መልክአምድራዊ አቀማመጥ ........ 23

3.2 የሀድያ ብሔር መተዳደሪያ ........ 23

3.2.1 እርሻ ........ 23

3.2.2 ከብት ማርባት ........ 24

3.3 መሰረተ ልማት ........ 24

3.4 ባህላዊ አስተዳደር ........ 25

4. የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ........ 27

4.1 ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት አጀማመር ........ 27

4.2 የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ........ 29

4.3 የቆጠራው ስርዓት ክዋኔ ........ 35

4.3.1 የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ........ 35

4.3.2 በዋዜማው የሚደረጉ ክዋኔዎች ........ 40

4.3.3 ወደ ወንዝ የመሄድ ስርዓት ክዋኔ ........ 46

4.3.4 ከወንዝ መልስ የሚደረጉ ስርዓተ ክዋኔዎች ........ 55

4.3.5 ወበጣ (Wobaxa) ወይም የገላ ማጠብ ስርዓት ክዋኔ ........ 66

5. ማጠቃለያ ........ 70

ዋቢ ጽሑፎች ........ 73

አባሪዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ውስጥ በሚገኘው የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ክዋኔ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓቱ አልተጠናም፤ ይህም የጥናቱ አነሳሽ አንዱ ምክንያት ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ ክዋኔውን ማሳየትና መግለጽ ነው፡፡

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለ መጠየቅ፣ በምልከታ እና በቡድን ውይይት ነው፡፡ በተገለፁት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎች ከተዳሰሱት ንድፈ ሃሳቦች አንጻር የክዋኔ ንድፈ ሃሳብን ማዕከል በማድረግ የተተነተኑ ሲሆን፤ ገላጭ (Descriptive) የትንተና ስልትም እጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በትንተና እንደታየውም ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት የሚካሄደው በባህሉ መሰረት መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች መሟላታቸው ሲረጋገጥና ፈቃድ ሲሰጥ ነው፡፡ የወገና ስርዓት የተካሄደለት አንድ ከብት አርቢ በኢኮኖሚው የተሻለ ከመሆኑም በላይ በባህሉ ደንብ መሰረት ለተግባሩ የተለየ ባህላዊ የማዕረግ ስያሜ ሹመት ይሰጠዋል፡፡ ሚስቱም የተለየ ስያሜና ክብር ይሰጣታል፡፡ ይህ ማዕረግ የተሰጠው ከብት አርቢ ማህበራዊ ደረጃው ከፍ እንደሚልና፤ በማህበረሰቡ ዘንድ ክብርና ዝና እንደሚሰጠው፣ የተለያዩ ማህበራዊ ሚናዎችም እንደሚኖሩት በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የጥናት ግኝቶች መነሻ በማድረግ በጥናቱ መጨረሻ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ይህን ባህላዊ ስርዓት ክዋኔ ሂደት በመቅረፅ ዶክመንተሪ ፊልም ቢያዘጋጅና ቢያስተዋውቅ፤ እንዲሁም ስርዓቱ በሚከወንበት አጋጣሚ ጎብኚዎች ተገኝተው እንዲመለከቱት ቢደረግ የሚሉ የይሁንታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

# 1.መግቢያ

ፎክሎር ዘውጎች አንዱ ሀገረሰባዊ ልማድ ነው፡፡ ሰዎች እንደባህላቸው የራሳቸው የሆኑ ሀገረሰባዊ ልማዶች አሏቸው፡፡ የሀድያ ብሔር ከሚፈጽሟቸው ሀገረሰባዊ ልማዶች ውስጥ ስርዓተ ከበራ ይጠቀሳል፡፡ አንድ ስርዓተ ከበራ ሲፈጸም እንደየባህሉ የራሱ የሆነ ዝግጅት፣ ሀገ ደንብ፣ የአከዋወን ቅደም ተከተል እንዲሁም የባህሉ መገለጫ የሆኑ ባህሪያት አሉት፡፡ ባህላዊ ስርዓት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መከወኑ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ይህም የማህበረሰቡን ባህል፣ ታሪክ፣ ልማድና ደንብ ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፋል፤ ስርዓቱም ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔን መቃኘትና መግለጽ ነው፡፡

የጥናቱ አደረጃጀትም፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዋና እና ዝርዝር አላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ ወሰን፣ አስፈላጊነት እና የጥናቱ ዘዴና የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እንዲሁም የመስክ ተሞክሮን ያካተተ ነው፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳን፣ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተዛማጅ ጽሑፎችና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ተካተዋል፡፡ ሶስተኛው ምዕራፍ ጥናቱ የሚካሄድበት ብሔር ባህላዊ እና ማህበራዊ ዳራን ይዟል፡፡ አራተኛው ምዕራፍ በመስክ ቆይታ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተደራጅተው የተገለፁበትና የተተነተኑበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የሀድያ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከሚገኙ ብሔረሰቦች ውስጥ አንዱ ነው። የሀድያ ብሔር ቋንቋ ሀድይኛ (ሀዲይሳ) የሚባል ሲሆን፤ ቋንቋው የሚመደበው ከኩሻዊ የቋንቋዎች ቤተሰብ ነው። ሀድያ የሚለው የብሔሩ መጠሪያ ስያሜ ትርጉምን አቶ አበበ ጊቻሞ ሲያብራሩ "ሀድያ የሚለው ቃል ከሁለት የተለያዩ ቃላት የተገኘ ሲሆን፤ እነሱም 'ሀድ' እና 'እያ' ናቸው፡፡ 'ሀድ' ማለት ብዙ፣ ሁሉ ሲሆን፤ 'እያ' የሚለው ደግሞ መሸከም፣ መቻልና መታገስ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሀድያ የሚለው የብሔሩ መጠሪያ ትርጉም ሁሉን ቻይ፤" እንደሚባል ገልፀዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 25/2005) ፡፡

ማንኛውም ማህበረሰብ ባህሉን፣ ታሪኩን፣ እምነቱንና ወግ ልማዱን እንዲሁም አመለካከቱን የሚገልጽባቸው ባህላዊ ስርዓቶች እንደሚኖሩት ሁሉ የሀድያ ብሔርም ባህሉን፣ ታሪኩን፣ እምነቱን፣ ወግና ልማዱን የሚገልጽባቸው ባህላዊ ስርዓቶች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል የሰርግ፣ የልደትና የለቅሶ ስርዓት፣ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ላይ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሱኝ ሁለት ምክንያቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ጥናቱ በሚጠናበት በሀድያ ዞን ሶሮ ወረዳ ለተወሰኑ ዓመታት ኖሬያለሁ፡፡ በቆየሁባቸው አመታት ውስጥ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ወይም ምርቃት እየተባለ ሰዎች ጥሪ እየተደረገላቸው ስርዓቱ የሚፈፀምበት ቦታ ደርሰው እንደመጡ ይነገሩኝ ነበር፡፡ ሄደው የመጡት ሰዎች ስርዓቱ ባህላዊ እንደሆነና በሚፈጸምበት ጊዜ ብዙ ትዕይንቶችን የያዘ እንደሆነ ይነግሩኝ ነበር፡፡

በመሆኑም አንድ ወቅት እኔም በባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ላይ እንድገኝ ጥሪ ተደረገልኝና ስርዓቱ የሚካሄድበት ቦታ ሄጄ ለማየት ቻልኩ፡፡ ከእኔ ቀደም ብለው በስርዓቱ ታድመው የነገሩኝና በኋላም ራሴ ሄጄ ስመለከት ዝግጅቱ፣ በቦታው የታደሙት ሰዎች ብዛት፣ የስርዓቱ አተገባበር በውስጤ ነበር፡፡ በመሆኑም ጥናት የማደርግበትን ጉዳይ ሳስብ ወዲያው የመጣልኝ ጉዳይ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ርዕሰ ጉዳዩ በክፍለ ትምህርቱ አለመጠናቱ ሌላው እንዳጠና አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማዎች

ይህ ጥናት አንድ ዋና አላማና አራት ዝርዝር አላማዎችን ይዟል፡፡

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ክዋኔን እና ማህበራዊ ፋይዳውን መግለጽ ነው፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

- በሀድያ ብሔር ባህል የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች መመርመር፡፡
- ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው የሚከወኑ ክዋኔዎችን መግለጽ፡፡
- ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ክዋኔ ላይ የሚቀርቡ ትዕምርቶችን በመለየት ከባህሉ አንጻር ያላቸውን ፋይዳ መተርጎም፡፡
- ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ያካሄዱ ሰዎች በአከባቢው ማህበረሰብ የሚሰጣቸው ማህበራዊ ደረጃ እና ተግባራቸውን መፈተሽ ፡፡

## 1.4.የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የመለሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች፡-

- ❖ በሀድያ ብሔር የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ያላባቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
- ❖ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ክዋኔው ምን ይመስላል?
- ❖ በሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ክዋኔ ላይ የሚታዩ ትዕምርቶች ትርጉማቸውና ፋይዳቸው ተለይተው ይታወቃሉን?

❖ በሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት በማካሄዳቸው በቤተሰባቸው፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ምን አይነት ሁኔታዎች ይፈጥራሉ?

❖ በሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ያካሄዱ ሰዎች የሚሰጧቸው ማህበራዊ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በሀድያ ዞን ሲሆን፣ ጥናቱ በዞኑ ካሉ አስር ወረዳዎች ውስጥ በሶሮ እና ጎንቦራ ወረዳዎች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በዞኑ ካሉ ወረዳዎች ውስጥ በብዛት የከብቶች ቆጠራ ስርዓት የሚካሄደው በሁለቱ ወረዳዎች በመሆኑ ነው፡፡ ከተጠቀሱት ወረዳዎች ውጭ ያሉትን ወረዳዎች ጥናቱ አይመለከትም፡፡ ጥናቱ በተለይ ትኩረት የሚያደርገው መቶ (ጥቤ) የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓተ ክዋኔ ላይ ብቻ ነው፡፡

## 1.6.የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት አስፈላጊነት የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔን ከመግለጽ በተጨማሪ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የአካባቢው ማህበረሰብ ስለባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔ የሚሰጠውን ትርጉም ምንነት ያስተዋውቃል፡፡
- ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔ ምንነት ለማያውቁ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡
- በባህላዊ ስርዓቱ ላይ ተጨማሪ ወይም አዲስ ጥናት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ እና የመረጃ መሰብሰቢያ

### 1.7.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ባህላዊ የቆጠራ ስርዓቱ ሲከወን የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመግለጽ፣ ለመተንተን ገላጭ (*descriptive*) የትንተና ስልትን ተጠቅሟል፡፡ በዚህም መሰረት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን

(*performance theory*) መስረት በማድረግ የሚያተኩረው በክዋኔ ተኮር (*performance centered approach*) የአጠናን ዘዴ ነው።

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የከዋኖቹን፣ የተሳታፊዎቹን ሚና፣ መቼት፣ በክዋኔው የሚጠቀሙባቸውን ኮዶች፣ ትዕምርቶች ትርጉምና ፋይዳቸውን፣ የክዋኔውን ቅደም ተከተል አጥኚው በአውዱ በመገኘት መረዳት መገንዘብ እንዳለበት Sims and Stephens (2002፡ 127-129) እና R.Hill (2007፡100-105) ይገልፃሉ። እንዲሁም Bauman (1983፡ 362-367) እንደሚገልጹት አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይን ለመተንተን አጥኚው በዚያው በክዋኔው አጋጣሚ በመገኘት ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች መረዳት እንዳለበት ይገልጻሉ።

ስለዚህም በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በክዋኔ ተኮር የአጠናን ዘዴ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

### 1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች እጥቅም ላይ ውለዋል። ከካልዓይ መረጃ ምንጮች አንዱ በሀድያ ብሔር ላይ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችና የምርምር ስራ ውጤቶች ናቸው። ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን የያዙ ጽሁፎች ሲሆኑ፣ በተጨማሪ ጥናቱን ለማካሄድ የሚያግዙ ንድፈ ሀሳቦችን የያዙ መጽሐፎች የተገኙ ሀሳቦች ተጠቅሜያለሁ።

ከቀዳማይ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ መስክ በመሄድ በክዋኔው አውድ በመገኘት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቆችና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ ናቸው። ከዚህ ቀጥዬ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በአጭር በአጭሩ አቀርባለሁ።

መረጃ ለመሰብሰብ ከተጠቀምኩባቸው ውስጥ አንዱ የምልከታ ዘዴ ነው። ምልከታ በመስክ በክዋኔው አጋጣሚ ተገኝቶ መመልከትን ይጠይቃል። Goldstein (1964፡ 80- 82) እና ፈቃደ (1991፡ 90- 96) እንደሚገልጹት ጥናት የሚደረግበት ጉዳይ ሲከወን በአውዱ አጥኚው ተገኝቶ በማስተዋል በመመልከት መረጃ መሠብሠብ ተገቢ ነው።

ምልከታን በመጠቀም ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ሲከወን በተፈጥሯዊ መቼት አውድ በመገኘት በስርዓቱ ላይ የከዋኞቹን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ በስርዓቱ ያሉ ትዕምርቶች፣ በስርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን በማስተዋል መረጃ ተሰብሧል፡፡

የተደረገው የምልከታ አይነት ያለተሳትፎ ምልከታ ሲሆን፤ ከምልከታ ቴክኒኮች ውስጥም ያልተገደበ ወይም ገደብ የሌለው ምልከታ ስርዓቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅ በአውዱ ተገኝቶ በመመልከት ነው፡፡ በአጠቃላይ አምስት የተለያዩ ቦታዎች ምልከታ ያደረኩ ሲሆን፤ እነሱም በሶሮ ወረዳ ሶስት ቦታ እንዲሁም በጎምቦራ ወረዳ ደግሞ ሁለት ናቸው፡፡

ሌላ መረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀምኩት የቃለ መጠይቅ ዘዴን ነው፡፡ Goldstein (1964፡104-105) እና ፈቃደ (1991፡96-104) እንደሚገልጹት በአንድ የመስክ ስራ ቃለ መጠይቅን መጠቀም በምልከታ ወቅት የነበረውን ክፍተት ለመሙላት እና የተለያዩ አመለካከቶችን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ስለዚህም በምልከታ ወቅት ያየኋቸው ነገሮች በማህበረሰቡ እንዲብራሩልኝ ወይም እንዲመልሱልኝ የምፈልጋቸውን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ስለሚያግዘኝ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ከቃለ መጠይቅ አይነቶች ጥልቅ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሜያለሁ፡፡

በዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔ ሲካሄድ አጠቃላይ የስርዓቱ ሂደት ላይ ከዋኞቹና ተሳታፊዎች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ መግባባት፣ የሚጠቀሟቸው ትዕምርቶችና የሚሰጣቸው ትርጓሜ፣ ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ፣ የተመልካቹ ሁኔታና አመለካከት የቃለ መጠይቅ ዘዴን በመጠቀም ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሁለት የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ የመጀመሪያው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ሲሆኑ በምልከታ ወቅት በጥያቄነት የተያዙና የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በድንገት ሚፈጠሩ ቃለ መጠይቆች ናቸው፡፡ ለመረጃ አቀባዮች የተዘጋጁ ጥያቄዎችን አቅርቤ እየመለሱ እያለ በድንገት ከሚናገሩት በመነሳት እዚያው የተፈጠሩ ናቸው፡፡

የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ በተመለከተ የኢላማ ናሙና ስልትን በመጠቀም ነው፡፡ ስለዚህም በቃለ መጠይቁ መረጃ በማቀበል የተሳተፉት ሰዎች ጥናቱ በሚሰራበት ርዕሰ

ጉዳይ ላይ የተሻለ ግንዛቤ አላቸው የሚባሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች የብሔሩን ባህል ታሪክ ወግ በተሻለ ያውቃሉና መረጃ ይሰጣሉ ከሚባሉት እንዲሁም ከዚህ በፊት የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ካካሄዱ ሰዎች ውስጥ በመምረጥ ነው፡፡ በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ጠቅላላ ሰዎች ሰላሳ አራት ሲሆኑ፤ ከእነዚህም ውስጥ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች አስራት አራት ሲሆኑ፤ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ደግሞ ሃያ ናቸው፡፡

በመጨረሻ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀምኩት ዘዴ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን የተጠቀምኩት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴ ያልተመለሱ ጥያቄዎች፣ ትርጓሜ የሚሹ ጉዳዮች ላይ በባህሉ መሰረት ትርጓሜ ለማግኘትና ለመመለስ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ጥያቄዎች ቀድመው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ሁለት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ያደረኩ ሲሆን፤ አንዱ በሶሮ ወረዳ አስር ሰዎችን ያሳተፈ ሲሆን ሌላው ደግሞ በጎንቦራ ወረዳ ስምንት ሰዎች የተሳተፉበት ነው፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ሰዎች የተመረጡት በኢላማ ናሙና ሲሆን፤ ጥናት በሚደረግበት ጉዳይ ላይ ጥሩ እውቀት ያላቸው፣ የዕድሜ ባለፀጎች፣ ባህሉን፣ ታሪኩን ያውቃሉ የሚባሉና በማህበረሰቡ የሚከበሩ ናቸው፡፡ እንዲሁም በጥያቄዎቹ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው እና መረጃ ይሰጣሉ የተባሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መረጃ ለመሰብሰብ የመረጃ አቀባዮችን ፈቃደኝነት በማረጋገጥ በአጋዥነት ቪዲዩ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራን እንዲሁም የጽሑፍ ማስታወሻ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 1.8 የመስክ ተሞክሮ

ለጥናት የመረጥኩትን አካባቢ ቀድም ብዬ የማውቀው ቢሆንም በጥናት መልክ ግን ትኩረት ሰጥቼ አላየሁትም ነበር፡፡ በመሆኑም ለጥናት ወደ መስክ ከመሰማራቴ በፊት ጥናት ስለማደርግበት ጉዳይ የተሰሩ ስራዎች፣ እንዲሁም በብሔሩ ዙሪያ የተሰሩ ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች መኖራቸውን ፈትሻለሁ፡፡ በተጨማሪም ስለጉዳዩ ግንዛቤ ያላቸው አንዳንድ ሰዎችን በአካልና በስልክ በማነጋገር ለመረዳት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

ወደ መስክ በምወጣበት ወቅት ከትምህርት ክፍሉ የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ በ 17/4/2005 ዓ.ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነስቼ ጉዞዬን ወደ ሆሳዕና አደርግሁ፡፡ ከዚያም የዞኑ ዋና ከተማ የሆነችው ሆሳዕና አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ገባሁ፡፡ በማግስቱ ከትምህርት ክፍሉ ያፃፍኩትን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ለዞኑ ባህል፣ ቱሪዝምና መንግስት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ተወካይ ለነበሩት ለአቶ ወንድሙ አቡሌ ሰጠሁ፡፡ ጥናት ስለሚደረግበት ጉዳይ መስክ ከመሄዴ በፊት በስልክ አነጋግሬያቸው ስለነበር በማስታወስ ተወያየን፡፡

እሳቸውም የበለጠ ሊያግዙኝ ከሚችሉት የባህል ጥናትና ልማት የስራ ሂደት ባለሙያዎች ጋር አገናኙኝ፡፡ ከስራ ሂደቱ ባለሙያዎች ጋር ጥናት የሚደረግበት ጉዳይ ላይ የተወሰነ ውይይት ካደረግን በኋላ ጥናት የማደርግበት ጉዳይ ሲከወን መረጃዎችን ከተፈጥሯዊ መቼት ማግኘት የምችልባቸውን ወረዳዎችን ጠቁመውኛል፡፡ ጥናት የሚደረግበትን ስርዓት የመከወኛ አጋጣሚ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረትና ትዕግስት ማድረግ እንደሚገባኝ የስነ ልቦና ዝግጅት እንዳደርግ ግንዛቤ ፈጥረውልኛል፡፡ ወደ ወረዳዎቹ ሲሄድ ሊረዱኝ የሚችሉ ሰዎችን ጠቁመውኛል፡፡

በማግስቱም መረጃ ለመሰብሰብ የሚሆኑኝ አጋዥ መሳሪያዎችን በመያዝ መረጃ ታገኝባቸዋለህ ካሉኝ ወረዳዎች ውስጥ ወደ ሶሮ ወረዳ በመጓዝ የወረዳው ዋና ከተማ ከሆነችው ጊምቢቹ ገባሁ፡፡ በመቀጠልም ስለ ባህሉ፣ ጥናት ስለሚደረግበት ጉዳይ ግንዛቤ ያላቸው የመስክ ረዳት ሊሆኑኝ የሚችሉት አቶ አበበ ጊቻሞ ጋር በመደወል መገናኘት ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም የመስክ ተግባሬን ሊያመቻችልኝ የሚችል አንድ ሰው አገናኙኝ፡፡ ከሁለቱም ጋር ጥናት ስለሚደረግበት ጉዳይ ተወያየን፤ ከውይይታችን በኋላም መረጃዎችን በተፈጥሯዊ መቼት አውድ ተገኝቼ መሰብሰብ እንድችል ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹልኝ ነገርኳቸው ተስማማንና እዛው አድሬ በማግስቱ ሌሎች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ፡፡ ከሶስት ቀን በኋላም ደውለው የክዋኔው አጋጣሚ መኖሩን ገልጸውልኝ እንድገኝ ነገሩኝ፡፡

ስርዓቱ የሚከወንበት ሶሮ ወረዳ አምቢ ለንጌ ቀበሌ ለመድረስ ቦታው እርቀት ስላለውና በእግር ለመሄድ አስቸጋሪ በመሆኑ መጓጓዣ ማፈላለግ የግድ ሆነብኝ፡፡ ከዚያም ለመጓጓዣ

የሚሆኑ ሶስት ሞተር ሳይክሎችን አፈላልጌ ተከራየሁ፡፡ ሶስት ያስፈለገበት ምክንያት አንዱ ለእኔ፣ አንዱ ለመስክ ረዳት ሶስተኛው ደግሞ ቦታውን ለሚያሳየን ሰው ነበር፡፡ አስቸጋሪውን ድንጋያማ መንገድ በሞተር ተጉዘን ስርዓቱ የሚከወንበት ቤት ደረስን፡፡ እዚያም እንደደረስን የመስክ ረዳቱ ከሰዎቹ ጋር በመነጋገር የመጣሁበትን ጉዳይና አላማዬን ነግረው አስተዋወቁኝ፤ እነሱም ፈቃደኛነታቸውን ገለጹልኝ፡፡ በቦታው ሁለት ቀን በመቆየት መረጃ ልሰበስብ ቻልኩኝ፡፡

ከላይ በገለጽኩት አይነት በተለያዩ ጊዜያት የከዋኔ አጋጣሚዎችን የመስክ ረዳቶቼ በማፈላለግ በሶሮ ወረዳ ቡርይ ለንጌ፣ ኦምቤ ለንጌ እና ገባባ ለንጌ ቀበሌዎች ውስጥ፣ በጎንቦራ ወረዳ አዴአና እና ኦሌ ቀበሌዎች በጥቅሉ አምስት ቦታዎች ተገኝቼ መረጃዎችን ከአውዱ ሰበሰብኩ፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ከመስክ ረዳቶቼ ጋር በከዋኔ አጋጣሚ የተገኘሁባቸው ቦታዎች ላይ ሁሉ ትህትናን በተላበሰ ሁኔታ የምንበላውንና የምንጠጣውን በማቅረብ፣ የምንተኛበትን በማመቻቸት የተደረገልን መስተንግዶ፣ የተሰጠን ክብር በመልካምነት ሳልጠቅስ የማላልፈው ነው፡፡

በከዋኔ አጋጣሚዎቹ ተገኝቼ በመመልከት መረጃ ስሰበስብ ልገነዘብ ያልቻልኳቸውን ለመረዳት ቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ ተጠቅሜያለሁ፡፡ የጥናቱን አላማ ለማሳካት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥንቃቄ በማስተዋል ለትንታኔ በሚያመች መልኩ የማደራጀት ስራ አከናውኛለሁ፡፡ የሀድይኛ ቋንቋ አልፎ አልፎ ከመስማት ውጭ ስለማልችል መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ተርጓሚ ተጠቅሜያለሁ፡፡ በመተርጎም እገዛ ያደረጉልኝ በዞኑ ትምህርት መምሪያ እና ባህልና ቱሪዝም ውስጥ ባለሞያ የሆኑና ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታና ሂደት ወር ከአስራ አምስት ቀን መስክ ቆይቻለሁ፡፡

መረጃዎችን ሳደራጅ ግርታን ወይም ጥርጣሬ የፈጠሩብኝ ጉዳዮችን ክፍተት ለመሙላት በድጋሚ ከሚያዝያ 24/2005 እስከ ግንቦት 5/9/2005 መስክ ሂጄ አጣርቼ ተመልሼያለሁ፡፡ በዚህ ሂደት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተቀረፁ ቃላዊ መረጃዎች ወደ ጽሁፍ የመቀየር፣ በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጹ መረጃዎች ወደ ሲዲ የማስገልበጥ ስራ ተከናውኗል፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናትና ለማጥናትና ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ችግሮች አጋጥመው ነበር፡፡ ካጋጠሙት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋና የሆኑትንና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ጥናት ትልቅ ችግር የሆነው የበጀት እጥረት ነበር፡፡ ለጥናቱ ማካሄጃ ተብሎ ከዩኒቨርሲቲው የተመደበው ብር በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሆኖም ግን ያጋጠመውን የበጀት እጥረት አጥኚው ተቸግሮም ቢሆን በመሸፈን ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ችሏል፡፡

መረጃ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚገኝበት የራቁ በመሆናቸው፤ መረጃዎችን በከዋኔ አጋጣሚዎች ተገኝቶ ለመሰብሰብ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ የሆነ የመጓጓዣ ችግር አጋጥሟል፡፡ ችግሩንም ለመቅረፍ ሞተር ሳይክል በመከራየት መረጃ ሊሰበሰብ ተችሏል፡፡

ጥናት የሚደረግበት ጉዳይ ላይ መረጃ ለመሰብሰብ የከዋኔ አጋጣሚ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ ሌላው ተጠቃሽ ችግር ነው፡፡ ምክንያቱም ጥናት የሚደረግበት ስርዓት የሚዘጋጀውና የሚፈፀመው አልፎ አልፎ ከመሆኑም በላይ ያንን ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ከመስክ ረዳቶቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠሬ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ባደረጉት ጥረት የከዋኔ አጋጣሚዎችን ማግኘት ተችሏል፡፡

መረጃ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች መብራት ካለበት አካባቢ ራቅ ያሉ በመሆናቸው መረጃ ለመሰብሰብ በአጋዥነት የያዝኳቸው ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ውስጥ ቪዲዮ ካሜራ ባትሪ መጨረሱ ሌላኛው ችግር ነበር፡፡ ክፍተቱን ለመሸፈን ማስታወሻ በመያዝና ፎቶ ካሜራ መጠቀም ተችሏል፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ስር ጥናት ከሚደረግበት ርዕስ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተዛማጅ ጽሑፎች እና ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች የተቃኙበት ነው፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ከዚህ ቀደም በሀድያ ብሔር የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ላይ የተደረገ ጥናት ባላገኝም በሀድያ ብሔር የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች አግኝቻለሁ፡፡ እነሱም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የተሰሩ ናቸው፡፡ አምስቱ የባችለር ዲግሪ ሟሟያ ጽሁፎች (ዲማጽ) ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ  የኤም.ኤ ዲግሪ ሟሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው፡፡ እነዚህን ቀጥዬ በአጭር በአጭሩ እቃኛለሁ፡፡

አስቴር ሳሙኤል (1974) "የሀድያ ብሔር የዘፈን ግጥሞች" በሚል ርዕስ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ (ዲማጽ) አቅርባለች፡፡ የጥናቷ ዋና አላማ የሀድያ ብሔር የዘፈን ግጥሞችን በመሰብሰብ በይዘታቸው መከፋፈል ነው፡፡ አጥኟዋ መረጃዋን የሰበሰበችው ከሲቄ፣ ከኮንተብ፣ ከሌሞና ጠምባሮ ወረዳዎች እንደሆነ ገልፃለች፡፡

መረጃዎቹ የተሰበሰቡት የቃል መጠይቅ ዘዴን እንዲሁም መቅረፀ ድምጽና ማስታወሻ መያዝ በአጋዥነት በመጠቀም እንደሆነ ጠቁማለች፡፡ በጠቅላላው 117 የዘፈን ግጥሞች የሰበሰበች ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ በ 21ዱ ላይ ትንታኔ እንደሰጠች በጥናቷ ተገልጿል፡፡ አጥኚዋ ባደረገችው ትንተና መሰረት የዘፈን ግጥሞቹ የግርዛት ዘፈን፣ የሠርግ ዘፈን፣ የአብዮታዊ እና የስራ ዘፈን መሆናቸውን ገልፃለች፡፡ የዘፈን ግጥሞቹ የህብረተሰቡን ስነ ልቦናዊ አስተሳሰብ፣ ማህበራዊ ኑሮ እና ባህል የሚገልፁ መሆናቸው በማጠቃለያዋ ጠቁማለች፡፡

አጥኚዋ ለጥናቷ የሚሆኑ መረጃዎችን ሰብስባ ትንታኔ መስጠቷና የዘፈን ግጥሞቹን አባሪ አድርጋ ማቅረቧ በጥሩ ጎን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በጥናቷ ውስጥ በንድፈ ሀሳብነት ያነሳችው ጉዳይ አለመኖሩ፣ የዘፈን ግጥሞቹን እነማን እንዳቀበሏት መግለጽ አለመቻሏና ዝርዝራቸው በጥናቱ አባሪ ተደርጎ አለመቅረቡ እንደ ክፍተት የሚወሰዱ ናቸው፡፡

ቆጠራ ዮሐንስ (1975) "የሀድያ ተረትና ምሳሌዎች" በሚል ርዕስ ያቀረበው ዲግሪ ሊላው ተጠቃሽ ጽሁፍ ነው። አላማውም ተረትና ምሳሌዎቹን ለመጪው ትውልድ ሰንዶ ማስቀመጥ የሚል ነው። የሀድይኛ ተረትና ምሳሌዎችን በመሰብሰብ ይዘታቸውን ተንትኗል። መረጃዎቹን የሰበሰበው ከሀድያ ዞን ሶስት ወረዳዎች ሲሆኑ እነሱም ከሲቂ ወረዳ (ሲቁና ኢምቡርሴ) ፣ ከኮንተብ ወረዳ (ቦብቾና ዱባንቾ) እና ከሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ እንደሆኑ ተገልጿል።

አጥኚው አብዛኛዎቹን ተረትና ምሳሌዎች የሰበሰበው የቃል መጠይቅ ዘዴን በመጠቀም ሲሆን፣ ቀሪዎቹን ደግሞ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በስብሰባዎች፣ በለቅሶ ቤት እና በመጠጥ ቤት በመገኘት ማስታወሻ በመያዝ እንደሆነ ገልጿል። 461 ተረትና ምሳሌዎችን ሰብስቧል። በ 57 ላይ የይዘት ትንተና አድርጓል። በትንተናውም ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በመልካም ምግባር (ሐቀኝነት፣ ብልሀነት፣ ጀግንነት እና ትዕግስት)፣ እንዲሁም በመጥፎ ምግባር (ሌብነት፣ ስንፍና ችኩልነት፣ እልህና ስስት)፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እንደሚያነሱ ጠቅሷል። በጥናቱ ማጠቃለያ በተረትና ምሳሌዎቹ ጥናት የተደረገበት የሀድያ ብሔር በኑሮው ሂደት ላይ የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ጉዳዮች እንዴት እንደሚገነዘብ መረዳት እንደሚያስችሉ ተገልጿል።

የቆጠራ ጥናት ጥሩ ጎን መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅን መጠቀሙ፣ በተጨማሪም በአጋጣሚዎች በመገኘት ለመሰብሰብ ያደረገው ጥረትና ትንታኔ መስጠቱ ነው። የተረትና ምሳሌ ዝርዝሮችን አባሪ አድርጎ ማቅረቡም መልካም ነው። መረጃ ያቀበሉትን ሰዎች ዝርዝር አለማካተቱ የጥናቱ ጉድለት ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ሻውል በቀለ (1989) "የሀድያ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ የዘፈን ግጥሞች" በሚል ርዕስ ዲግሪ አቅርቧል። የጥናቱ አላማ በቃል የሚነገሩትን የቃል ግጥሞች በጽሁፍ ማስፈር፣ የዘፈን ግጥሞቹን በቅርፅና በይዘት መከፋፈል የሚል ነው። የዘፈን ግጥሞቹ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅን ተጠቅሟል። እንዲሁም ስንደዶ በሚቀጭበት ጊዜ፣ በሰርግ፣ በጥምቀት በዓልና በግርዛት መከሰቻ አጋጣሚዎች ተገኝቶ ምልከታ አድርጓል። አጥኚው መረጃ የሰበሰበው ከብሔሩ ተወላጅ ከሆኑና በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ አላቸው ከሚባሉ የእድሜ

ባለፀጋዎች ነው፡፡ ቁጥራቸውም አስራ ስድስት ወንዶችና ሶስት ሴቶች እንደሆኑ ዝርዝራቸው አባሪ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

አጥኚው በአጠቃላይ 107 የዘፈን ግጥሞች ሰብስቦ በ 51 ዱ ላይ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ በትንታኔው የዘፈን ግጥሞቹ በጎረምሶችና በኮረዳዎች የቀረቡና የሙገሳና የነቀፋ ይዘት ያላቸው መሆናቸው ገልጿል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ የከንፈር ወዳጆች የሚዘፍኗቸው ዘፈኖች ፍቅረኛን ከማሞገስ ወይም ከመንቀፍ በተጨማሪም ታታሪነት፣ ጨዋነትን፣ አስተዋይነት እና መልካም አስተዳደግን እንደሚያመለክቱ ጠቁሟል፡፡ ጥናቱ የተደረገው በሀድያ ዞን ቢሆንም አጥኚው ትኩረት ያደረገባቸውን ወይም መረጃ የሰበሰበባቸውን ቦታዎች በግለጽ አላስቀመጠም፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ (1993) "የባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሀድያ ብሔር" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት አላማ ብሔሩ ዕለት በዕለት የሚጠቀምባቸውን ቁሶች ማስተዋወቅ ነው፡፡ አጥኚው መረጃ የሰበሰበው በሀድያ ዞን ካሉት ወረዳዎች ውስጥ ሌሞ፣ ሶሮ፣ ምሻ እና ከባደዎች መሆኑን ገልጿል፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ የቃለ መጠይቅ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን፣ መረጃ ያቀበሉት ከብሔሩ ተወላጆች ውስጥ በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎች እና ገበሬዎች ናቸው፡፡ ዝርዝራቸውምን አባሪ አድርጎ አቅርቧል፡፡

በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በጥናቱ የተዘረዘሩት የቤት ዕቃዎች ለምግብ ማብሰያ (መገልገያ) አስራ ስድስት አይነቶች፣ ለእህል መስፈሪያና ማስቀመጫ የሚሆኑ አስራ አንድ፣ ለመጠጥ ማዘጋጃና መጠጫ ስምንት፣ ለእንሰት ስራ የሚያገለግሉ ስምንት፣ ለመቀመጫና መኝታ ዘጠኝ ለተለያዩ ተግባራት ሰላሳ ስምንት ናቸው፡፡ እንዲሁም ከእርሻ መሳሪያዎች ውስጥ ከማሳው ዝግጅት እስከ ዘር መዝሪያ ጊዜ የሚያገለግሉ አስራ አራት፣ በሰብል መሰብሰቢያ ወቅት የሚረዱ መሳሪያዎች አምስት እና ሌሎች ጠቃሚ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በጠቅላላው የ113 ቁሶችን ዝርዝር አቅርቧል፡፡ ባህላዊ ቁሶቹ ከሸክላ፣ ከድንጋይ፣ ከቀንድ፣ ከቆዳ፣ ከእንጨት እና ከብረት እንደሚሰሩም ጠቁሟል፡፡ በጥናቱ የቀረቡት የቤት ዕቃዎች እንዲሁም የእርሻ መሳሪያዎች የብሔሩን ባህልና ታሪክ እንደሚያስተዋውቁ በማጠቃለያው ገልጿል፡፡

አጥኚው ከአላማው አንጻር ያተኮረባቸው ባህላዊ ቁሶች ከምን እንደሚሰሩና አገልግሎታቸውንም ለመጥቀስ ያረገው ጥረት በጥሩ ጎን የሚጠቀስ ሲሆን ጥናቱ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያለው ንድፈ ሀሳብ አለመጠቀሙ ጉድለት ነው፡፡

ሌላው ተጠቃሽ ዲማጽ ተስፋዬ ሊሞሬ (1993) "የህዲይኛ ተረቶች ይዘት" በሚል ርዕስ ያቀረበው ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የህድያ ተረቶችን በመሰብሰብ የሚያንፀባርቁትን ማህበራዊ ጉዳች ማሳየት፣ የህድያ ተረቶችን ለአንባቢ ማስተዋወቅ እና ተረቶቹ እንዳይጠፉ አንዳዶቹን በመመዝገብ ማስቀመጥ ነው፡፡ ተረቶቹን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ስለ ሥነ ቃልና ስለ ተረት የተለያዩ ሀሳቦችን ከጥናቱ ጋር በማገናኘት ገለጻ አድርጓል፡፡ መረጃዎቹን የሰበሰበው ከሶሮ፣ ከሌሞ፣ ከምሻና ባደዋቾ ወረዳዎች እንደሆነ ጠቁሟል፡፡ በጠቅላላ 27 ተረቶች ሰብስቦ በ 8 ተረቶች ላይ ትንተና አድርጓል፡፡ ባደረገው ትንተና ተረቶቹ ከቅርጽ አንጻር መግቢያ፣ ሁተታ እና መደምደሚያ፣ የአጀማመር እና የአጨራረስ ህግ ያላቸው መሆኑን በተጨማሪም የተራችና የአድማጭ ሚና እንደሚታይባቸው ጠቅሷል፡፡ ከይዘት አንጻር ደስታን፣ ጀግንነት፣ ጥበብንና ብልፅግናን፣ አለማዋስተዋልን፣ ትዕግስትን፣ ህብረትንና ሀብትን ይገልጻሉ ብሏል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያም ተረቶቹ የብሔሩን አስተሳሰብ አኗኗር፣ እምነት፣ ባህልና ታሪክ አካተው መያዛቸውን ጠቅሷል ፡፡

አጥኚው አላማውን ለማሳካት ተረቶቹን ሰብስቦ ትንተና አድርጎ ያገኘውን ማስቀመጡ፣ የሰበሰባቸውን ተረቶች አባሪ አድርጎ ማቅረቡ በጥሩ ጎን የምጠቅሳቸው ናቸው፡፡ በአላማው ተረቶቹን ከቅርጽ አንጻር አያለሁ ብሎ ሳያስቀምጥ በጥናቱ ላይ ከቅርጽ አንጻር ትንታኔ መስጠቱ የጥናቱ ደካማ ጎን ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪ ሚሚያነት የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች ላይ ቅኝት አደርጋለሁ፡፡ ቅኝቱን የምጀምረው አዳነች ካሳ (2002) "የህድያ ሴቶች በቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሰረተ ቁላዊ ባህል ጥናት" በሚል ርዕስ ባቀረበችው ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ የህድያ ሴቶች በቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የሚታዩ ቁላዊ ባህሎችን አጥንቶ በጽሁፍ ማስቀመጥ የሚል ነው፡፡ አጥኚዋ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይት ዘዴዎችን ተጠቅማለች፡፡ ትንታኔ ያደረገችው

ስለቁሳዊ ባህል የዘርፉ ምሁራን ያስቀመጧቸውን ሞዴሎች በመጠቀም ነው፡፡ መረጃ ለማግኘት በዋናነት የመረጠቻቸው በዞኑ ካሉ ወረዳዎች ውስጥ ሆሳዕና ከተማ፣ ሌሞ፣ ሶሮ፣ ሚሻ፣ ጊቤ እና ምዕራብ ባደዋቾ ናቸው፡፡ ሴቶቹ በጋራ የሚከውኑባቸው ቡድኖች የጌጃ ቡድን (መታገገ)፣ የግላሴና ቡድን (በእርዱኝ የሚሰባሰብ) እና የወበጣ ቡድን (የእራስ ገላን ማጠብ) እንደሆኑ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡ ሴቶቹ በቡድን የሚከውኗቸው ተግባራት እንስት መፋቅ፣ የወበጣ ቀን ምግብ ዝግጅት፣ የጅባ ምንጣፍ እና የስፌት ስራዎች ናቸው፡፡ በትንታኔዋ ቁሶቹ ከተሰሩበት ተግባር ባሻገር ሲገለገሉባቸው ያታን፣ እድሜን ማህበራዊ ደረጃን እና የእርስ በርስ መስተጋብርን እንደሚያሳዩ ገልጻለች፡፡ በጥናቷ ማጠቃለያ ቡድኖቹ ከተመሰረቱበት አቢይ ክዋኔ በተጨማሪም ለሌሎች በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳዮችም እንደሚያገለግሉ ጠቁማለች፡፡ በተለይም ሴቶች በሴትነታቸው ለሚያነሷቸው ጉዳዮች ጥሩ አጋጣሚዎች መሆናቸውንና ለመደጋገፍ፣ በጋራ ለመሻሻል፣ የእለት ኑሮን ለመመራት የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልጻለች፡፡

ዝናሽ ሰለሞን (2004) "የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻና የሰርግ ስነ ስርዓት" በሚል ያቀረበችው ጥናት ዋና አላማ ባህላዊ ጋብቻና የሰርግ ስነ ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስሉ ማሳየት ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅንና የቡድን ውይይትን ተጠቅማለች፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በዞኑ ካሉ ወረዳዎች ውስጥ በምስራቅ ባደዋቾ (በአስር ቀበሌዎች) ላይ በማተኮር እንደሆነ ጠቁማለች፡፡ የክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን ስነ ዘዴ በማድረግ ገላጭ የትንተና ስልትን ተጠቅማለች፡፡

ሂረቻ (ወዶ ገብ)፣ ጎሰኖ (ጠለፋ)፣ ለዲሻ (በቤተሰብ ስምምነት)፣ ለጎ ገሲማ (የውርስ) የሚባሉ በብሔረሰቡ የሚታወቁ ባህላዊ የጋብቻ ዓይነቶች እንዳሉ በጥናቷ ገልጻለች፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በብዛት ተቀባይነት ያለውና በስፋት የሚከወነው (ለድሻ) በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀመው ጋብቻ እንደሆነ ጠቁማለች፡፡ በዚህ ባህላዊ ጋብቻ ስርዓት ከትውውቅ እስከ ሰርጉ ፍጻሜ ድረስ የተለያዩ ስርዓቶች እንዳሉ በመጥቀስ በሰርጉ ላይ የሚቀርቡት ባህላዊ ምግቦች እንዲሁም የሚዘፈኑት ዘፈኖች ትልቅ ትርጉም እንዳላቸው በጥናቷ አመልክታለች፡፡ ዝናሽ በጥናቷ ማጠቃለያ ብሔሩ ከትውውቅ እስከ ሰርጉ ባለው ሂደት በእያንዳንዱ ክዋኔ አማካይነት የሚተላለፉ መልዕክቶች በማህበረሰቡ የሚታወቁና ብሔሩንም የመግለፅ አቅም ያላቸው ናቸው ብላለች፡፡

በመጨረሻ ቀለመወርቅ ተክሉ (2004) "የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት ይጠቀሳል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሀድያ ብሔር ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች በማዜም በሚደረድሯቸው የቃል ግጥሞች የሚያነሷቸውን ጉዳዮች መተንተን ነው፡፡ አጥኚዋ ያተኮረችባቸው ወረዳዎች ሌሞ፣ አናሌሞ፣ ምሻ እና ጎንቦራ ናቸው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ዘዴዎችን ተጠቅማለች፡፡ መረጃዎቹን ያሰባሰበችው ሴቶቹ ስራቸውን በቡድንም ሆነ በተናጠል እያከናወኑ ሲያዜሙ አጋጣሚው ላይ በመገኘት ነው፡፡ በስራዎቹ አጋጣሚ የተሳተፉት ሴቶች ብዛት ዘጠና ስድስት እንደሆኑ በአባሪው ተገልጿል፡፡ ሴቶች ስራቸውን እየሰሩ የተገኙባቸው የስራ አይነቶች ስምንት ሲሆኑ እነሱም፡- ወተት መናጥ፣ ሙቀጫ መውቀጥ፣ ስንደዶ መልቀም፣ እረኝነት፣ ወፍጮ መፍጨት፣ እንሰት መፋቅ፣ የጓሮ አትክልት መኮትኮትና እንጨት ለቀማ ናቸው፡፡ የሰበሰበቻቸው ቃል ግጥሞች 156 ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 47ቱ ቃል ግጥሞች ላይ ትንታኔ ሰጥታለች፡፡

ባደረገችው ትንታኔም የስራን መልካምነት፣ የእንሰት ተክልን ማወደስ፣ ዝና እና ጀግንነትን ማውሳት ፣ ውበትን ማድነቅ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ ጨዋታ፣ ስለከንፈር ወዳጅ እንዲሁም የሀድያ ሴቶችን ማንነት የሚገልጹ ሀሳቦችን አንስታለች፡፡ በስራዎቹ አጋጣሚም የሚዘፈኑት ዘፈኖች ከስራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውና የሌላቸው ናቸው፡፡ በስራ አጋጣሚዎቹ ወቅት ዘፈኖቹን በቡድንም ሆነ በተነጣል መዝፈናቸው (ማዜማቸው) የስራውን አድካሚነት ለመርሳት እንደሚረዳቸው ገልጻለች፡፡ መንፈሳቸውን እንደ አድርጎ ለማበረታትና በዘፈኑ ለመዝናናት እንደሚረዳቸውም ጠቅሳለች፡፡ በጥናቷ ማጠቃለያ ቃል ግጥሞቹ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ህይወት፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንደሚያነሱ ገልጻለች፡፡

ለሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያነት የተደረጉት ጥናቶች አላማቸውን ለማሳካት ያደረጉት ጥረት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴያቸውና ትንታኔ ለመስጠት የተከተሉት መንገድ በጠንካራ ጎንነት ሊጠቀስላቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡

በአጠቃላይ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያነት ቀርበው ቅኝት የተደረገባቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምዳቸው ነገር ቢኖር ይህ ጥናት በሚጠናበት

አካባቢ ላይ የተሰሩ በመሆናቸውና ፎክሎራዊ ጉዳይን በመያዛቸው ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የኔ ጥናት ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ዝምድና የላቸውም፡፡

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

የፎክሎር ዘርፎች በአራት ዋና ክፍሎች እንደሚመደቡ Dorson (1972፡2-5) ይገልፃሉ፡፡ እነሱም ስነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ ናቸው:: የዚህ ጥናት ትኩረት በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ በሚካተት የፎክሎር አይነት ላይ በመሆኑ ስለ ሀገረሰባዊ ልማድ ጥቂት ነጥቦችን አነሳለሁ፡፡ እንደ Dorson አገላለጽ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚካተቱ አራት ርዕሰ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም ፌስቲቫሎችና ክብረ በዓላት፣ መዝናኛ ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒት እና ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች ናቸው፡፡ የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍሎች ሰዎች በቡድን ወይም በጥንድ የሚከውኗቸው ደስታና ሀዘናቸውን የሚጋሩባቸው፣ በሀገረሰባዊ እውቀት ህግና ደንብ የተበጀላቸው ልማዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም "ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓተ ክዋኔ በሀድያ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ጥናት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚጠቀሱት ውስጥ በባህላዊ ስርዓተ ከበራ (Ritual) ላይ ያተኩራል፡፡

### 2.2.1 ባህላዊ ስርዓቶች

ባህላዊ ስርዓቶች (Rituals) ሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ባህላዊ ስርዓተ ከበራዎች በጋራ የሚከውኗቸው ሲሆኑ ባህሉንና ልማዱን ተከትለው በተለያዩ ዝግጅቶች የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ባህላዊ ስርዓት የተለያዩ ድርጊቶች፣ እንቅስቃሴዎች የሚታይበትና የየራሱ አደረጃጀት አለው፡፡

ባህላዊ ስርዓተ ከበራዎች እንደየማህበረሰቡ ባህል፣ ወግና ልማድ የየራሳቸው የሆነ መለያ ቅርፅ አላቸው፡፡ የሚፈጽሟቸው ማህበረሰቦች (ቡድኖች) ይግባቡባቸዋል፡፡ መግባባቱም በቃል ምልልስ እና በድርጊት ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ እንደሆነ Bell (1997፡ 91-3) እና Gruenwald (2003፡ 2) ያብራራሉ፡፡

ስርዓተ ከበራዎች ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ እና እንዲሁም ደግሞ ሳይያያዙ ሊተገበሩ ይችላሉ፡፡ Sims and Stephens (2005፡103) ሲጠቅሱ መንፈሳዊ (*Sacred*) ከሀይማኖት ጋር በተገናኘ የሚፈፀሙ ወይም የሚከበሩ ስርዓቶች ሲሆኑ፤ ሰዎቹ ስርዓቱን በመተግበራቸው ከልዕለ ተፈጥሮ ኃይል *(Super Natural Power)* ጋር የጠበቀ ግንኙነት ትስስር እንደሚፈጥሩበት ይገልጻሉ፡፡

ሃይማኖታዊ ያልሆኑት (Secular) ስርዓቶች ደግሞ ማህበረሰቡ ከኑሮው (ከህይወቱ) ጋር በማገናኘት፡ ወይም ህይወቱን በመቅረጽና በመምራት ረገድ ተጠብቀው ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ሚና አላቸው፡፡ መንፈሳዊና አለማዊ ስርዓቶች ተለያይተው ቢቀርቡም ብዙ ጊዜ አለማዊውም ሆነ መንፈሰዊው ባህላዊ ስርዓቶች እርስ በርስ ተያይዘው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

ባህላዊ ስርዓቶች በየማህበረ ባህሉ የሚከወኑት ለተለያዩ ጉዳዮች ሲሆን፤ ክዋኔያቸው በማህበረሰቡ እምነት፡ ልማድና አመለካከት የተቃኘ ነው፡፡ Sims and Stephens (2005፡ 94) ማህበራዊ ስርዓቶች ከሚከወኑባቸው ምክንያቶች አንዱ የተለያዩ ማህበራዊ ክስተቶችንና አጋጣሚዎችን ለመጠቆም ለማብሰር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

ባህላዊ ስርዓቶች የራሳቸው መገለጫ አላቸው፡፡ መገለጫ ከሚባሉት ውስጥ ደግሞ አንዱ ክዋኔ ነው፡፡ እያንዳንዱ ስርዓት እንደየባህሉ የራሱ የሆነ ቅርፅና የክዋኔ ስልት አለው፡፡ ምክንያቱም ስርዓት ያለ ክዋኔ ሊካሄድ አይችልምና ነው፡፡ አንድ ስርዓት በሚከወንበት ወቅት በንግግር በድርጊት፡ በምልክት፡ በቅደም ተከተል ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ጎልተው የሚታወቁት ደግሞ ሲከወኑ ነው፡፡ ሲከወኑም በከዋኙ፡ በተሳታፊውና በታዳሚው መካከል መግባባትን ይፈጥራሉ፡፡ በተግባቦቱም መልዕክት ይተላለፋል፡፡ ስለዚህም አንድ ስርዓት የሚከወንበት ቦታ፡ የክዋኔው ጅማሬ ሂደትና ማብቂያ የሚጠቀማቸው ትዕምርቶች በማህበረሰቡ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ትዕምርቶችም በባህሉ ደንብና ስርዓት የሚያስተላልፉት፡ የሚወክሉት ጽንስ ሀሳብ አላቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም Rappaport (1992፡ 252) *"A ritual is an order of acts and utterances and as such is enlivened or realized only when those acts are performed and those utterances voiced."* በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሌላው የባህላዊ ስርዓቶች መገለጫ ተደጋግመው መከናወናቸው፤ በከዋኔው ላይ ለሚገኙ የማህበረሰቡ ቡድኑ አባላት በተለይም ተተኪው ትውልድ ስለባህል ልማዳቸው በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማስቻላቸው ነው፡፡ ባህላዊ ስርዓቶች መከወናቸው ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉና እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል፡፡

Rappaport (1992፡ 255) እንደሚገልጹት በማንኛውም ስርዓት ውስጥ ሊለወጡ የማይችሉ ዶግማዊ (canon) የሆኑ መለያዎች አሉ፡፡ በማህበረ ባህሉ ልማድና ደንብ መሰረት ስርዓቱ የሚታወቅባቸው መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች አይነኩም፡፡ ምክንያቱም ስርዓቱ ሲተገበር የሚታወቅባቸው ዋና ዋና ነገሮች መረጃ እና መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸውና፡፡ ዶግማዊ የሆኑት ጉዳዮች ሊዛቡ አይገባም፡፡ ዶግማዊ ጉዳዮች የሚዛቡ ከሆነ የመልዕክት ለውጥ ሊመጣ ይችላል ይላሉ፡፡

በመቀጠል ደግሞ ከስርዓት አይነቶች መካከል ወግ ማዕረግ (*Rites of passage*) ስለሚባለው ስርዓት እንመልከት፡፡

**የወግ ማዕረግ ስርዓት** (Rites of passage)

የሽግግር (ወግ ማዕረግ) ስርዓት ከባህላዊ ስርዓቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሰዎች በህይወት ዘመናቸው ውስጥ የተለያዩ የወግ ማዕረግ ስርዓቶችን ይፈፅማሉ፡፡ ስርዓቱን የሚፈፅሙት በባህላቸው መሰረት ነው፡፡ የወግ ማዕረግ ስርዓት የሚፈፀምላቸው ሰዎች ካሉበት ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላኛው መሸጋገራቸውን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ የሽግግር ስርዓት ከሚደረግባቸው መካከል ለአብነት ያህል ጋብቻና ልደትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በጥቅሉ ወግ ማዕረግ የህይወት ዘመን ዑደትን *(Life - cycle)* ያካትታል፡፡

የሽግግር ስርዓቶችን Bell (1997፡ 94) በሁለት ይከፍላሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ በህይወት ዘመን ከአካል ዕድገት ጋር የሚገናኙ ሲሆኑ፤ ተፈጥራዊ ሂደቶችን ማህበረ ባህሉ በሚረዳበት መልኩ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በሁለተኛነት የሚጠቀሱት ደግሞ ከሰው ልጅ አካል እድገት ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው በማህበረ ባህሉ ልማድ መሰረት አንድ ሰው በእድሜ ዘመኑ በተሰማራበት መስክ የተለየ ተግባር በመስራቱ የሚዘጋጁ ስርዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች የሚፈጸሙት አንድ ሰው በማህበረ ባህሉ የተደነገጉትን ሲያሟላ፣ የተለየ ተግባር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**የህይወት ዘመን ዑደት** (life - cycle)

ሰዎች በሚኖሩበት ዘመን በባህላቸው ደንብና ልማድ መሰረት መፈፀም የሚገባቸውን ፈጽመው ሲገኙ እውቅና የሚሰጥባቸው የተለያዩ ነገሮች አሉ፡፡ አንድ የማህበረሰቡ አባል እውቅና የሚሰጠው የማህበረሰቡ ባህል በደነገገው መሰረት ተገቢውን መፈፀሙ ወይም ሟሟላቱ በማህበረሰቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ተግባሩን በደንቡ መሰረት መፈፀሙ ሲረጋገጥ ባህላዊ ስርዓት ይዘጋጅለታል፡፡ በባህሉ መሰረት ግለሰቡ የተለየ ማህበራዊ ደረጃ እና መጠሪያ ስያሜ ይሰጠውና ዕውቅናን ይላበሳል፡፡ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ስርዓት እንዲሁ አይዘጋጅም፡፡ ስርዓቱም የራሱ የሆነ መለያ ወይም መገለጫ አለው፡፡ Bell "The *logic of these rites credits symbolic stages and passages that redefine social and personal identify*" (1997፡95) ይላሉ፡፡

አንድ ባህላዊ ስርዓት በሚፈፀምበት ወቅት እንደ አውዱ እና የስርዓቱ ቅርፅ የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎችን በተጨማሪነት ይዞ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በመዝፈን፣ ባህላዊ ቁሶችን በመያዝ፣ አካላዊ እንቅስቀሴ በማድረግ፣ ምግብ በማዘጋጀት በጥምረት በስርዓቱ ሊቀርቡ እንደሚችሉ Sims and Stephes (2005፡ 97) ጠቅሰዋል፡፡ በስርዓቱም ላይም በዋናነት ስርዓቱን የሚፈፅሙትና የሚያረጋግጡት አባላት እና የተሳታፊ ሰዎች የአቀማመጥ ስርዓት ይኖራቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊ ስርዓት እንደየማህበረሰቡ ባህልና እምነት የተለያዩ አገልግሎቶች ይኖሩታል፡፡ ማህበረሰቡን (የባህሉን ባለቤቶች) ያስተዋውቃል፣ የስርዓቱን አገልግሎት ፋይዳ ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም የአንድ ማህበረሰብ ባህል እንዲጠነክርና እንዲቀጥል ያደረጋል፡፡

### 2.2.2 ክዋኔ

አንድን የፎክሎር ዘርፍ የበለጠ ተረድቶ ለማጥናት በክዋኔው ላይ ተገኝቶ መረጃ መሰብሰብን ይጠይቃል፡፡ ክዋኔ ስለተጠኚው ማህበረሰብ ስለሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ያስችላል፡፡ በክዋኔ ወቅት የተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች ይፈፀማሉ፡፡ ባህላዊ እሴቶቹ ማህበረሰቡ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ከመሆናቸውም በላይ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለያዩ ፋይዳዎች ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ

ሲከወን እንደ ማህበረሰቡ እምነት አመለካከት የሚያበረክተው ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ስነ ልቦናዊ የሆነ አንዳች ፋይዳ አለው፡፡

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚከወንበት ወቅት የማህበረሰቡ ባህል፣ ታሪክ፣ ጥበቡ እና እምነት አመለካከቱ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ክዋኔ የራሱ ማራኪ ጥበባዊ አቀራረብ አለው፡፡ የከዋኙ፣ የተሳታፊውና የታዳሚው ሚና በመከወኛ ባህላዊ ቁሶቹ በመታጀብ ይቀርባል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡን የማግባባት ፋይዳ አለው ሲሉ Bauman (1992፣ 41- 44) ፣ Finnegan (1992፣ 89-95) እንዲሁም Sims and Stephens (2005፣137-139) ገልፀዋል፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይን የበለጠ ተረድቶ ለማጥናት በክዋኔው አውድ መገኘት ይኖርበታል፡፡ ቀጥለን ስለ አውድ የተወሰኑ ነጥቦችን እንመልከት፡፡

**አውድ**

Bauman (1983፣ 362-367) በክዋኔ ፎክሎርን መረዳት የሚቻለው በማህበረሰቡ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ መሰረት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ባህላዊና ማህበራዊ አውዶች በውስጣቸው የተለያዩ ጉዳዮችን ይይዛሉ፡፡ እነዚህን በዝርዝር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**ባህላዊ አውድ**

Bauman እንደሚሉት ባህላዊ አውድ የአንድ ማህበረ ባህል አባላት የሚግባቡበት ነው፡፡ በውስጡም ሶስት ንዑሳን አውዶች ይይዛል፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

የትርጉም አውድ (Context of Meaning) አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይን ለመረዳት ከሚያስችሉ ባህላዊ አውዶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ አውድ የአንድ ማህበረሰብን ባህል፣ አኗኗሩን እምነቱን፣ ስርዓቶቹን፣ እሴቶቹንና ተምሳሌቶቹን ይመለከታል፡፡

ተቋማዊ አውድ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚተገበርበትና ጥቅም ላይ የሚውልበት፣ የራሱ ተቋም አለው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ተቋማትም የየራሳቸው አላማና ግብ ይዘው የተመሰረቱ ናቸው፡፡ እነሱም እምነት/ሀይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ተቋማት ውስጥ ያሉ ፎክሎሮች በምንና እንዴት ይገኛሉ? ይግባባሉ? በሚለውና ፋይዳቸው ላይ ያተኩራል፡፡

የተግባቦት አውድ (Context of Communication) አንድ የፎክሎር አይነት ከሌላው የፎክሎር አይነት ጋር ያለውን ዝምድና ይመለከታል፡፡

### ማህበራዊ አውድ

ማህበራዊ አውድ ብዙ ሰዎችን ሊይዝ ወይም ሊያሳትፍ የሚችል አውድ ነው፡፡ ይህን አወድ ለመረዳት የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ መዋቅሮችን መረዳትና ማጤን ይገባል፡፡ ማህበራዊ አውድ በውስጡ የተለያዩ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነዚህም ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድና ሁኔታዊ አውድ ናቸው፡፡

ማህበራዊ መሰረት (Social Base) ከሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ባለቤቶች ጋር ተያይዞ ያለውን ይመለከታል፡፡ አንድን ፍክሎራዊ ጉዳይን ለማጥናት ማህበረሰቡን ወይም ቡድኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እድሜ፣ ፆታና ሙያን በማህረባዊ ደረጃ እና በልዩ ልዩ ቡድኖች ይከፈላሉ፡፡ ስለዚህም የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለማጥናት ማህበራዊ አውድ መነሻነት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ግለሰባዊ አውድ ፎክሎር በማህበርና በቡድን እንደሚገልፅ ሁሉ በግልም ይገለፃል፡፡ ግለሰቡ ለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም፣ ያለው አመለካከለት ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ያለው ሁኔታ በዚህ አውድ ይመረመራል፡፡

ሁኔታዊ አውድ የተግባቦት አውድ ነው፡፡ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይን በባህሉ ባለቤቶች በሚከወንበት ጊዜ ያሉትን ሁነቶች (events) ለማወቅ ትርጉም ለመስጠት የሚያግዝ አውድ ነው፡፡ የፎክሎር አጥኚዎችም በብዛት የሚጠቀሙበት አውድ ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ የሚጠናው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በባህሉ ባለቤቶች በሚከወንበት ጊዜ መቼቱን የተሳታፊዎችን ወይም የታዳሚዎቹን ማንነትና ሚናቸውን፣ ከዋኔው የሚመራበት ባህላዊ ህጎች፣ በከዋኙና በታዳሚው ያሉ መግባባቶች አተረጓጎም፣ ድርጊቶች ቅደም ተከተልን ሁኔታውን ለመረዳት ያስችላል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ለማጥናት እና ለመረዳት አጥኚው በአውዱ በመገኘት ሲከወን ከባህሉ አንፃር ማየት ይጠበቃል፡፡ አጥኚው በከዋኔ ላይ ትኩረት አድርጎ ሲያጠና ከዋኝ፣ ተሳታፊ ወይም ታዳሚ፣ መቼት፣ የመከወኛ ቁስ፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ ህገ ደንብ መልዕክቱን በጠቅላላው አውዱን መመልከት አለበት፡፡

## 3. የጥናቱ አካባቢ

የሀድያ ብሔር በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከሚገኙ 14 ዞኖች እና 4 ልዩ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ዞኑ በአስር ወረዳዎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ሲሆን፣ ርዕሰ ከተማዋም ሆሳዕና በመባል ትታወቃለች፡፡ ሆሳዕና ከክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ በስተ ሰሜን 203 ኪ.ሜ እንዲሁም ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 230 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የሀድያ ዞን በደቡብ ምስራቅ ከሀላባ ልዩ ወረዳና ከኦሮሚያ ክልል፣ በሰሜን ምስራቅ ከስልጢ ዞን፣ በምዕራብ ከየም ልዩ ወረዳና ኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከከምባታ ጠምባሮና ወላይታ ዞኖች እና በሰሜን ከጉራጌ ዞን ጋር ይዋሰናል፡፡ እንደ Hadiya Zone Finance and Economic Development መፅሔት (2004፣ 8) በ 2004 ዓ.ም የዞኑ የህዝብ ብዛት 1,386,984 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 689,686 ወንዶች 697,298 ሴቶች ናቸው፡፡

### 3.1 መልክአምድራዊ አቀማመጥ

የሀድያ ዞን መልክአምድር ሜዳማ፣ ተዳፋት እና ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ አለው፡፡ የዞኑ ስነ ህዝብ ማስተባበሪያ አመታዊ መጽሔት (2004፣ 8) ላይ እንደቀረበው የዞኑ የቆዳ ስፋት 4,109 ካሬ ኪሎ ሜትር እንደሚደርስ ሲገመት ከዚህም ውስጥ 69% የለማ፣ 7.22% ሊለማ የሚችል፣ 7% ለግጦሽ የዋለ፣ 8.78% በደንና በቁጥቋጦ፣ እንዲሁም ቀሪው 8% በሌሎች የተሸፈነ ነው፡፡ የአየር ንብረቱም 19% ደጋማ፣ 68.1% ወይናደጋማ እና 12.9% ደግሞ ቆላማ ነው፡፡

### 3.2 የሀድያ ብሔር መተዳደሪያ

#### 3.2.1 እርሻ

የሀድያ ብሔር ዋና መተዳደሪያ እርሻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዞኑ ካለው መሬት ውስጥ በግብርና ለአመታዊ ሰብል 63%፣ ለቋሚ ሰብል 6% አገልግሎት እንደሚውል ተገልጿል፡፡ በዋናነት ከሚመረቱት ውስጥ እንሰት፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ በርበሬ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምርቶች ከፍሪዎቹ ፍጆታ አልፈው በሽያጭም እንደሚቀርቡ ተጠቅሷል፡፡ (የዞኑ ስነ ህዝብ ማስተባበሪያ አመታዊ መጽሔት፣ 2004፡31)፡፡

### 3.2.2 ከብት ማርባት

በብሔሩ ዘንድ ከእርሻ ስራ በተጓዳኝ የቀንድ ከብቶችን ማርባት የተለመደ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ያቀበሉኝ አቶ እሸቱ ጡሚሶ "በሀድያ አንድ ግለሰብ በርካታ ቁጥር ያላቸው የቀንድ ከብቶችን ማርባት ልማድ ከጥንት አባቶቻችን ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን አሁን ለግጦሽ የሚሆን ቦታ ጥበት ከመኖሩ የተነሳ እንደድሮው በብዛት የማርባቱ ሁኔታ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በተለይም በሶሮ፣ ጎምቦራና ጊቤ ወረዳዎች ውስጥ በርካታ ከብቶችን የማርባት ልማድ አለ፤" ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 2/2005) ፡፡

እንደ አቶ እሸቱ ገለጻ በእነዚህ ወረዳዎች በአሁኑ ጊዜም ብዙ ከብቶችን የማርባቱ ልማድ ሳይጠፋ ቀጥሎ ያለው ቆላማ በሆኑት አካባቢዎች ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በብዛት ያልሰፈሩባቸው ሰፋፊ ቦታዎች በመኖራቸውና ለከብቶች የሚሆን መኖ በመኖሩ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በሌሎች የዞኑ አካባቢዎች ከብቶች አይረቡም ማለት አይደለም፡፡ ከላይ እንደ ተጠቀሱት ወረዳዎች ቆላማ አካባቢ እንደሚረቡት በርካታ ቁጥር ያላቸው ከብቶች አያርቡ እንጂ ለወተት የሚሆኑ በጣም አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ከብቶች ያረባሉ፡፡

## 3.3 መሰረተ ልማት

በዞኑ ውስጥ ለማህበረሰቡ አገልግሎት የሚሠጡ የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም መንገድ ተጠቃሽ ነው፡፡ የዞኑን የመንገድ ሁኔታ ስንመለከት ርዕሰ ከተማዋ ሆሳዕናን ከሁሉም የወረዳ ዋና ከተማዎች የሚያገናኝ የጠጠር መንገድ አለ፡፡ ዋና ከተማዋን ከሌሎች ከተሞች ጋር ማለትም ከአዲስ አበባ፣ ከናዝሬት፣ ከሀዋሳ፣ ከቡታጅራ፣ ከዝዋይ፣ ከወራቤ፣ ከዱራሜ፣ ከወላይታና ከአርባ ምንጭ የሚያገናኛት የአስፋልት መንገድ ያለሲሆን፤ ከወልቂጤ ጋር ደግሞ በጠጠር መንገድ ትገናኛለች፡፡

ርዕሰ ከተማዋን ሆሳዕናን ጨምሮ ሁሉም የወረዳ ዋና ከተማዎችና አንድ አንድ የገጠር ቀበሌዎች የ24 ሰዓት የሀይድሮ ኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ የመደበኛ እና የሞባይል ስልክ አገልግሎትም ተጠቃሚ ናቸው፡፡

## 3.4 ባህላዊ አስተዳደር

በሀድያ ብሔር የተለያዩ እርከን ያላቸው ባህላዊ አስተዳደሮች እንዳሉ መረጃ አቀባዩ ዳኛ ደሳለኝ ሱጌቦ ነግረውኛል፡፡ እነሱም 1ኛ ምኔ (የቤተሰብ መሪ)፣ 2ኛ ሞል ዳና (የጎጥ መሪ)፣ 3ኛ ሱል ዳና (የነገድ መሪ)፣ 4ኛ ጊቾ ዳና (የጎሳ መሪ)፣ 5ኛ ጊራ (የብሔረሰብ መሪ) የተሰኙት ደረጃዎች ባህላዊ የአስተዳደር እርከኖች ናቸው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 16/2005)፡፡

የሀድያ ባህላዊ አስተዳዳሪዎች አመራረጥ መመዘኛዎች አሉት፡፡ የሚመረጠው ግለሰብ ግላዊ ብቃት እና የህብረተሰቡ አመለካከት የሚሉት መስፈርቶች ናቸው፡፡ ግላዊ ብቃት ሲባል የብሔሩን ባህላዊ እሴቶችን ጠንቅቆ የማወቅ፣ አንደበተ ርዕቱነት፣ አስተዋይነት፣ የተረጋጋ፣ ቀናነት፣ ለጋሽነት፣ የሽምጋይነትና የይቅርባይነት ችሎታና ልምድ፣ ሀቀኝነት፣ የስራ ተነሳሽነትና የህብት ደረጃ (አጠቃላይ የኑሮው ሁኔታ) የሚስቱ ከሰው ጋር ያላት መግባባት፣ ደግነት፣ የስራ ታታሪነት ወዘተ. ናቸው፡፡ የህብረተሰቡ አመለካከት መመዘኛን በተመለከተም፤ በባህሉ መሰረት ከጎሳ ወይም ከቤተሰብ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአስተዳደር ልምድ፣ የቤተሰብ ወይም የጎሳ ደረጃ ከፍ ያለ መሆን፣ የሚነቀፍበት እንከን፣ ጉድለት የሌለው የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መስፈርቶች አንጻር በኃላፊነት የታጨው ግለሰብ በግል ብቃቱና በህብረተሰቡ አተያይ ተመዝኖ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ለሀላፊነት እንዲበቃ ይደረጋል፡፡ ለሀላፊነት የሚበቃው እንደ ስልጣን እርከኑ መጠነኛ ከሆነ (ጨምበለቃ ሉባ) ወይም ከፍተኛ ከሆነ (ጨለለቃ ሉባ) ድግስ ተደግሶ በባህሉ ልማድ መሠረት ተመርቆ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ (ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ፕሮፋይል 2001፥13) ፡፡

በፕሮፋይሉ ላይ እንደተገለጸው የሀድያ ባህላዊ አስተዳደር የተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎችና ማዕረጎች አሉት፡፡ እነሱም "አድላ /ገራድ/፣ ወሸባ፣ ደዳቾ፣ አስማቹኤ፣ አበጋዝ፣ አባገዳ፣ አንጃቾ፣ ገደብ ገራድ፣ አሸን ገራድ፣ ወለብ ገራድ፣ ይማም እና መጋባ" የተሰኙ ናቸው፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ‹አድል /ገራዳ/› ከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ ዕርከን ሲሆን ለብሔሩ ነገስታት /ሡልጣኔት/ የሚሰጥ የማዕረግ መጠሪያ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ባህላዊ የማስተዳደር ስርዓት ዳኝነት ስልጣን በሀድያ ባህል የየጎሳ መሪዎች ሲሆን እነሱም ጉዳዮችን በየደረጃው በማየት ለሚቀጥለው ባህላዊ የአስተዳደር እርከን ያስተላለፋሉ፡፡

የሀድያ ባህላዊ አስተዳደር ስርዓት "ሴራ" ይባላል (ኤርሲዶ አንታሴ1999፡18) ፡፡ በዋናነት ባህላዊ አስተዳደሩ የሚያተኩረው ባህላዊና ማህበራዊ ስርዓቶችን በማስከበር፣ ህዝቡን ከጥቃት መከላከል፣ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ በማስወገድ፣ የአስተዳደሩን ሹማምንት በመሰየም ላይ ነው፡፡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የዳኝነት ጉዳዮች መካከል የቤት ቃጠሎ፣ የስርቆት፣ የክህደት፣ የድንበር መጣስ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 4. የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት

በዚህ ምዕራፍ ስለ ሀድያ ብሔር የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ከዋኔ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት አጀማመር፣ ስርዓቱን ለማካሄድ የሚሟሉ መሰረታዊ ነጥቦች እና የቆጠራው ስርዓት ከዋኔ ሂደት በቅደም ተከተል ይገለጻሉ፡፡

### 4.1 ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት አጀማመር

ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ማለት አንድ ከብት አርቢ ከብቶቹ ከሙቶ በላይ ሲሆኑለት ድግስ በመደገስ ሰዎች አውቀውለት ከሀብቱ ጋር በተያያዘ የክብር ማዕረግ ስያሜ የሚያገኝበትና የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው፡፡ አቶ እሸቱ ጡሚሶ "‹ወገና› የሚለው ቃል ትርጉም ውሃ መርጨት ማለት ሲሆን፤ ይህም ስርዓቱ ሲፈጸም ውሃ፣ ማር እና ወተት ተቀላቅለው በከብቶቹ ላይ ሲረጭ ነው፡፡ ስለዚህም ‹ወገና› የስርዓቱ መጠሪያ ስያሜ ነው ሲሉ፤" ገልጸውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 30/2005)፡፡

የወገና ስርዓት አጀማመርን በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦች ይጠቀሳሉ፡፡ መቼ እንደተጀመረ ቁርጥ ያለ መልስ ማግኘት አልተቻለም፡፡ አሁን ያሉት የብሔሩ አባላት ከአባቶቻችን ሰማን ያሉትን ከመግለጽ በስተቀር የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነው ለማለት የሚያስችል፣ ሁሉንም የሚያስማማ አንድ መልስ የላቸውም፡፡ በአብዛኛው የሚስማሙት ግን ከቀዳማዊ ምንሊክ ዘመነ መንግስት በፊት ጀምሮ ስርዓቱ የቀጠለ ነው በሚለው አሳብ ነው፡፡ በሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ ከተማ አስር ሰዎች በተሳተፉበት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ የወገና ስርዓት የአጀማመር ሂደትን ጠይቁ ዳኛ አቤቦ ለሴሶ የተባሉት ተሳታፊ እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡-

> *... የቀንድ ከብቶችን በብዛት የማርባቱ ልማድ የቆየ ነው፡፡ ከብቶችን በብዛት ማርባት ደግሞ በወቅቱ የሀብታምነት መለኪያና መገለጫ ሲሆን ታዋቂነትንም ያስገኝ ነበር፡፡ ስለዚህም ብዙ ከብቶችን ያረባ ባለ ብዙ ከብት፣ ሀብታም ተብሎ ሲታወቅ፤ በሌሎቹ አርቢዎች ዘንድም ፉክክር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ፉክክሩ ባለብዙ ከብት፣ ሀብታም ተብሎ ለመታወቅ ከፍተኛ ምኞትንና ጉጉትን ይፈጥርባቸዋል፡፡ እንዲህ እያለ እስካሁን ድረስ ይህ የቆጠራ ስርዓት ቀጥሏል፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ፣ 26/2005 ዓ.ም) ፡፡*

እንደ መረጃ አቀባዮቹ አገላለጽ በሀድያ ብሔር በርካታ ቁጥር ያላቸው የቀንድ ከብቶችን የማርባቱ ልማድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ ብዙ ከብቶችን ያረባ ደግሞ ሀብታም፣ ከመባሉም ባሻገር ዝናንና ዕውቅናን ያገኛል፡፡ በከብቶቹ ብዛት የታወቀውና ሀብታም የሆነው አርቢ ከሌሎቹ አርቢዎች ተለይቶ ለግጦሽ የሚሆኑ ቦታዎችን በመከለል ግዛቱ ያደርጋል፡፡

ከብቶችን ማስቆጠር ዕውቅናን የሚያላብስ እና የማዕርግ ስምን የሚያሰጥ በመሆኑ በሁሉም ዘንድ ከብቶችን ማርባት እና የግጦሽ ቦታን መከለል ልማድ ሆነ፡፡ በዚህም የተነሳ በከብት አርቢዎች ዘንድ የእርስ በርስ ፉክክሩ ቀጠለ፡፡ ሲፎካከሩም በከብቶቻቸው ብዛት መተቻቸት ተፈጠረ፡፡ ቆይቶም መፎካከሩ እና መተቻቸቱ የሀብት መለኪያ እርከን እንዲወሰን አስገደደ፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት አበጋዝ[1] ስዩም ደሪሎ የተባሉት የከብቶቹ ብዛት ምን ያህል ነው? በማለት ላቀረብኩት ጥያቄ "ከብቶችን በማርባት ሀብታም፣ ባለብዙ ከብት ለመባል የሚጠቡትን ጥጆችና ያልደረሱትን ሳይጨምር የትልልቆቹ ከብቶች ቁጥር መቶ (ጥቤ Xibbe) እንዲሆን ተስማሙ እየተባለ ይነገራል፤" ሲሉ መልሰዋል (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ 26/2005)፡፡ የከብቶቹን ብዛት ለመወሰን መቶ (ጥቤ) እንደ እርከን ተገለጸ እንጂ መቼ እንደተስማሙ በትክክል የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

መቶ ቁጥር (ጥቤ) ለምን እንደገደብ ተወሰደ ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ አቶ አበበ ጊቻሞ ሲገልፁ "በሀድያ ከብቶችን ሲያረቡ አስር በማለት የሚጀመር ሲሆን አስር ሙሉ ተደርጎ

[1] አበጋዝ፡- በባህሉ የተለየ ስራ ለሰራ የሚሰጥ የክብር ማዕረግ ሹመት ስያሜ ነው፡፡ (አበጋዝ ዱባና ለሌሶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 26/2005)፡፡

ነው የሚታሰበው፣ አስር አስሮች ሲደርሱ መቶ ይሆናሉ፡፡ መቶ አስሮችም አንድ ሺህ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ሙሉ ተደርገው ስለሚታሰቡና ስለሚታመንባቸው ነው" ብለውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 23/2005 ዓ.ም) ፡፡

በድሮ ጊዜ ከብቶቹን በማሳየት እና እውቅና ለማግኘት የሚፈልግ አርቢ ጥሪ አድርጎላቸው ለሚመጡት ሰዎች ቡሎ (Bullo) የተሰኘ ከገብስ ዱቄትና ከቅቤ የሚዘጋጅ ለተከበረ እንግዳ፣ ለባል፣ ለሽማግሌዎች፣ ለሙሽሮች እና ለጠንካራ ጀግናች የሚቀርብ ባህላዊ ምግብ ይመግብ እንደ ነበር በሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ አበጋዝ ዮናስ ላምቦሬ ገልጸውልኛል፡፡ (ተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ፡ 26/2005 ዓ.ም)፡፡

ከላይ የሀድያ ብሔር ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት አጀማመር ምን እንደሚመስል ባጭሩ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ እገልጻለሁ፡፡

## 4.2 የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች

በሀድያ ብሔር ብዙ የቀንድ ከብቶችን ያረባ ባህሉ የሚፈቅደውን ህግና ደንብ አሟልቶ ሲገኝ የወገና ስርዓት ይፈፀምለታል፡፡ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ የተባሉ መረጃ አቀባይ የከብቶችን ቆጠራ ስርዓት ለማካሄድ መሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች እንዲህ ይላሉ፡፡

> የወገና ስርዓትን ለማዘጋጀትና ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው አንድ ከብት አርቢ ያረባቸው ከብቶች ቁጥር መቶ (ጥቤ) እና ከዚያ በላይ መሆን ነው፡፡ አንድ አርቢ ከብቶች አርብቶ ቁጥራቸው መቶና ከዚያ በላይ ስለሆኑለት የወገና ስርዓት አያዘጋጅም፡፡ በሀድያ ባህል ከብቶቹ መቶ ሞልተዋል የወገና ስርዓት አዘጋጃለሁ ብሎ ራሱ መጠየቅ የለበትም፣ ቢጠይቅም እንደውርደት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ 25/2005) ፡፡

በባህሉ የእኔ ከብቶች ይቆጠሩልኝ ወይም የወገና ስርዓት ይፈጸምልኝ ማለት ነውር ነው፡፡ ከጠየቀ ይናቃል፣ ይተቻል፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ በባህሉ ህግና ደንብ መሰረት ፈቅዶ ክብርና ዝናን፣ የተለየ ስያሜን ሲሰጥ፣ ሲያከብር ነው ተቀባይነት ያለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ገንዘብ ስላለው በባህሉ የተቀመጠውን ቁጥር ያህል ከብቶች ገዝቶ የወገና ስርዓት እንዲካሄድለት ማድረግ አይችልም፡፡ ይህም የሚያስንቅና የሚያዋርድ ነው፡፡ አቶ አበበ አቡኔ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚሉት "የዚህ ዓይነት የብልጣ ብልጥ ዘዴን ተጠቅሞ ስርዓቱ ቢደረግለት ወደፊት ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ጥሩ ነገር አይገጥመውም ተብሎ ስለሚታሰብ ደፍሮ የሚያደርግም የለም፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 24/2005 ዓ.ም) ፡፡ አንድ ሰው ገንዘብ ስላለው ስርዓቱ አይፈፀምለትም፡፡ ምናልባት እንኳን ስርዓቱን ፈጽሞ ቢገኝ ይረገማል፡፡ በዚህም የተነሳ የያዘው ሀብት ሁሉ እንደጉም ይበተናል፡፡ ለወደፊትም ዘሩ ትልቅ ደረጃ አይደርስም ተብሎ ይታመናል፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድም ክበር አይሰጠውም፡፡

ስለዚህም አንድ አርቢ ከብቶችን ሲያረባ የሚገጥሙትን ፈተናዎች ሁሉ አልፎ የከብቶቹ ቁጥር ለወገና ስርዓት መድረሳቸውን ቢያውቅም ዝም ይላል፡፡ ‹ከብቶችህ ለወገና ስርዓት ደርሰዋል አስቆጥር› ብሎ የሚቀሰቅስ አካል በባህሉ መሰረት አለ፡፡ እንደ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ አገላለጽ "አስቆጥር ብለው የሚቀሰቅሱት ከእሱ በፊት የወገና ስርዓትን አዘጋጅቶ የተፈጸመለት ወይም ከአባቱ ወንድም ልጆች ውስጥ ነው፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005) ፡፡

ቀድሞ የወገና ስርዓት የተካሄደለት አማካሪው ወይም የአጎት ልጅ እንዲያስታውሱ፣ እንዲቀሰቅሱ የተደረገበት ምክንያት በቅርበት ሆነው ከብቶቹን ሲያረባ የገጠሙትን ፈተናዎች፣ ልፋቱንና ውስጠ ምስጢሩን ያውቃሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከብቶችህ መቶ ደርሰዋል አስቆጥር፣ የወገና ስርዓት አዘጋጅ ብለው ሲቀሰቅሱት አርቢው "እሺ እናንተ ካላችሁ አግዙኝ" ይላል በማለት አበጋዝ ስዩም ደሪሎ ይገልጻሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

ቀስቃሾቹ የአርቢውን ፈቃደኝነት ካረጋገጡ በኋላ ለቤተሰብ መሪ ሽማግሌዎች እና በአካባቢ ላሉ ከዚህ በፊት መቶ ላስቆጠሩ ይናገራሉ፡፡ እንደ ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሬ ገለጻ "የተነገራቸው አበጋዞች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በመሆን ተወያይተው፣ የሚያጣሩበትን ቀን ወስነው አርቢውም እዲያውቅ ይደረግና ትክክለኛነቱን እንዲያጣሩ አራት ሰዎችን

ይልካሉ፡፡ እነኛም ሰዎች በባህሉ መሰረት ያጣራሉ፤" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ 24/2005) ፡፡

አጣሪዎቹ አበጋዞች የሆኑበት ምክንያት በሂደቱ ውስጥ እነሱ ያለፉበት በመሆናቸውና መሟላት ያለባቸውን ነገሮች ስለሚያውቁና እንዲሁም ማዕረግ ስላላቸው ነው፡፡ ወደ ሰውዬው ዘንድ በመሄድ በባህሉ ህግና ደንብ መሰረት የማጣራት ተግባራቸውን ይፈጽማሉ፡፡ ለማጣራት የሚጠቀሙባቸው ጥያቄዎች እና መሟላት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ የማጣራት ሂደቱን በተመለከተ በሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ ላይ በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ የሚከተሉት ሀሳቦች ተነስተዋል፡፡

አጣሪ አበጋዞቹ በያዙት ቀን ቀጠሮ መሰረት ወደ ሰውየው ቤት ይሄዳሉ፡፡ ሰውዬውም ተዘጋጅቶ ይጠብቃቸዋል፡፡ እንደደረሱ ሰውዬው ያረባቸው ከብቶች በበረት ውስጥ እንዳሉ ተዟዙረው ይመለከታሉ፡፡ ከዚያም ባስቆጣሪው ሰው ግቢ ጥላ የሆነ ስፍራ ላይ ተቀምጠው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀርቡለታል ፡፡ ሰውዬውም ምላሹን ይሰጣል ፡፡

አንደኛው ጥያቄ ፡- "ክብርና ዝና በመፈለግ ለመታወቅ ጓጉተህ ስርዓቱ እንዲካሄድልህ በማሰብ ምናልባት ራስህ ያላረባሀቸውን ከብቶች ቀላቅለህ ከሆነ በግልጽ ንገረን" ይሉታል፡፡ ሰውዬውም "አልቀላቀልኩም ለፍቼ ያረባኋቸው ናቸው" በማለት ይመልሳል፡፡ አጣሪዎቹም "ጥሩ ካልቀላቀልክ አንተን ያትርፍህ፣ ሀብትህ ካንተ አይራቅ፣ ቀላቅለህ ከሆነ ግን ንብረትህ ትቶህ ይሸሽ፣ ያጥፋህ" ይላሉ፡፡

ሁለተኛው ጥያቄ፡- "የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት እንዲካሄድልህ በማለት የቤተዘመድ ከብቶች ቀላቅለሃል?" ይሉታል፡፡ እሱም "በፍጹም አልቀላቀልኩም" ሲል ይመልሳል፡፡ ከዛም ወተት ከቤቱ ያስመጡና ያቀምሱታል፡፡ ወተት የመቅመሱ ትርጓሜ ምናልባት ችግር ካለበት እንዲረክስለት ወይም ችግር እንዳይፈጠርበት በማለት ነው፡፡

ሶስተኛው ጥያቄ፡- "ባሳየኸን ከብቶች ውስጥ ምናልባት በሌብነት የመጣ ከብት ተቀላቅሎብህ ይሆን?" ሲሉት እሱም "በፍጹም የለም" ሲል ይመልሳል፡፡ "የለም ካልክ በዚህ ጦር መሬት ውጋ" ይሉታል፡፡ እሱም እርግጠኛ ከሆነ ይወጋል፡፡ መሬት ማስወጋቱ መሀላ

ሲሆን ዋሽተህ ከሆነ በጦር የወጋሃት መሬት ትዋጥህ፣ እድሜህ አጭር ይሁን እንደማለት ነው፡፡

አራተኛው ጥያቄ፡- "ከብቶችህን ባረባህባቸው ጊዜያት ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ስትዘዋወር አውቀህ የሰው ሳር አብልተህ አሳዝነህ ከሆነ ንገረን" ይሉታል፡፡ ሰውዬውም "እውቄ የዚህ ዓይነት ተግባር አልፈጸምኩም" ሲል ይመልሳል፡፡ ጠያቂዎቹም ለምለም ሳር ከዛው ከግቢው ውስጥ ነጭተው ይሰጡታል፡፡ የሳሩ ትርጓሜም እንደዚህ ለምለም ሳር ከቤትህ እርጥብ (የወተት ዘር) አይጥፋ እንደማለት ነው፡፡

አጣሪዎቹ ጥያቄ ሲጠይቁትና ሲመልስ ምናልባት ቢዋሽስ የሚል ጥያቄ በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ላይ አያይዤ አንስቼ ነበር፡፡ ተወያዮቹም "በሀድያ ባህል ደንብ ለዚህ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ጉዳይ ቢሆንም በተለይ በታወቁና በተከበሩ ሽማግሌዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይሰጣል፡፡ ከብት አርቢውም ትክክለኛ መልስ ካልሰጠ እረገማለሁ በማለት ይፈራል፡፡ ከተረገመ ወደፊት በጤናው፣ በቤተሰቡና በሀብቱ ጥሩ ነገር አይገጥመውም ተብሎ ስለሚታመን አይዋሽም፣" ሲሉ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በዋናነት ከብቶቹን በትክክል እራሱ አርብቶ እንዳሟላ ለማረጋገጥ የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ የወገና ስርዓትን ለማካሄድ ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪም አጣሪዎቹ የከብቶቹን ቁጥርና የአረባብ ሂደቱን ካጣሩ በኋላ በተያያዥነት ከሚያዩዋቸው ውስጥ አርቢው የሚኖርበት ቤት ይዘት፣ የግቢው ሁኔታ፣ በምግብ ቤተሰቡን ማጥገቡ፣ እሱም ሆነ ባለቤቱ የሚቀመጡባቸው በቅሎና ፈረስ እንዳለው፣ ፍየል[2] ማርባቱ፣ የሚተኛበት ነት (ሂርፊና Hirfana)[3]፣ ከከብት እርባታው ጎን ለጎን በእርሻ ስራ ላይ ያለው

---

[2] ፍየል፡- አጣሪዎቹ ፍየል ማርባቱን የሚያዩት የግድ ሆኖ አይደለም፡፡ ምናልባት ከብቶቹን በሚያረባበት ጊዜ ለሚገጥሙት አንዳንድ ችግሮች ማቃለያ እንዲሆነው ከሚያረባቸው ፍየሎች ውስጥ እየሸጠ ክፍተቱን መሙላቱን ለማረጋገጥ ነው ፡፡ ምክንያቱም ፍየል ቶሎ ቶሎ ስለምትወልድ ነው፡፡ (ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 24/2005 ዓ.ም)

[3] ሂርፊና፡- ሂርፊና ትልቅ የከብት ቆዳ በባለሙያ ለስልሶ ለመተኛነት የሚያገለግል ነው፡፡ (አቶ አበበ አቡኔ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 5/2005 ዓ.ም) ፡፡

እንቅስቃሴና የጓሮ አያያዙ ይታያል፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም)፡፡

እንዲሁም ከብቶቹን ባረባባቸው ጊዜያት ከብቶቹን የጠበቀበት የአርጩሜ ቁራጭ ስብስብ ይታያል፡፡ ይህ የሚታየው በትክክል ከብቶቹን እራሱ ለፍቶ ጠብቆ እንዳረባቸው ለመረዳት ያስችላል በማለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ከብቶቹን ሲያረባ በረት (ጋድራ Gaadira) የሰራባቸው ቦታዎችና የሚታለቡ ላሞች ብዛት ይታያል፡፡ እነዚህም የሚታዩበት ምክንያት በትክክል ለፍቶ ማርባቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እንዲሁም ከብቶቹን የት የት አካባቢ እየተዘዋወረ እንዳረባቸው ይጠይቁታል፡፡ ይህም ምን ያህል መልፋቱን መቸገሩን ለማጣራት ነው፡፡

በተጨማሪም ሰውዬውም ሆነ ሚስቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው መግባባት፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ፣ አስተዋይነት፣ ሀቀኝነት የሰውን ንብረት አለመፈለጋቸውና በባህሪያቸው የተረጋጉ መሆናቸው ወዘተ የአካባቢውን ሰዎች በመጠየቅ ያጣራሉ፡፡

አጣሪዎቹ ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን መሰረታዊ ነጥቦች ግለሰቡ ማሟላቱን ሲያረጋግጡ የቆጠራ ስርዓት ማዘጋጀት እንደሚችል ይገልጹለታል፡፡ እሱም የይሁንታ ፈቃዱን ተቀብሎ ስርዓቱን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማዘጋጀት ይጀምራል፡፡

በሀድያ ባህል መቶ ከብቶችን አርብቶ ካስቆጠረ፣ የወገና ስርዓት ካደረገ የሚሰጠው ስያሜ አለ፡፡ ይህም ጥባሞ[4]፣ አበጋዝ የተሰኘ የክብር ሹመት ስያሜ ይሰጠዋል፡፡ አበጋዝ ስለሚባለው ባህላዊ የማዕረግ ስያሜ አበጋዝ ዱባን ለሌሶ የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲገልጹ፡-

---

[4] ጥባሞ ፡- በሀድይኛ ቋንቋ ‹‹ጥቤ›› መቶ ማለት ሲሆን ‹‹ጥባሞ›› ሲሆን ደግሞ በባህሉ መሰረት መቶና ከዚያ በላይ ከብቶችን ያስቆጠረ ባለ ብዙ ከብት፣ ሀብታም፣ የተለየና የተከበረ፣ በጥንካሬው የታወቀ፣ ብዙ ፈተናዎችን ያለፈና ለክብር የበቃ ማለት ነው፡፡ (አበጋዝ ስዩም ደሪሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 25/2005 )፡፡

*አበጋዝ የሚለው የክብር ሹመት ስያሜ ድሮ ድሮ ለኀበዝ ጦረኛ ወይም ጀግና የሚሰጥ ስያሜ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተስማራበት ሁሉ በባህሉ የተለየ ስራን የሰራ በተለይ ደግሞ ከብቶችን አርብቶ መቶ ላስቆጠረ ይህ ስያሜ ይሰጣል፡፡ የጦር መሪው በረሃ ለበረሃ ተንከራቶ ብዙ ችግርን እንደሚያሸንፍ ሁሉ የከብት አርቢውም እንደዚሁ ከብቶችን ይዞ በመንከራተቱ መሰዋዕትነትን ከፍሎ ለቁጠራ ስለደረሰ አላማውን ያሳካ ጀግና የተለየና የታወቀ በመሆኑ ይህ ባህላዊ የክብር ሹመት ስያሜ ይሰጠዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣* 25/2005) ፡፡

ይህ ስያሜ የተሰጠው ሰው "ሀድያ በሚያደርገው በማንኛውም ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ምርቃት (ቡራኬ) በማድረግ ስብሰባ ሊከፍት ይችላል፡፡ ግጭት ሲፈጠር ይፈታል፣ ያስታርቃል፡፡ በስህተትም ይሁን እያወቀ በሰው ሀብትና ንብረት ላይ እጁን አይከትም፣ አይወስድም፡፡ የተከበረ የተለየ ሰው በመሆኑ ሚስቱም ለእሱ አጋዥ በመሆኗ "ጊፍቱ" የተሰኘ የክብር ስያሜ ይሰጣታል፡፡ የተከበረ ሰው ሚስት፣ የተለየች የታወቀች መሆኗን ለመግለጽ ነው፣" ሲሉ አቶ እሸቱ ጡሚሶ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 30/2005) ፡፡

ከላይ የተገለጸውን ማዕረግ ለማግኘት መቶ ከብቶችን ለማርባት የሚደረገው ጥረትን ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሬ የተባሉት ሲገልጹ፡-

*... ከብቶችን በማርባት ትልቅ ደረጃ ለመድረስ የሚደረገው ጥረት ሲጀመር እስከ አስር ከብቶች በማርባት እያለ በሂደት ሃያ ከብቶች ያረባ ፎርገሳ* (Foorgassa) *አነስተኛ ከእጅ ወደ አፍ፣ እስከ ሰማንያ ከብቶችን ያረባ ጉበንታ* (Gubaanataa) *መካከለኛ ሀብታም ሲሆን፣ መቶና ከዚያ በላይ ያረባ ጥባሞ* (Xibbaamo) *ከፍተኛ ሀብታም እንደማለት ሲሆን ሌላኛውና የመጨረሻው ሺህ ኩማሞ* (Kumaamo) *በከብት የማርባት ሂደት የመጨረሻው ጣሪያ ላይ የደረሰ ነው፡፡ ከብቶችን አርብቶ መቶና ከዚያ በላይ አድርሶ የወገና ስርዓት በማካሄድ ጥባሞ መባል፣ በሀብት መታወቅ፣ የተለየ ክብርና ባህላዊ ስያሜ ማግኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሀብረተሰቡ ዘንድ የተለየ ስፍራ እንደሚያሰጠው፣ ማህበራዊ ደረጃው እንደሚሻሻል ይገልፃሉ፡፡* (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 24/2005 ዓ.ም)፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ አንድ ሴት ከብቶች አርብታ መሟላት ያለባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች አሟልታ ያስቆጠረች ትኖር ይሆን? በማለት በሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ ከተማ በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ አንስቼ ነበር፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ተሳታፊ የሆኑት አቶ አበበ ጊቻሞ የተባሉት ሲገልጹ፡-

*ሴት ለብቻዋ አርብታ አስቆጥራ አታውቅም፡፡ ባሏ አርብቶ ሲያስቆጥር እሷም አለችበት፣ ለዚህም ነው ለሷም የማዕረግ ስያሜ የሚሰጣት፡፡ ባልየውም እሷ*

*ሳታግዘው ብቻውን እርብቶ ሲያስቆጥር ይቸገራል፡፡ ሴት ግን ለብቻዋ እርብታ ያስቆጠረች የለችም፡፡ ኑሮዋን መምራት የምትጀምረው ንብረት የምታፈራው ባል አግብታ ነው፡፡ ባልየው ከብቶቹን ለማርባት ከቦታ ቦታ ሲዘዋር እሷ የቤት ውስጥ ተግባራትን ታከናውናለች፤ ብለዋል፡፡* (ታህሳስ፡ 26/2005) ፡፡

## 4.3 የቆጠራው ስርዓት ክዋኔ

በሀድያ ብሔር ባህልና ደንብ መሰረት የከብቶች ቆጠራ ስርዓት የራሱ ክዋኔ አለው፡፡ የክዋኔውን ሂደት በትክክል ለመግለጽ የቆጠራው ቅደመ ዝግጅት፣ በዋዜማው የሚደረጉ ክዋኔዎች፣ ወደ ወንዝ የመሄድ ስርዓት ክዋኔ፣ ከወንዝ መልስ የሚደረጉ ስርዓት ክዋኔዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.3.1 የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት

የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ስርዓት ለማዘጋጀትና ብሎም ለመፈፀም በባህሉ ደንብ መሰረት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በ4.2 ላይ እንደተገለጸው መሟላታቸው ተረጋግጦ በአጣሪዎች የይሁንታ ፈቃድ ማግኘት የግድ ነው፡፡ ስርዓቱን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማዘጋጀት ሰፋ ያለ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ዝግጅቱ የሚወስደውን ጊዜ አስመልክቶ መረጃ ያቀበሉኝ አቶ አበበ አቡኔ "ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት" እንደሚወስድ ይጠቅሳሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፡ 24/2005 ዓ.ም) ፡፡ ይህን ያህል ጊዜ የሚወስደው በስርዓቱ ላይ የሚገኙት ሰዎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ስለሚሆኑና ዝግጅቱም ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሙሉ ለማሟላትና ለማዘጋጀት ነው፡፡

ለስርዓቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማዘጋጀት የሴቱን በኩል ሚስቱ ከቅርብ ቤት ዘመዶቿ እና ጎረቤቶቿ ጋር በመሆን የወንዱን በኩል ደግሞ ሰውዬው ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ ከዝግጅቱ መጀመሪያ ጊዜ አንስቶ እስከ ስርዓቱ ማሳረጊያ ዕለት ድረስ አስቆጣሪው ለብቻው እንዲንቀሳቀስ አይመከርም፡፡ አቶ አበበ ጊቻሞ ምክንያቱን ሲገልጹ "(መሀራንቾ Mahaarancho) ክብር የሚገባው በመሆኑ፤ ክብር ከመስጠትና ጥንቃቄ ከማድረግ አንፃር ነው፤" ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም)፡፡ በአቅራቢያው ያሉ ሰዎች ለወገና ስርዓት ዝግጅት ማድረግ ላይ ነው የሚለውን ወሬ ሲሰሙ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ማክበር ይጀምራሉ፡፡ ምክንያቱም ከብቶቹን ሲያረባ በርካታ ፈተናዎችን በማለፍ ለትልቅ

ክብርና ዝና በመድረሱ ነው፡፡ ጥንቃቄ የሚደረግለት ለፍቶ ለደረሰበት ባህላዊ ሹመት፣ ክብርና ዝና ዘመድ አዝማድ ወገኖች ባሉበት ስርዓቱ ተፈጽሞ እስኪፀድቅለት ድረስ አንዳች ችግር እንዳይገጥመው በማለት ነው፡፡ ስለዚህም ለብቻው ወደ ወንዝ፣ ጫካና እራቅ ያሉ ቦታዎች አይሄድም፡፡ ብቻውን ከሆነ የሚተናኮለው ምቀኛ አይጠፋም ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ስርዓቱ ተፈፅሞ በይፋ ማዕረጉ ፀድቆ እስከሚታወቅ ድረስ አብሮት የሚንቀሳቀስ መካሪ ይኖረዋል፡፡

ከዝግጅቱ መካከል "በቂ የእንግዳ መቀበያ ቤት ማዘጋጀት፣ ቅቤ በእንስራ ማጠራቀም፣ አዲስ በረት ለከብቶቹ መስራት፣ የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮችን (ዳቦ፣ እንጀራ፣ ጠጅና ብርዝ) ማዘጋጀት፣ ማር በእንስራ፣ ለእርድ የሚሆኑ በሬዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት፤" መሆናቸውን ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሬ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ታህሳስ፣ 24/2005 ዓ.ም) ፡፡

በቂ የእንግዶች ማረፊያ ቦታ ማዘጋጀት አንዱ ጉዳይ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ሰውዬው ያሉት ቤቶች ለሚመጡት ታዳሚዎች የማይበቁ ከሆኑ አዲስ የሳር ቤት ይሰራል ወይም ድንኳኖች ይተከላል፡፡ ካልሆነም እልፍኝ ያላቸው ጎረቤቶቹን በትብብር ጠይቆ ያዘጋጃል:: ይህን ያህል ብዛት ያለው ማረፊያ የሚዘጋጅበት ምክንያት የሚመጡት እንግዶች ቤተ ዘመዶች (የሰውዬውና የሚስቱ) በየወገናቸው በቡድን ቡድን በመሆን ሲሆን፤ ከሁለት እስከ ሶስት ቀን ስለሚቆዩ ለእያንዳዱ ወገን አንድ አንድ ማረፊያ ስለሚሰጥ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ቤት ተለይቶ ስርዓቱን ለሚፈጽሙት ጥባሞች፣ አበጋዞች ያዘጋጃል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ጊዜ ምልከታ ባደረኩባቸው አምስት ቦታዎች አበጋዞቹ ያረፉበት ቤት ለብቻ የተለየ ሲሆን፤ ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዳመጣጣቸው በቡድን በቡድን በመሆን በተዘጋጁላቸው ድንኳኖች እና ቤቶች ሆነው ተመልክቻለሁ፡፡ ከተመለከትኳቸው አምስት ቦታዎች ላይ የተተከሉት ድንኳኖች አነስተኛው አራት ከፍተኛው ስምንት ናቸው፡፡ ስምንት ድንኳኖች ተተክለው ያየሁት ታህሳስ 20/2005 ዓ.ም በሶሮ ወረዳ አምቤ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ደስታ ጎቦሮ የተዘጋጀ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ድንኳኖቹ ሰፋ ሰፋ ያሉ ሲሆኑ፤ በሰውዬው ቤት አካባቢና በአቅራቢው ባሉ ጎረቤቶች ቤት አካባቢ አለፍ አለፍ ብለው ተተክለዋል፡፡ አስቆጣሪው ሰውዬ ሶስት ቤት ያለው ሲሆን በአንዱ ቤት አበጋዞቹ ሲገለገሉበት ተመልክቻለሁ፡፡

ለስርዓቱ መከወኛ ከሚዘጋጁት ዝግጅቶች ውስጥ ባህላዊ ምግቦች እና መጠጦች አሉበት፡፡ ይህንን አስመልክተው አቶ አበበ ጊቻሞ "በስርዓቱ ላይ የሚቀርቡት መብልና መጠጦች የሚዘጋጁት ካልከረሙ የእህል ዓይነቶች ነው፡፡ የከረሙ የእህል ዓይነቶች ከሆኑ ነቀዝ ይበላቸዋል፡፡ ነቀዝ ከበላቸው ተቀባይነት የላቸውም፤" ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡


ያልከረሙ ወይም አዲስ የእህል አይነቶች እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ቢዘሩ ይበቅላሉ፤ ሲበሉ ለሰውነት ኃይል ይሰጣሉ፡፡ የከረሙ የእህል ዓይነቶች ከሆኑ ነቀዝ ይበላቸዋል፡፡ ነቀዝ ከበላቸው ቢዘሩ አይበቅሉም፡፡ ቢበሉም ለሰውነት የሚገባውን ጥቅም አይሰጡም፤ ሀይል የላቸውም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በተጨማሪም አርቢው ሰውዬ ሀይል እንዳለው፡ የእሱ ተግባር ለዘር ዘሩ ይተላለፍ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ስለዚህም በስርዓቱ ላይ የከረሙ የእህል ዓይነቶችን መጠቀም አይቻልም፡፡ አስቆጣሪውም ጥሩ ነገር አይገጥመውም ተብሎም ይታመናል፡፡

በስርዓቱ ላይ የሚታረዱ በሬዎችን በተመለከተ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ "ሁሉም በሬዎች ያልተኮላሹ መሆን አለባቸው፡፡ በወገና ስርዓት የተኮላሹ በሬዎች እንዲታረዱ ባህሉ አይፈቅድም፤" ሲሉ ገልጸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም)፡፡ የተኮላሹ በሬዎች እዲታረዱ የማይፈቀደው በመኮላሸታቸው ዘርን ሊተኩ ስለማይችሉ ነው፡፡ ስለዚህም ያልተኮላሹ በሬዎች የሚታረዱበት ምክንያት ከመታረዳቸው በፊት ዘርን ይተኩ ስለነበር ነው፡፡ አንድም ያላረጁ ስለሆኑ ትኩስ ኃይል አላቸው በማለት ነው፡፡ አስቆጣሪውም በርካታ ፈተናዎችን ተጋፍጦ አሸንፎ ለዚህ ክብር በመብቃቱ ኃይል እንዳለው ለማመልከት ነው፡፡ የክብት ዘር ከሰውዬው ቤት እንዳይጠፋ፤ በዘሩ እንዲቀጥል በማሰብ ነው፡፡ በቆጠራ ስርዓት ድፍን ጥቁር በሬ አይታረድም፡፡ ጥቁር በሬ የማይታረድበት ምክንያት "የጥሩ ነገር መገለጫ ተደርጎ ስለማይወሰድ ነው፡፡ ጥቁር በሬ ከታረደ አስቆጣሪው ሰውዬ ጥሩ ነገር አይገጥመውም ተብሎ ይታመናል፡፡" (አበጋዝ ሸጎ ኑራሞ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 23/2005) ፡፡

በዝግጅቱ ወቅት ስርዓቱ ከመፈጸሙ ከሶስት ወር በፊት አዲስ በረት ይሰራል፡፡ አበጋዝ ጊንታሞ ወልገዮ "አዲስ በረት የሚሰራው ሰውዬው በማስቆጠሩ ወደ አዲስ ማህበራዊ ደረጃ

ይሸጋገራል፡፡ ከብቶቹም ወደ አዲስ በረት የሚገቡትም ለዚህ ነው" ሲሉ ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

አዲሱን በረት የሚሰሩት የአስቆጣሪው ወንድም ልጆች፣ የቅርብ ቤተዘመዶች እና ጎረቤቶች ናቸው፡፡ በረቱ የሚሰራው ከሰውዬው መኖሪያ ቤት አካባቢ ሲሆን ሰፊ ነው፡፡ አሰራሩም በአንዳድ ቦታዎች እዚያው በረቱ ውስጥ ለጥጆች የተወሰነ ቦታ ከለል ሲያደርጉ፤ አንዳንዱ ጋ ደግሞ ከበረቱ ጋር በማገናኘት ለጥጆች አነስተኛ ጎጆ ቤት ይሰራሉ፡፡ ይህንንም በመስክ ቆይታዬ ወቅት ስርዓቱ በተከናወኑባቸው ቦታዎች ተመልክቻለሁ፡፡ ለጥጆች አነስተኛ ጎጆ ቤት ከበረቱ ጋር ተሰርቶ ያየሁት በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ ለአቶ ላምባሞ ሚጦሬ በተዘጋጀው ስርዓት ላይ ነው፡፡ ለጥጆች የሚሆን ቦታ በበረቱ ውስጥ ተከልሎ ያየሁት ደግሞ ሶሮ ወረዳ ገባባ ለንጌ፣ ኦምቤ ለንጌ እና ቡርይ ለንጌ ቀበሌዎች፤ እንዲሁም በጎንቦራ ኦሌ ቀበሌ በተካሄዱ ስርዓቶች ላይ መመልከት ችያለሁ፡፡



ፎቶ 1.በሶሮ ወረዳ ኦምቤ ለንጌ ቀበሌ ለጥጆች ማደሪያ ውስጡ ከለል ተደርጎ የተሰራ በረት፣



ፎቶ2. በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ ከበረቱ ጋር ተያይዞ ለጥጆች ማደሪያ የተሰራ በረት፣

አበጋዝ ጊንታሞ ወልገኖ አያይዘው ሲገልጹ "በረቱን የሚሰሩት ሰዎች ሰርተው ሲጨርሱ ከሰውዬው ከብቶቹ መሀል አንድ የደረሰ ወይፈን ከአንድ እንስራ ቅቤ ጋር ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ተጨምሮ ይቀርብላቸዋል፡፡ እነሱም የተሰጣቸውን ወይፈን አርደው በልተው ጭፈራ ይጀምራሉ" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡ በረቱን ለሰሩት ሰዎች ይህ ስጦታ የተሰጣቸው ደስታን ለመግለጽና ዋዜማውን ለማብሰር ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ለስርዓቱ የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ እንደ ባህሉ ስርዓት ተዘጋጅተው ካለቁ ስርዓቱ የሚካሄድበት ቀን ይወሰናል፡፡ ስርዓቱ የሚካሄድበትን ቀን በተመለከተ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ከተጠቀሱት ወሮች ውስጥ ህዳር፣ ታህሳስና ጥር በብዛት ሲፈለጉ ሚያዝያ ወርም አልፎ አልፎ ይመረጣል፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ፣ 26/2005 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ የተጠቀሱ ወሮች የሚመረጡበት ምክንያት በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ እንደተገለፀው ከህዳር ጀምሮ እስከ ጥር አዝመራ የሚሰበሰብበት ወቅት በመሆኑ፣ ለዝግጅቱ የሚሆኑ አዲስ የእህል አይነቶች እንደልብ ስለሚገኙና የጥጋብ ወሮች በመሆናቸው ነው፡፡ የሚያዝያ ወር የተመረጠው በጋው አልፎ ዝናብ ይዞ ስለሚመጣ እርጥበት ልምላሜ የሚታይበት በመሆኑ ነው፡፡

ስርዓቱን ለመፈፀም ከቀኖች ውስጥ በብዛት የሚመረጠው እሁድ ነው፡፡ እሁድ የተመረጠበት ምክንያት ከቀኖች ሁሉ ሙሉ ተደርጎ የሚወሰድና ተቀባይነት አለው ተብሎ በባህሉ ስለሚታሰብ ነው፡፡[5] በተጨማሪም የተጠሩት እንግዶች በስርዓቱ ላይ እንዲገኙ አመቺ ይሆናል በማለት ነው፡፡

ስርዓቱ የሚፈጸምበት ወርና ቀን ከታወቀ በኋላ በስርዓቱ ላይ ለሚገኙት ሰዎች ጥሪ ይተላለፋል፡፡ ጥሪው የሚተላለፈው አበጋዝ ስዩም ደሪሎ እንደ ገለጹት "ስርዓቱን ለሚፈጽሙና ለሚያፀድቁት ጥባሞች ወይም አበጋዞች፣ ለጎሳ መሪ፣ ለቤተሰብ መሪ፣ ለቤተዘመድ (ለሰውዬው ወገኖች፣ ለሚስት ወገኖች) ፡ ልጆች ድረው ከሆነ (ለወንድ ልጆች ሚስት ወገኖች፣ ለሴት ልጆች ባል ወገኖች) ፡ በአካባቢ ላሉ ሰዎችና ሌሎች ወዳጆቻቸው ናቸው፤" ብለዋል፡፡ (ቃል መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

---

[5] ስርዓቱ የሚከወንበትን ቀን በተመለከተ ሲባል የሰማሁት አፈ ታሪክ በማለት አቶ አበበ ጊቻሞ ሲገልጹ "በሀድያ የሳምንቱ ቀናት ከሁኔታዎች ጋር በማገናኘት የሚሰጣቸው ስያሜ አለ፡፡ ሰኞ የጦርነት ቀን፣ ማክሰኞ የገበያ ቀን፣ እሮብ ደረቅ ፣ ሐሙስ የገበያ ቀን፣ አርብ ደረቅ፣ ቅዳሜ ማረፊያ እና እሁድ ሙሉ የቀኖች ሁሉ አባት ይባላል፤" ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 5/2005 ዓ.ም) ፡፡

ለሚጠሩት ሰዎች ከየወገን ወገናቸው አንድ አንድ ሰው ተመርጦ ጥሪውን እንዲያደርስ ያደርጋሉ፡፡ ጥሪው የሚተላለፈው አንድ ወር ያህል ሲቀር ነው፡፡ ጥሪው የደረሳቸው ወገኖችም ወደ ተጠሩበት ለመሄድ በወገናቸው በመነጋገር በባህሉ መሰረት የሚያመጧቸው ነገሮች ላይ ይወስኑና የስርዓቱን ቀን ይጠብቃሉ፡፡ ምን ምን ይዘው እንደሚመጡ በሚቀጥለው ንዑስ ክፍል ተጠቅሷል፡፡

### 4.3.2 በዋዜማው የሚደረጉ ክዋኔዎች

በዋዜማው ዕለት በስርዓቱ ላይ በመገኘት የሚሳተፉ፣ ስርዓቱን የሚፈጽሙትና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በሙሉ ቤተ ዘመዶች በቡድን በቡድን በመሆን ወደ አስቆጣሪው ቤት ይመጣሉ፡፡ ሲመጡ ሰውዬው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ከፈተና አልፎ ለዚህ ትልቅ ክብርና ዝና በመድረሱ ያላቸውን ደስታ ለመግለጽ ያልተኮላሸ ትልቅ በሬ፣ ማር በእንስራ፣ እህል በበቅሎ ጭነው፣ ድፎ ዳቦ፣ የአናት ቅቤ እና ወጪታ (Woceta)[6] እንዲሁም አልፎ አልፎም ለሰውዬው ፈረስ ከነ ኮርቻው በስጦታነት ይዘው፤ ጡሩንባ በመንፋት እልል እያሉ፣ እየጨፈሩ ይመጣሉ፡፡ በመስክ ቆይታዬ ምልከታ ባደረኩበት በጎንቦራ ወረዳ አዴእና ቀበሌ በአቶ ላምባሞ ሚጦሬ በተዘጋጀው ስርዓት ላይ ቤተ ዘመዶች አስራ ሁለት በሬ ይዘው እንደመጡ እንዲሁም በሶሮ ወረዳ ኦምቤ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ደስታ ጎቦሮ በተዘጋጀ ስርዓት ላይ ፈረስ ከነ ኮርቻው ጭምር በስጦታነት ይዘው እንደመጡ ተመልክቻለሁ፡፡

---

[6] ወጪታ (Woceta) ፡- ባህላዊ ቁስ ሲሆን የእንስራ አይነት ቅርፅ ያለው ሆኖ መጠኑ አነስተኛ ነው፡፡ ከሸክላ ተሰርቶ ዙሪያው በዛጎል ይሸፈናል፡፡ ማንጠልጠያ መያዣ ከቆዳ ይሰራለታል፡፡ በዚህ ስርዓት ላይም የተነጠረ ቂቤ ይቀርብበታል፡፡ (አቶ አበበ አቡኑ፣ ቃለመጠይቅ ጥር 5/2005 )፡፡

ተሳታፊዎቹ እሰውዬው ግቢ በር ሲደርሱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በእልልታ በጭብጨባ ተቀብለዋቸዋል፡፡ እስቆጣሪውም ከነሚስቱ በመሆን ከብት ሲጠብቅ የሚጠቀምባቸው ቁሶች ጦር (ሽልቴ)[7] እና ወተት ማለቢያ፣ መጠጫ (ኦቾ Ochcho)[8] በመያዝ፤ ሚስቱም ወጪታ ይዛ ጎን ለጎን ቆመው የሚመጡትን እንግዶች ተቀብለዋል፡፡ ይህንንም በመስክ ቆይታዬ በጎምቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ በአቶ ላምባሞ ሚጦሬ በተዘጋጀ ስርዓት ላይ መመልከት ችያለሁ፡፡



ፎቶ 3. በጎንቦራ ወረዳ ኦሌ ቀበሌ ቤተ ዘመዶች ለደስታ መግለጫ በሬ ይዘው ሲመጡ፤



ፎቶ 4. በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ ቤተ ዘመዶች ወጪታና ዳቦ ይዘው መጥተው፤

ከሚጨፍሯቸው ጭፈራዎች ውስጥ ለማሳያነት የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

---

[7] ጦር፡- እንደ አቶ አበበ አቡኔ አገላለጽ "በሀድያ ባህል የተለያዩ የጦር አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ሽልቴ (Shallittei) ረዥሙ ጆሮ የሌለው ጦር፣ ለም መጫሞ (Lammachchaamo) ሁለት ጆሮ ያለውና ጤንቆ (Xenqo'o ) ትንሽ ጦር ናቸው። እነዚህ የጦር ዓይነቶችም የሚይዛቸውን ሰው ዕድሜ፣ ማንነቱን የሚጠቁሙ ናቸው" ብለውኛል። (ቃለ መጠይቅ፤ ጥር 5/2005 ዓ.ም) ፡፡

[8] ኦቾ (Ochcho) ፡- አቶ አበበ አቡኔ እንደነገሩኝ ጮጮ (ኦቾ) ከባህላዊ ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው ፡፡ የሚሰራውም ከስንደዶ ሲሆን ማንጠልጠያው ቆዳ ነው፡፡ የማሰሮ አይነት ቅርፅ ያለው ነው፡፡ ውስጡም ትኩስ ደም በማድረግ ቀዳዳዎቹ እንዲደፈኑ ይደርጋል፡፡ ከዚያም የተለያዩ ሽታንት ባላቸው እንጨቶች ጭስ ይታጠናል፡፡ አገልግሎቱ በከብት ጥበቃ ወቅት ወተት የሚጠጣበት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 4/2005) ፡፡

Xibbukko Xibbukko Hashshu Xibbukko

Xibbukko Xibbukko Hashshu Xibbukko

ባለ መቶ ሆነ እሰይ ቂጥሩን ሞላ፣

ባለ መቶ ሆነ እሰይ ቂጥሩን ሞላ፡፡

እያሉ በመጨፈር አርቢው ለወገና ስርዓት በመድረሱ ደስታቸውን በመግለጽ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከመጡ በኋላ በአስቆጣሪው ሰውዬ ግቢ ይገባሉ፡፡ በመቀጠል የሚተገበረው ተግባር በየወገኑ ለደስታ መግለጫነት ተነድተው የመጡት በሬዎች ማረድ ነው፡፡ እርዱ የሚፈጸመው የየወገኑ ተወካይ ሽማግሌዎች አስቆጣሪውን ና ያመጣነውን በሬ መርቀህ ተቀበለን በማለት ጠርተው ነው፡፡ እሱም እሺ ይላል፤ ከሽማግሌዎቹ ጋር በመሆን ወደ አመጧቸውና በግቢው ውስጥ ታስረው ወደ ቆሙት በሬዎች ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም ተወካዮቹ ሽማግሌዎች ይመርቁታል፡፡ ምርቃቱም "አክብረንሃል ተከበር፤ ይህ ክብር ለዘር ዘርህ ይድረስ" በማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎቹ ሰዎች "አሜን ይሙላ" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም አንተም መርቀህ ተቀበለን ይላሉ፡፡ ሰውዬውም "እንዳከበራችሁኝ ክበሩ፣ እግዚአብሔር ይስጣችሁ" በማለት ይመርቃል፡፡ ከዚያም የሰውዬውን እጅ ስመው በሬዎቹን ያርዳሉ፡፡ እጅ የመሳማቸው ትርጓሜም አንድም ምርቃትህ፣ በረከትህ ይድረሰን ሲሆን፣ አንድም ማክበራቸውን የበላይ ማድረጋቸውን ለመግለጽ ነው፡፡



ፎቶ 5. ቤተዘመዶች ለደስታ መግለጫ ያመጡትን ስጦታ አስቆጣሪው አቶ ላምባሞ ሚጦሬ መርቀው ሲቀበሏቸው፣ ተወካይ ሽማግሌዎቹም እጃቸውን በመሳም ላይ፣

ቤተዘመዶች ካረዷቸው በሬዎች ስጋ ላይ ከሻኛው፣ ከፍርንባው እና ከጎድኑ የተወሰነ ቆርጠው ሰውዬው ቤት ያስገባሉ፡፡ ቀሪውን ስጋ ሁሉ ለማረፊያነት ወደተሰጣቸው ድንኳን ወይም ቤት ይወስዳሉ፡፡ ምግብም በማዘጋጀት እራሳቸውን በራሳቸው ያስተናግዳሉ፡፡ ይህንንም በሶሮ ወረዳ ገባባ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ሀንቂቦ ጃቴቦ በተዘጋጀ ስርዓት ላይ ተመልክቻለሁ፡፡ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ እንደሚሉት "እራሳቸው በራሳቸው እንዲያስተናግዱ የተደረገበት ምክንያት የሚመጡት ሰዎች በርካታ ስለሆኑ ለማስተናገድ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው፡፡ ከሰውዬው የሚፈልጉት ማጣፈጫ ቅመሞችን፣ ቅቤ፣ እንጀራና መጠጦችን ነው፤" ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005 ዓ.ም)

ከዚህ ሁሉ ሂደት ጎን ለጎን ደግሞ ስርዓቱን በመፈፀም የሚያረጋግጡት ጥባሞች፣ አበጋዞች ይመጣሉ፡፡ እነኚህ ሰዎች ለሰውዬው ለክብሩ መገለጫ ይዘው የሚመጡት ነገር እንደሌለ በምልከታዬ ወቅት በጎንቦራ ወረዳ አሌ ቀበሌ በአቶ እየቆ ለጩቦ ቆጠራ ጊዜ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ እንደመጡም አስተናጋጆች ለእነሱ ተብሎ ለብቻ ወደተዘጋጀላቸው ቤት ወስደው እንዲያርፉ ያደርጓቸዋል፡፡



ፎቶ 6. አበጋዞቹ በተዘጋጀላቸው ቤት ተቀምጠው፣

አበጋዞቹ ለምን ለብቻቸው ተለይተው አንድ ቤት ሆኑ? ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ገራድ ኤርቃሎ ሚከሬ ሲገልጹልኝ፡-

*. . . ለብቻ አንድ ቤት ከሌሎቹ ሰዎች ተለይተው የተቀመጡት ማዕረግ ስላለቸው ነው፡፡ ምክንያቱም አበጋዞቹ ብዙ ፈተናዎችን ተጋፍጠው ያለፉ፣ ድህነትን በማሸነፍ ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን መመገብ የሚችሉ፣ የተከበሩና በዝናቸው የታወቁ፣ ባህላዊ የሹመት ስያሜ ያላቸው በመሆናቸው ነው፡፡ እንዲሁም ስርዓቱን የሚፈጽሙ የሚያረጋግጡ ስለሆኑ ነው፡፡* (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፡ 24/2005) ፡፡

ይህንኑ አቶ አበበ አቡኔ ሲያብራሩ "አበጋዞቹ ለብቻ የሆኑት የተለዩና የተከበሩ፣ ባህላዊ የሹመት ስያሜ የተሰጣቸው ሲሆኑ፣ በባህሉም የተጣላን የሚያስታርቁ የሚመርቁ ሲሆኑ፣ ይፈራሉ፣ ይከበራሉ፡፡ ስለዚህም በማዕረጋቸው ተመሳሳይ ስለሆኑ ተለይተው ለብቻ ይቀመጣሉ፡፡ በግንኙነታቸው አጋጣሚም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፣ ይጨዋወታሉ፣" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 24/2005) ፡፡

አበጋዞቹ ለብቻ የሚሆኑበት ምክንያትን ከላይ የተገለጸ ቢሆንም ለዚህ ክብርና ዝና ለመብቃት በህይወት ዘመናቸው ክብቶችን በማርባት ብዙ ፈተና እና ችግሮችን በማለፍ የወገና ስርዓት አዘጋጅተው ስለተፈጸመላቸው ሲሆን፣ በማህበረሰቡ ዘንድም የተለየ ቦታና ዕውቅና ስለሚሰጣቸው ነው፡፡ በመስክ ቆይታዬ ምልከታ ባደረኩባቸው ቦታዎች ካየሁት ለመጥቀስ በሶሮ ወረዳ ቡርዬ ለንጌ ቀበሌ ታህሳስ 27/2005 በአቶ ደሳለኝ ኤርቃሎ ቆጠራ ላይ ተገኝቼ እንደተመለከትኩት አበጋዞቹ ለብቻ በተለየ ቤት ሆነው፣ እነሱ ያሉበት ቤት ማዕረግ የሌለው ሰው ለመግባት እንደማይፈቀድለት መገንዘብ ችያለሁ፡፡

በተጨማሪም ባላቸው ክብርና ማዕረግ ተለይተው ሲቀመጡ የሚያዩ ሌሎች ከብት አርቢዎች በህይወት ዘመናቸው ለዚህ ክብርና ማዕረግ ለመድረስ እንዲነሳሱ፡ እንዲፎካከሩ ያደርጋል፡፡

አበጋዞች በሚያርፉበት ቤት ቦታ ቦታ ይዘው ከተቀመጡ በኋላ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል፡፡ መስተንግዶው ቅቤ በብዛት ያለበት ክትፎ (ሱልሶ Sulso'o)፣ ጠጅ፣ ብርዝ እንደፍላጎታቸው ይቀርብላቸዋል፡፡ አቶ አበበ ጊቻሞ ስለሚደረግላቸው መስተንግዶ ሲገልጹ "በሚደረግላቸው መስተንግዶ የሚቀርብላቸው ምግብና መጠጥ በቃ እስከሚሉ ወይም ተርፏቸው እስከሚነሳ ድረስ መሆን አለበት፡፡ በደንብ ካልተስተናገዱ እኛን እንኳን በደንብ አጥግቦ ማስተናገድ ያልቻለ መቶ እስቆጠረ ሊባል አይገባውም በማለት ሊያጣጥሉ ይችላሉ ተብሎ ስለሚሰጋ ነው፣" ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ጥር፡ 5/2005 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በኋላ ሁሉም በየወገኑ ሆኖ በልቶ ጠጥቶ ጠግቦ ሌሊቱን በሙሉ የተወሰኑት ይጨፍራሉ፤ አንዳንዱም በደስታ ስሜት ሆኖ ዘር ዘሩን እየጠራ ይፎክራል፤ እንዲሁም ቀረርቶ (ድራንቻ Diraancha)[9] ሲያሰማ፤ ሌሎቹ ደግሞ በያሉበት ክብ ክብ ሰርተው የራሳቸውን ወሬ ሲያወሩ፤ በሶሮ ወረዳ ኦምቤ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ደስታ ጎቦሮ የቆጠራ ስርዓት ላይ አይቻለሁ፡፡ ከሚያሰሙት ቀረርቶ (ድራንቻ) ለአብነት የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡ ይዘቱም አስቆጣሪው ኑሮው የተሟላ መሆኑን፣ በተግባሩ ጠንካራና ጀግና እንደሆነ፣ ሀብት ሞልቶት የተረፈው ስም አስጠሪ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ (ቀረርቶውን የሰማሁት በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ በአቶ ላምባሞ ሚጦሬ የቆጠራ ስርዓት ላይ ነው)፡፡

Baalle yoo sammo
Buuro itakka'ate
Bandoo Horoore
Belecoo Labasii hirifanii
Baalli kiinim barkuma
Begadim maccaamo
Duuna heemachchisa
Daqayyam biir oota
Laro kumaam beet
Baallilli laro kumanne
Baalle hiraagaanchi beet
Bagado baddoobee'i Hadiyyichcho
Gunguunsi agirinne bagadaam maccaaminne
Gooraade'i sayif gaaxxi illagenne
Gaadaano shaa hoora dabaro
Jor oota gindanso
Bagaxxi woronnem biqee edaakka

---

[9] ድራንቻ (Diraancha) ፡- ድራንቻ የሚለው ቃል በአማርኛ ቀረርቶ እንደ ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በጦርነት ተዋግቶ ላስመዘገበው የጀግንነት ተግባር፣ እንዲሁም በተሰማራበት ስራ ለምሳሌ ከብት በማርባት ባገኘው ስኬት፣ ሀብት፣ ጉብዝና እና ችሎታው ተገናዝቦ ማንነቱን በማሞገስ በዜማ ግጥም የሚደረደርበት ነው፡፡ (አቶ አሸቱ ጡሚሶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 27/2005 ዓ.ም)፡፡

Baddoo bee'e Hadiyyichcho

Hanqi Hadiyyichcho Hadiyyichcho

ላባ በእናቴ የሰካ

ቅቤ የምትበላ ቅቤ የምትቀባ

ጆሮዎቼ የሚያብረቀርቁለት

ልብሱ የለሰለሰ ቁርበት

የጥልቁን እለት ትራሱ ያደረገ

ጦሩንም ባለጆሮእሙን የፈለገ

ተራራን እንደደመና አጥቋሪ

በአውላላ ሜዳ አጥር አጣሪ

የባለ ሽህ ከብት ባለቤት

የሽለቆ አይን የሺህ ሀብት

ገደል ሰንጣቂ ባለ ትንቢት

በጦር ፊት የማይፈራ የሀድያ ልጅ

ቅንነት የሰነቀ ግፍን ደግሞ የማይሰራ

በጎራዴ ሰይፍ በጦር ግንባር

ጋሻ ለባሽ ያዥ ጆሮጓም ጦር

ሽፍታ ገድሎ ምርኮ መላሽ

በጦር ግንባር ቀዳሚ

ፊርቶ የማይጠፋ ሀድያ

እውነትም ሀድያ ሀድያ፡፡

በጥቅሉ በዋዜማው እለት ለሊቱን ሙሉ የመጡት እንግዶች በቡድን በቡድናቸው ሆነው እየበሉ እየጠጡ፣ እየተደሰቱ እየጨፈሩ፣ እየተጨዋወቱ ንጋት ላይ የሚከወነውን ስርዓት ይጠባበቃሉ፡፡

### 4.3.3 ወደ ወንዝ የመሄድ ስርዓት ከዋኔ

በ4.3.2 ላይ እንደተገለጸው በዋዜማው እለት የመጡ ሰዎች በሉተው ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ ምሽቱን በተለያዩ ጫወታዎች ያሳልፋሉ፡፡ ከዚያም ወንዝ መሄጃ ሰዓት ሲደርስ ለመሄድ ይዘጋጃሉ፡፡ የመሄጃ ሰዓቱም ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ባለው ውስጥ ነው፡፡ ወደ ወንዝ መሄጃ ሰዓት ሲቃረብ እንቅስቀሴው የሚጀምር ሲሆን፣

በዋዜማው ዕለት መጥተው ካደሩት ቤተዘመዶች ውስጥ ወጣቶቹ በመሰባሰብ አበጋዛ አወንሴሄ (Abagaaza awwanseehee) ይላሉ፡፡ ይህም አበጋዝ ምራን እንሂድ እንደ ማለት ሲሆን የስርዓቱ መፈፀሚያ ሰዓት መድረሱን መጠቆሚያና መቀስቀሻ ነው፡፡ ወደ ወንዝ ለመሄድ ሰው ሁሉ ካረፈበት ቦታ የከብቶቹ በረት ያለበት ጋ መሰባሰብ ይጀምራል፡፡ ወንዝ የሚደረገው ስርዓትን ለመከታተል እዚያ የተገኘ ሰው ሁሉ ሲሄድ፤ በምልከታዬ ጊዜ ልገነዘብ የቻልኩት አቅም የሌላቸው ሽማግሌዎች ብቻ እቤት ይቆያሉ፡፡ (ሶሮ ወረዳ እምቤ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ደስታ ነበሮ ቆጠራ ጊዜ አስተውያለሁ)፡፡ ስርዓቱ የሚከወንበት ወንዝ በአካባቢው ካሉ ወንዞች ወስጥ ለአስቆጣሪው ሰውዬ ቤት ቀረብ ብሎ ያለው ነው፡፡ ወንዙ ክረምት ከበጋ የሚፈስ ነው፡፡

አበጋዝ ጊንታሞ ወልገኖን ወደ ወንዝ በሌሊት መሄድ ለምን እንዳስፈለገ እንዲሁም ወንዙ የማይደርቅ የሆነበት ምክንያትን ጠይቄአቸው ሲመልሱልኝ "ሌሊት መሄድ ያስፈለገው ሰው ሳይነካካው ባደረው የወንዝ ውሃ ስርዓቱን ለመፈጸም ነው፡፡ ወንዙ የማይደርቅ እንዲሆን የተፈለገው ልክ እንደ ወንዙ የሰውዬውም ሀብት ለዘር ዘሩ እንዲሸጋገር በማለት ነው" ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

ስርዓቱ የሚፈፀምበት ወንዝን ሰው ተሻግሮት ስርዓቱ ከተፈጸመ በሰውዬው ሀብት ላይ ጥላ ይሆንበታል፤ ሀብቱ አይጨምርም ለጤንነቱም ጥሩ አይደለም ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲሁም በጋ ከክረምት የማይፈስ ወንዝ ላይ ስርዓቱ ከተፈፀመ ሀብቱ፡ ዝናው ለዘሩ አይሸጋገርም ተብሎ ይታመናል፡፡ በማይደርቅ ወንዝ ላይ ስርዓቱ ከተፈፀመ ያለውን መጥፎ ችግር ሁሉ አጥቦ ይዞ ይሄዳል፤ ሀብቱ ዝናው ከራሱ አልፎ ለዘርዘሩ ይተላለፋል ይባላል፡፡

ሁሉም ሰው ከያለበት ቦታ እየተነሳ የከብቶቹ በረት ወዳለበት ይሰበሰባል፡፡ አስቆጣሪው ሰውዬም ከሚስቱ[10] ጋር አንድ ላይ በመሆን ጦርና የዝግባ ቅጠል፤ ሚስቱ ደግሞ በወተት

[10] ሚስት፡- አቶ አበበ ጊቻሞ እንደገለጹልኝ "ምናልባት አስቆጣሪው ሰውዬ ሁለት ሚስት ያለው ከሆነ ሁለተኛዋም ሚስት አብራ ትሆናለች፡፡ ስርዓቱ ግን በዋነኛነት የሚከናወነው በመጀመሪዋ ሚስት ቤት ነው፤" ብለውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 24/2005 ዓ.ም) ምልከታ ካደረኩባቸው ቦታዎች ውስጥ በሶሮ ወረዳ እምቤ ለንጌ ቀበሌ በተካሄደው ስርዓት ላይ አስቆጣሪው አቶ ደስታ ነቦሮ ባለ ሁለት ሚስት በመሆናቸው ሁለተኛዋ ሚስት አብራ ሆና ስርዓቱ ግን የተከወነው በመጀመሪያዋ ሚስት ቤት እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡

ማለቢያ፣ መጠጫ (ጮጮ) ትኩስ ወተትና የዝግባ ቅጠል በመያዝ ካረፉበት ቦታ ወደ በረቱ ታጅበው ይመጣሉ፡፡ የሰውዬው እህት ማርና አነስተኛ ላፋ በመያዝ አብራ ትሆናለች፡፡ ሰውዬው እህት ከሌለውስ ብዬ ለጠየኳቸው "የአክስቱ (አባቱ እህት) ልጅ አብራ ትሆናለች" ሲሉ ነግረውኛል፡፡ (ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሬ፡ ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 25/2005)፡፡ ሁሉም ሰው ከከብቶቹ በረት በር ፊት ለፊት በግራና በቀኝ በመደርደር መሀሉን ክፍት አድርገው ይቆማሉ፡፡ አስቆጣሪው ከነባለቤቱ፡ ከአበጋዞቹ ውስጥ የተወከሉት አንጋፋ አበጋዞች ብጋራ በመሆን በረቱ እንዲከፈት ፈቃድ ይሰጣሉ፡፡

በባህሉ መሰረት በረቱን የሚከፍተው የአስቆጣሪው ሰውዬ ወንድ ልጅ ሲሆን፤ አስቆጣሪው ወንድ ልጅ ከሌለው እራሱ ይከፍታል፡፡ ምክንያቱም ሌላ ሰው የሚከፍት ከሆነ የለፋበት ሀብቱ በረከቱ ከሰውዬው ይሸሻል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በመስክ ቆይታዬ ምልከታ ካደረኩባቸው ውስጥ በሶሮ ወረዳ ቡረይ ለንጌ ቀበሌ ያስቆጠሩት አቶ ደሳለኝ ኤርቃሎ ወንድ ልጅ ስለሌላቸው በረቱን እራሳቸው ሲከፍቱ መመልከት ችያለሁ፡፡ ሴት ልጅ ለምን በረቱን አትከፍትም ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ አቶ አበበ አቡኔ የተባሉት ሲገልጹ፡-

> *በባህሉ ሴት ልጅ እንድትከፍት አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም በባህሉ የአባት ተግባርን ተክቶ ይፈጽማል የሚባለው ወንድ ልጅ ነው፡፡ አባት ሲሞት ንብረት የሚወርሰው፤ ዘርን የሚያስጠራው ወንድ ልጅ ነው፡፡ ከብት አርብቶ ለማዕረግ መብቃት የሚችለውም ወንድ ልጅ ነው፡፡ ሴት ከባሏ ጋር ሆና ነው ማርባት የምትችለው፡፡ ስለዚህም ሴት ልጅ በረት እንድትከፍት አይፈቀድላትም፤ ሲሉ* ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ጥር፡ 5/2005) ፡፡

ወንዱ ልጅ በረቱ ውስጥ በመግባት በቅርብ ጊዜ ከተወለዱት ጥጆች ውስጥ ደስ ያለውን በማቀፍ (በመያዝ) የበረቱን በር ከፍቶ ይወጣል፡፡ የጥጃዋ እናት ላምም ጥጃዋን በማለት ተከትላ ከበረቱ ትወጣለች፡፡ ከዚያ ሌሎችም ከብቶች እየተከታተሉ በሰልፍ ከበረቱ ይወጣሉ፡፡ ጥጃ የታቀፈው (የያዘው) ልጅም ወደ ወንዝ ይመራል፡፡ ሰዎቹም በግራና በቀኝ ሆነው እንዲሁም ሰውዬውን ከነባለቤቱ አጅበው ቀረርቶ (ድራንቻ) እያሰሙ፣ በጭፈራና በእልል ይጓዛሉ፡፡ ወደ ወንዝ በሚኬድበት ጊዜ ማንኛውም ሰው ከብቶቹን አቋርጦ ማለፍ አይፈቀድም፤ ነውር ነው፡፡

የሰውዬው ወንድ ልጅ ጥጃ ይዞ በረቱን እንዲከፍት የተደረገበት ትርጓሜን አበጋዝ ስዩም ደሪሎ እንደሚሉት “በሀድያ ባህል ወንድ ልጅ ዘር ስለሚያስጠራ ወደፊት አባቱ የደረሰበት ትልቅ ክብርና ዝና፣ ባህላዊ ስያሜን እንዲያገኝ፣ በዘር ዘሩ እንዲተላለፍ በረከቱ ይደርሰዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ያቀፊውን ጥጃ እንዲወስድ የሚደረገውም ለዚሁ ነው፣” ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ከራሳቸው ጋር በማገናኘት መረጃ ያቀበሉኝ አበጋዝ አጪቶ ኦርጂኖ እንደሚሉት “ወንድ ልጅ በረት እንዲከፍት መደረጉ ያለው በረከት በዘሩ ይተላለፍ በማለት ነው፡፡ ሁኔታውን በይበልጥ ለማስረገጥ በእኔ ቤተሰብ ክብት በማስቆጠር እኔ 12ኛ ትውልድ ነኝ፡፡ የእኔ ልጅ ደግሞ እንደዚሁ አስቆጥሮ 13ኛ ሆኗል፡፡ ስለዚህም በረከቱ ይደርሳል፤” በማለት አብራርተውልኛል፡፡(ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 5/2005 ዓ.ም)፡፡




ፎቶ 7. ጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ የአቶ ላምባሞ ሚጦራ ወንድ ልጅ በረት ከፍቶ ጥጃ ይዞ ወደ ጎንቦራ ወንዝ ሲሄዱ፤

ከብቶቹ ወደ ወንዝ በሚሄዱበት ጊዜ ማቋረጥ የተከለከለበት ምክንያት አቶ አበበ ጊቻሞ “በረከት ይወስዳል፤ ችግር ይደርስበታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፤” ብለውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም) ፡፡ በመስክ ቆይታዬ ወቅትም ሰዎች ከብቶቹን አቋርጠው እንዳያልፉ የሚጠብቁ እንዳሉ በጎምቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ ጥር 5/2005 በተካሄደው በአቶ ላምባሞ ሚጦሬ ቆጠራ ላይ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

ምልከታ ባደረኩበቸው ቦታዎች ስርዓቱ የተፈጸመባቸው ወንዞች ሁለት ሲሆን እነሱም በሶሮ ወረዳ ‹‹ገሙና›› የተሰኘው፣ በጎንቦራ ወረዳ ‹‹ጎንቦራ›› የተሰኘው ናቸው፡፡ ወንዞቹ ስርዓቱ ከሚፈጸምላቸው ሰዎች ቤት በአማካይ ለመሄድ ብቻ ከአንድ ሰዓት እስከ አንድ ተኩል የሚያስኬድ ርቀት አላቸው፡፡ ከብቶቹ ወንዝ ሲደርሱ በግራ በኩል እንዲሻገሩ በማድረግ፣ ሰብስበው ያቆሟቸዋል፡፡ በስርዓቱ ላይ የተገኙ ሰዎች ወንዙን ሳይሻገሩ ከወዲህ ማዶ አፋፍ ላይ ሆነው ስርዓቱን ይከታተላሉ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አስቆጣሪው ሰውዬ፣ ባለቤቱና እህቱ ከቤት ሲነሱ የያዟቸው የመከወኛ ቁሶች በወተት መጠጫ (ኦቾ) ትኩስ ወተት ፡ ማር፣ የዝግባ ቅጠል ዝንጣፊና መካከለኛ ሳፋ ይዘው ወንዙ ውስጥ ገብተው ቆሙ፡፡ በመቀጠልም በሳፋው ከወንዙ ውሃ በመቅዳት፣ ማሩንና ወተቱን ጨምረው ቀላቀሉ፡፡ ከዚያም ወንዙን ተሻግረው እንዲቆሙ የተደረጉት ከብቶች በረቱን በከፈተው ልጅ መሪነት ተመልሰው በቀኝ በኩል አሻገሯቸው፡፡ ሲሻገሩ ሰውዬው ባለቤቱ እና እህቱ በጋራ በመሆን የተቀላቀለውን (ማር፣ ወተትና ውሃ) በዝግባ ቅጠል እየነከሩ በከብቶቹ ላይ ረጭተዋል፡፡ ወንዝ ላይ የሚከወነው ስርዓት ከሁለት ሰዓት ተኩል እስከ ሶስት ሰዓት ወስዷል፡፡ የመርጨቱን ስርዓት በሚከወኑበት ወቅት እንዲህ ይላሉ፡፡

| | |
|---|---|
| Larro hururee | ከብቶች ዘልቃችሁ ሂዱ |
| Larro Liilee'e | ከብቶች ብዙ ተባዙ |
| Larro barkatee | ከብቶች በርከቱ ፡፡ |



ፎቶ 8. አስቆጣሪው ደስታ ጎቦሮ ከሁለቱ ሚስቶቻቸውና ከእህታቸው ጋር በመሆን ከብቶቹ ሲሻገሩ ለመርጨት ገሙና በተባለው ወንዝ መሃል ቆመው፡፡



ፎቶ 9. ከብቶቹ እየተረጨባቸው ወንዝ ሲሻገሩ፤

ከብቶቹ ሲሻገሩ እየረጩ እየረጩ በመጨረሻ ላይ ወንዙን ከሚሻገሩት ከብቶች ውስጥ የሰውዬው እህት ደስ ያላትን አንድ ከብት ጭራ ይዛ ተሻገረች፡፡



*ፎቶ 10. ሶሮ ወረዳ ኦምቤ ለንጌ ቀበሌ ያስቆጠሩት የአቶ ደስታ ኀቦሮ እህት በመጨረሻ ወንዙን ከሚሻገሩት ከብቶች ውስጥ መርጣ ጭራ ይዛ ስትሻገር ፡*

ስርዓቱ ሲከወን ከሚመለከቱት ሰዎች ውስጥ እናቶች እልል ሲሉ ችሎታው ያላቸው ድራንቻ አሰምተዋል፡፡

በወንዝ የሚደረገው ስርዓት ከዋኔ ካለቀ በኋላ ሰውዬውን ከነሚስቱ በማጀብ ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ ሲመለሱ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፡፡ ከእነሱም ውስጥ ማኸር ኢዮና (Mahaar Iyyonaa)[11] የሚለውና ሽምበለላዮኔ (Shambalalloyonni)[12] የተሰኙት ይጠቀሳሉ፡፡

**Mahaar Iyyonaa**
Iyyonaa Iyyonaa mahaar Iyyonaa

Gax fella'innem mahaar Iyyonaa

Gubanaatinnem mahaar Iyyonaa

Gorba'l xibbi nnem mahaar Iyyonaa

ሹመትህ ይጽና ክበር

---

[11] ማኸር ኢዮና፡- ማለት የተሰጠህ ማዕረግ ያኑርህ ሹመት ይዳብር እንደማለት ነው፡፡

[12] ሽምበለላዮኔ ፡- ማለት የተትረፈረፈ፣ የሞላ እንደማለት ነው፡፡

ቤት ሞልቶ ካሉ ፍየሎችህ ጋር

ከተሟላ ከብቶችህ ጋር

ከሞሉ ጊደሮችህ ጋር፡፡

የዘፈኑ ይዘት የተሰጠህ ማዕረግ የተሰጠህ ስያሜ ይጽናልህ ያለህ ሀብት ከአንተ አይለይ የተከበርክ ሁን ማለት ነው ፡፡

Shambalalloyonni

Shambalalloyonni shambalalloyonni

Shambalalloyonni shambalalloyonni

Gax fella'innem shambalalloyonni

Gubanaam minem shambalalloyonni

Guba'i xibbinnem shambalalloyonn

Gammaam Hallinnem shambalalloyonni

Guuto'aam landinnem shambalalloyonni

Gubeedaam oosinnem shambalalloyonni

Shambalalloyonni shambalalloyonni

የሞላ የተትረፈረፈ በሽበሽ

የሞላ የተትረፈረፈ በሽበሽ

በማደሪያ ያሉ ፍየሎች በሽበሽ

ካማረውና መዝጊያው ጠንካራ ቤትህ በሽበሽ

ከመቶ ከብቶችህ ጋር በሽበሽ

ጋማቸው ጎፈሬ ከመሰሉ አህዮችህ ጋር በሽበሽ

ሴት ልጅ በሽበሽ

ከባለጡንቻዎች ወንድ ልጆችህ ጋር በሽበሽ

የሞላ የተትረፈረፈ በሽበሽ የሆነ፡፡

የዘፈኑ ይዘት የወገና ስርዓት የተፈጸመለት ሰውዬ ያለውን ሀብት ብዛት (በተለይም የከብቶች) ቤቱንና ኑሮው ሁሉም ነገር የሞላው መሆኑን በመግለጽ፣ በማድነቅና መገረምን የተሰጠው ማዕረግ ይገባዋል ማለት ነው፡፡

ከብቶቹ ወንዙን በታች (በግራ) በኩል ተሻግረው በመቀጠልም ደግሞ በላይ (በቀኝ) በኩል እንዲመለሱ የተደረገው ለምንድ ነው? በማለት አበጋዝ ሽጎ ኑራሞን ስጠይቃቸው "በመጀመሪያ በግራ በኩል መሻገራቸው እንደጥምቀት ነው፡፡ የነበረባቸው ችግር በወንዙ ውሃ ታጥቦ እንዲወርድ ማድረግ ነው፡፡ በቀኝ መመለሳቸው ነፃ መሆናቸውን፣ አዲስነታቸውን ለማመልከት" እንደሆነ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 23/2005 ዓ.ም)፡፡

ከሳቸው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በመጀመሪያ በግራ መሻገራቸው ለወገና ስርዓት ለመድረስ የነበረባቸው ክፉ ነገር ሁሉ በወንዙ ውሃ ታጥቦ ወደታች ይውረድ፤ የነበረው ችግር ሁሉ በግራ ይውደቅ፤ እንደማለት ነው፡፡ በቀኝ በኩል እንዲመለሱ ተደርጎ መረጨታቸው፤ ያለባቸው ክፉ ነገር በወንዙ ውሃ ስለታጠበ ከዚህ ወዲህ ችግር አያጋጥማችሁ ነፃ ሁኑ፤ ቀኝ ያጋጥማችሁ፤ የሚል ትርጓሜ ይይዛል፡፡

ሌላው በከብቶቹ ላይ የተረጨው የማር፣ የወተትና የውሃ ቅይጥ ትርጉም ምን እንደሆነ በጎንቦራ ወረዳ ኦሌ ቀበሌ ስምንት ሰዎች የተሳተፉበት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ የነበሩት አበጋዝ አጪቆ ኦርጅኖ የተባሉት እዲህ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

> *ውሃ የማያልቅ ትልቅ ስጦታ ሲሆን እንደልብ ይገኛል፡፡ ከብቶቹም እንደ ክረምት ወንዝ ይሙሉ፣ ይብዙ፤ በሽታና ድርቅ አያጥፋቸው እንደማለት ነው፡፡ ማር በሀድያ በርካታ አገልግሎት ያለው ሲሆን ለአብነትም ለምርቃት ማካሄጃ ለመድኃኒትነት ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በከብቶቹ ላይ መረጨቱ ምርቃቱ እንዲሰምር እንዲራቡ፤ ከክፉ ነገር ከረሃብ፣ ከበሽታና ከሰው አይን እንዲተርፉ፤ መድኃኒት ነው ብሎ በማሰብ ነው፡፡ ወተት መረጨቱም በከብቶቹ ላይ ምንም ችግር አይድረስ፡፡ መድኃኒት ይሁናችሁ፤ እርቡ ወተት አይታጣባችሁ እንደማለት ነው፡፡ ለመርጫነት የተጠቀሙት የዝግባ ቅጠልን በተመለከተ የዝግባ ዛፍ ክረምት ከበጋ ሁሌም አረንጓዴ ነው፤ ቅጠሉ ሁሉ በአንድ ጊዜ አይራገፍም፤ ከብቶቹም እንዲሁ የወቅቶች መቀያየር ችግር አይፈጠርባችሁ ማለት ነው፡፡* (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ጥር፣ 5/2005 ዓ.ም)፡፡

በተጨማሪም በቡድን ውይይቱ ጊዜ የዝግባ ቅጠል ለመርጫነት የያዙበት ምክንያት የዝግባ ዛፍ ሲያድግ ቅርንጫፎቹ የበዙ ሲሆኑ፤ በአንድ የዝግባ ዛፍ ዝንጣፊ ላይ ብቻ በርካታ ቅጠሎች ይገኛሉ፡፡ እንደዚሁም ከብቶቹ ይራቡ ቁጥራቸው ይብዛ እንደማለት ነው፡፡ የሰውየው እህት በመጨረሻ ወንዙን ከሚሻገሩት ውስጥ የአንዱን ከብት ጭራ ይዛ ተሻግራ እንድትወስድ የሚደረገው ከኋላ ከለላ መሆኗን፤ ምስጢር ደባቂነቷን ለመግለጽ ሲሆን፤ እንዲሁም ዝናና ክብሩ ይድረሳት፤ የሚል ትርጓሜን እንደሚይዝ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ተጠቅሷል፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፤ ጥር 5/2005) ፡፡

ከብቶችን ወደ ወንዝ ይዘው በመሄድ የመርጨት ስርዓት ሲከወን በመስክ ቆይታዬ በተገኘሁበት በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ አቶ ላምባሞ ሚጦሬ ሲያስቆጥሩ ከብቶቹ ወንዙን በግራ ተሻግረው በቀኝ በኩል ሲመለሱ አንድ ኮርማ ስሪያ ይዞ በአንዲት ላም ላይ ሲወጣ ያዩ አባቶች ሲደሰቱ፣ እናቶች እልልታ ሲያሰሙ በመመልከቴ አበጋዝ ኤርሶ ቱበሌ እንዲያብራሩልኝ ጠይቄያቸው ሲነግሩኝ "የወገና ስርዓት እየተፈፀመ ስሪያ መፈጠሩ ለሰውዬው ትልቅ በረከት ነው፡፡ ከብቶቹ እንደሚረቡለት ይህ ዝና እና ክብር ለልጅ ልጆቹ እንደሚደርስ የሚያበስር በመሆኑ ነው የተደሰቱት እልል ያሉት፤" ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 4/2005) ፡፡

### 4.3.4 ከወንዝ መልስ የሚደረጉ ስርዓተ ከዋኔዎች

ከብቶቹን ወንዝ በመውሰድ (4.3.3) ላይ እንደተገለፀው የመርጨት ስርዓት ከተከወነ በኋላ ሰውዬውን ከነባለቤቱ በማጀብ ባህላዊ ጭፈራ እያዜሙ ወደ ቤት መልስ ይደረጋል ፡፡ እቤት ሲደርሱ አስቆጣሪውና ሚስቱ በቤታቸው ምሰሶ አጠገብ (ጅባ)[13] ምንጣፍ ተነጥፎ በላዩ ላይ ነት (ሂርፈና) ላይ ይቀመጣሉ፡፡

[13] ጅባ፡- ከእንሰት ተልክ የሚሰራና ለመኝታ ምንጣፍነት የሚያገለግል ነው፡፡



ፎቶ 11. በጎንቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ ያስቆጠሩት አቶ ላምባሞ ሚጦሬ ከባለቤታቸው ጋር ከወንዝ መልስ ምሰሶ አጠገብ ተቀምጠው፣

አስቆጣሪው ሰውዬና ባለቤቱ ምሰሶ አጠገብ የተቀመጡበትን ምክንያት አቶ አበበ አቡኔ ሲያብራሩ "ምሰሶ ቤቱን በሙሉ ተሸክሞ የያዘ ነው፤ ምሰሶው ባይኖር ቤቱ ቤት አይሆንም፡፡ በሀድያ ባህል አንድ አባወራ የቤተሰቡ ምሰሶ ወይም ዋና ተድርጎ ነው የሚታየው፡፡ በምሰሶ ስር መቀመጡም አንተ እንደምሰሶ ሁሉን ተሸክመህ የያዝክ ነህ፡፡ ለወደፊትም የቤተ ዘመድ ዋና ሰብሳቢ ምሰሶ ያድርግህ እንደማለት ነው" ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

በተጨማሪም አቶ አበበ ጊቻሞ ሲገልጹ "በሀድያ ባህል ለቤት ለምሰሶ የሚሆን እንጨት የሚቆረጠው ባለቤቱ የመረጠው እና በምሳር ምልክት ካደረገ በኋላ ነው፡፡ እንዲሁም የሚቆምበት ጉድጓድ ለመቆፈር ባለቤቱ በመቆፈሪያ ቦታው ላይ እንደመቆፈር በማድረግ ጀምሮ ሲሰጥ ነው የሚቆፈረው፡፡ ስለዚህም አባወራው በምሰሶ ይመሰላል፡፡ አንድ አባወራ ሲሞት ምሰሶው ተሰበረ እንደሚባል" አያይዘው ይጠቅሳሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ ታህሳስ፡ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡

በመሆኑ ምሰሶው ስር ከነባለቤቱ መቀመጡ የቤቱ አባወራ ዋና መሆኑን፤ ባለቤቱም አጋዥ መሆኗን ለመግለጽ ነው፡፡ በሀድያ ምሰሶ አጠገብ መቀመጥ የሚችሉት የቤቱ አባወራ እና ባለቤቱ ብቻ ናቸው፡፡ ሌላ ሰው መቀመጥ አይፈቀድለትም ፡፡

አባወራውና ሚስቱ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ሁሉም አበጋዞቹ ሁለቱ ወደ ተቀመጡበት ቤት ሄደው ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም ከሰውዬው ከብቶች መካከል ለስርዓቱ መከወኛ የሚሆን አንድ ወይፈን ቀርቧል፡፡ የቀረበው ወይፈን ከመታረዱ በፊት አካሉ ላይ የሚታይ ችግር እንደሌለበት ከአበጋዞቹ የተወከሉት ፍተሻ አድርገዋል፡፡ እንደ አበጋዝ ሽጎ ኑራሞ ገለጻ "ፍተሻው ያስፈለገበት ምክንያት ምናልባት በዓይኑ፣ በእግሩ፣ በጆሮው፣ በቀንዱ፣ በጭራው ላይ እንከን፣ ጉዳት ወይም ጉድለት፣ ካለበት ተቀባይነት ስለማይኖረው ነው፡፡ ጉድለት እንዳለበት እየታወቀ ታርዶ ስርዓቱ ከተፈጸመ ለወደፊቱ ሰውዬው ጥሩ ነገር አይገጥመውም ተብሎ ስለሚታመን ነው፤" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 21/2005)፡፡ በመስክ ቆይታዬ ውስጥ በሶሮ ወረዳ ኦምቤ ለንጌ ቀበሌ በአቶ ደስታ ጎቦሮ ቆጠራ ጊዜ፣ ለስርዓቱ መፈፀሚያ ተብሎ የቀረበ ወይፈን ሲራመድ ያነከሳል ብለው ሲመልሱ ተመልክቼያለሁ፡፡

የሚቀርበው ወይፈን ተቀባይነት የሚያገኘው በአካሉ ላይ ችግር የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ከዚያም ወይፈኑ ቀርቦ ምርቃት አካሂደዋል ፡፡ የሚመርቁት ከሰውዬው ጎሳ እና ቤተሰብ የተወከሉ ሽማግሌዎችና ሰውዬው ጭምር ነው፡፡ በወይፈኑ ጀርባ ላይ ለምለም እርጥብ ሳር በማድረግ ነው፡፡ ሲመርቁ ‹‹ሀብትህ ይባረክ፣ ተከበር፣ ይህ ዝና ክብር ደስታ ለልጆችህ ይተላለፍ፣ ክፉ ከአንተ ይራቅ›› በማለት ነው፡፡

ምርቃቱ በለምለም እርጥብ ሳር መካሄዱ አቶ አበበ አቡኔ "በሀድያ ባህል ምርቃት ከሚካሄድባቸው ነገሮች አንዱ ለምለም ሳር ነው፡፡ ለምለም ሳር (ሰርዶ) በጋ ወቅት ደርቆ የጠፋ ቢመስልም ዝናብ ሲዘንብ ወዲያው ይበቅላል፡፡ ምርቃቱም በለምለም ሳር መካሄዱ ለምለምና እርጥብ በመሆኑ ለሰውዬው ጥሩ ነገርን እንዲገጥመው መመኘትን፤ ምርቃቱ ይስመርልህ፤ ይሙላ እንደማለት ነው፤" ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 25/2005 ዓ.ም) ፡፡



*ፎቶ 12. ስርዓቱ የሚፈጸምበት ወይፈን ቀርቦ ለምለም ሳር ላይ ተደርጎ ምርቃት ሲካሄድ፣*

ምርቃቱ ከተካሄደ በኋላ ወይፈኑ ታረደ፡፡ እንደታረደም ወዲያውኑ ነፍሱ ሳትወጣ እየተንፈራገጠ እያለ ቆዳው ከመገፈፉ በፊት የዘር ማስተላለፊያው ብልት (ሀንጩፋ Hancufa)[14] ሙሉ በሙሉ ተገፎ ወጣ፡፡ ቀጥሎም ነፍሱ ከወጣች በኋላ ቆዳውን በመግፈፍ ብልቶቹን ለያይተው በማውጣት አስቀመጡ፡፡

ወይፈኑ ታርዶ እየተንፈራገጠ እያለ ተለይቶ ለምን እንደወጣ ዳኛ ደሳለኝ ሱጌቦ ሲገልጹ "የዘር ማስተላለፊያ ብልት (ሀንጩፋው) የስርዓቱ መፈጸሚያ ስለሆነ ሳይሞት ከነህይወቱ እንዳለ፤ ዘሩ ቀጣይነት እንዳለው በማሰብ ነው፡፡ ያልተከላሸ የሆነበትም ምክንያት የከብት ዘር፣ ሀብት ከአስቆጣሪው ቤት እንዳይጠፋ በማለት ነው" ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 24/2005) ፡፡

ከታረደው ወይፈን ስጋ ላይ ለስርዓቱ መከወኛ የሚሆኑት ብልቶችን ለይቶ በማስቀመጥ ክትፎ ያዘጋጃሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ለአበጋዞቹ ማር ቀርቦላቸው እየበሉ ጠጅ፣ ብርዝ እየጠጡ እየተጫዋወቱ ቆይተዋል፡፡ ከቆይታው በኋላ ቅቤ በብዛት የተጨመረበት ክትፎ ቀርቦላቸው ተርፎ እስኪመለስ ድረስ በሉ፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደገለጽኩት አበጋዞቹ

---

[14] ሀንጩፋ ፡- የበሬ፣ የወይፈን የዘር ማስተላለፊያ፣ ሸንት መሸኛው ብልት አበጋዝ ለሆነ ሰው ክንድ ላይ የሚጠለቅ ነው፡፡ (ዳኛ ደሳለኝ ሱጌቦ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ፣ 24/2005)፡፡

እኛን እንኳን ማጥገብ ያልቻለ መቶ አስቆጥሯል፣ ሀብታምና ባለ ብዙ ከብት ሊባል አይገባውም በማለት ውድቅ ያረጋሉ ተብሎ ስለሚሰጋ ነው፡፡ ሰውዬውና ባለቤቱም በተቀመጡበት ሆነው ይስተናገዳሉ፡፡ በልተው ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ ስርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡ ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ስርዓቱን የሚፈጽሙትና የሚያጸድቁት አበጋዞቹ ሲሆኑ፤ በዋናነት ግን የስርዓቱ ከዋኝ በወቅቱ (በጊዜው) ካሉት አበጋዞች ውስጥ ከብት በማስቆጠር አንጋፋ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ አንጋፋው አበጋዝ ሲከውኑ የመከወኛ ቁሶችን በማቀበል ለመርዳት ቅርብ ጊዜ ካስቆጠሩት አበጋዞች ውስጥ በእድሜ አነስ ከሚሉት አንዳቸው አብረው ይሆናሉ፡፡

ስርዓቱን ለመፈጸም ከታረደው ወይፈን ስጋ ሻኛ (Dallichcho)፣ ፍርንባ (Eeddiraaso)፣ ጎድን (Midaado) እና የዘር ማስተላለፊያ ብልት (ሀንጩፋ Hancufa) እና ሌሎች የተነጠረ ቅቤ ‹‹ወጪታ››፣ የአናት ቅቤ እና ወለላ ማር (Marabo) ቀርበዋል፡፡ የስርዓቱ ዋና ፈጻሚ አንጋፋው እና አብሮ በመሆን የሚረዱት አበጋዞች ሁለቱም አስቆጣሪው እና ባለቤቱ ወደ ተቀመጡበት ቀረቡ፡፡ አከዋወናቸውም በመጀመሪያ ለሰውዬው ቀጥሎ ለሚስቱ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ አካሄድ ሻኛው ሰውዬው በጥርሱ እንዲነክስ በማድረግ በቢላዋ ተቆረጠ፣ ለሚስቱም እንደዚሁ በማድረግ ፍርንባውንና ጎድኑን በየተራ በጥርሳቸው እያስነከሱ ሁለት ሁለት ጊዜ ቆረጡላቸው፡፡ በማስከተልም ሀንጩፋውን በሰውዬው የግራ እጅ ላይ እንደማስገባት ካሉና መልሰው ወዲያው በቀኝ እጁ ክንድ ላይ አጠለቁለት፡፡ ለሚስቱ ደግሞ በወይፈኑ ሆድ ዕቃ ዙሪያ ላይ የሚገኘው ሞራ (ሞቾ Moochcho) በደረቷ አለበሷት፡፡ ከዚያም ከተነጠረው ቅቤና ማር በቅደም ተከተል ሁለት ሁለት ማንኪያ አቀመሷቸው፡፡ በመጨረሻም ከሰውዬው እህቶች መካከል ትልቋ የአናት ቅቤ በግራ እጇ ዘርግታ ይዛ በቀኝ እጇ እየቆነጠረች ሁለት ሁለት ጊዜ ሁለቱም ቀባች፡፡ እህት ከሌለው የአባቱ እህት ወይም የእህት ልጅ ልትቀባ እንደምትችል አቶ ታምራት ቂንጣሞነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 5/2005)፡፡



ፎቶ 13. ለአቶ እየቆ ለጩቦ ሀንጩፋ በእጃቸው ጠልቆላቸው፡



ፎቶ 14. ለአቶ ደሰታ ኀበሮ ሚስት ለወ/ሮ አበበች ኦራሞ ሞቾ በደረቷ ሲያለብሷት ፣

አበጋዞቹ ስርዓቱን ፈፅመው እንደጨረሱ በዋናነት ስርዓቱን የፈጸሙት አንጋፈው አበጋዝ አስቆጣሪውን ‹‹አበጋዝ፣ ጥባሞ›› በማለት፡ ሚስቱን ደግሞ ‹‹ጊፍቴ›› ብለው ጠሩዋቸው፡፡ ሌሎቹ አበጋዞች ‹‹ይሁን እኛም ብለናል ተከበሩ ,ያከብራችሁ›› እያሉ ማጽደቃቸው ገለጹ፡፡

ከላይ የተገለጸውን ስርዓት አበጋዞቹ ሲከውኑ ማኻር ኢዮና (Mahaar Iyyonaa) እያሉ ሲሆን፤ የተቀመጡት አበጋዞችም በመቀበል ማኽር ኢዮና (Mahaar Iyyonaa) የተከበርክ ሁን፤ ይቅናህ ሻዕሞና (Shaa’mmona) ብለዋል፡፡ ይህ ክብር አይለይህ እንደማለት ነው፡፡

ከላይ ለቀረቡት ስርዓተ ክዋኔዎች ትርጉም ሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ ከተማ አስር ሰዎች በተሳተፉበት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ አንስቼ የሚከተሉት ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

አበጋዞቹ ስርዓቱን ለመፈፀምና ለማፅደቅ ወይፈን እንዲቀርብ ያደረጉት ወይፈን እድገቱን ያልጨረሰ ትኩስ ሃይል ያለው ነው፡፡ ያልተከላሸ በመሆኑም ዘሩን ይተካል፡፡ ልክ እንደዚሁም ሁሉ አስቆጣሪው ሰውዬ ከብቶቹን ሲያረባ በርካታ ፈተናዎችን ያሸነፈ ሀይል ካለው ወደፊትም አሁን ካገኘው ወግ ማዕረግ የበለጠ እንደሚያገኝ ለማመልከት ነው፡፡ ያገኘው ክብርና ዝና ለልጅ ልጆቹ ይተላለፋል ተብሎ ስለሚታሰብ፡፡ ወይፈኑ ታርዶ ነፍሱ ሳትወጣ ገና እየተንፈራገጠ ሀንጩፋው ተገፎ የወጣበት ምክንያት እንዳልሞተ፣ ከነህይወቱ እንዳለ በማሰብ ሲሆን፤ ለሰውዬው ክብት ይርባለት እንደማለት ነው፡፡

ሻኛው ምርቃት ማድረጊያ ነው፡፡ ሻኛው የበላይ፣ ትልቅ፣ የተከበርክ ነህ ማለት ነው፡፡ ብዙ ከብቶች በሚጠበቁበት ቦታ ከርቀት ሲታዩ ለተመልካች በአይን ቶሎ የሚገባው ባለ ሻኛው ወይፈን፣ ኮርማ ነው፡፡ ሲያገሳ ድምጹ ከፍት ይሰማል፡፡ የተለየ ሞገስ አለው፡፡ ኃይል ስላለው ቢዋጋ ያሸንፋል፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ሰውዬው በሻኛ ሲመረቅ ሰው በበዛበት ቦታ ሁሉ በክብር በሞገስ ታይ፤ እንደሻኛው የበላይ ሁን፤ ብትናገር ተደመጥ፤ በተሰማራህበት ሁሉ አሸንፍ፡፡ የአንተ ክብር የኛ ክብር ነው ምራን፤ ክፉውን ሁሉ አጥፋ እንደማለት ነው፡፡

ፍርንባ በባህሉ ምርቃት የሚካሄድበት ነው፡፡ ከስጋ ብልቶች መካከል ጮማ፣ ወዝ ያለው ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ ምርቃት ሲካሄድበት የተለየህ ወዛም ሁን፤ ሰውነትህ አይድረቅ ማለት ነው፡፡

ጎድን በሆድ ውስጥ ያሉትን የሆድ ዕቃዎች ሁሉ ሸፍኖ ከአደጋ ተከላከሎ የያዘ ነው፡፡ አንተም ለዚህ ክብር ለፍተህ ጥረህ ደርሰሃል፡፡ ከዚህ በኋላ ማህበረሰቡን ሰብስቦ ያዥ፤ በእኩል ዓይን የምታይ ያድርግህ እንደማለት ነው፡፡

ሀንጬፋ በሰውዬው ክንድ ላይ ሲያጠልቁ በግራ እጁ ላይ ለማጥለቅ ብለው መልሰው በቀኝ እጅ ክንድ ላይ የሚያጠልቁበት ምክንያት ሶሮ ወረዳ በተደረገው የተተኳሪ ቡድን ውይይት እንደተገለጸው፡-

> *በመጀመሪያ ወደ ግራ እጅ ላይ መጠቆማቸው የሚያመላክተው ከዚህ በፊት የኖረበትን ህይወት ዘመን ሲሆን፤ ይህም በፈተናና በችግር መሞላቱን ነው፡፡ ነገር ግን ያንን ሁሉ ችግር፣ ፈተና ጥሰህ አሸንፈህ ለዚህ ክብር መብቃቱን ሲያመለክቱ በቀኝ እጁ ክንድ ላይ ያጠልቁለታል፡፡ ግራ ከሆነው ችግር ፈተና ጨለማ ወጥተህ ብርሃን በሆነው ቀኝ ላይ ነህ የሚል ትርጓሜን ይይዛል፡፡ ሀንጬፋው በክንድ ላይ መጥለቁ አንድም በባህሉ ደንብ መሰረት በህይወት ዘመኑ ለፈጸመው ተግባር ጥንካሬውን፣ ጀግንነቱን ወንድነቱን ያመላክታል፡፡ አንድም ለተከበረ ትልቅ ሰው ክንድ ላይ የሚጠልቅ የማዕረግ መግለጫ ነው፡፡ አንድም ማህበራዊ ደረጃው ፤ ከፍ ማለቱን መቀየሩን ይጠቁማል፡፡ እንዲሁም ሀንጬፋው በክንዱ ሲጠልቅ ትዕግስተኛ ይሆናል ተብሎ በማለት ነው፡፡ (ታህሳስ፡ 26/2005)፡፡*

በሀድያ ምርቃት ከሚካሄድባቸው ነገሮች አንዱ ማር ነው፡፡ ንቦች ጣፋጭ የሆነውን ማር የሚያመርቱት የተለያዩ ቦታዎች ተዟዙረው ከተለያዩ አበባዎች በመቅሰም ነው፡፡ አንትም

እንደዚሁ በህይወት ዘመንህ ከብቶች አርብተህ ለዚህ ትልቅ ክብርና ዝና፣ ባህላዊ የሹመት ስያሜ ለማግኘት ከብቶችህን ይዘህ የተለያዩ ቦታዎች ተዟዙረሃል፣ ለፍተሃል፡፡ በመሆኑም ሰዎች ዘንድ የምትናገረው፣ የምትተገብረው እንደ ማሩ ይጣፍጥልህ የተወደድክ ሁን ማለት ነው፡፡

በአናት ቅቤ መቀባቱ ከብቶች አርብተህ ለዚህ ክብር የደረስከው በፀሐይ ሙቀት እየተቃጠልክ ደርቀህ ነው ማለት ነው፡፡ አላማውን ያሳካ፣ ጠንካራ ጎበዝ ሀብታም መሆኑንም ያመላክታል ፡፡ ቅቤውን የምትቀባው ሴት ቅቤውን በእንሰት ቅጠል በግራ እጇ በመያዝ በቀኝ እጇ ባልና ሚስቱን ቀብታለች፡፡ ግራው አስቸጋሪ ነገሮችን ለማመልከት ሲሆን፤ በቀኝ እጅ መቀባቷ ስኬትን ለመግለጽ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ቀብታ ስትጨርስ እጇቿን እንድትታጠብ አይፈቀድም፡፡ ከታጠበች በረከቱን እንዳጠፋች ይቆጠራል፡፡ እጇቿን ሳትታጠብ ትንንሽ ልጆች ፀጉር ላይ ወይም በአካሏ ላይ ትጠራርጋለች ፡፡



ፎቶ 15. በጎንቦራ ወረዳ ኦሌ ቀበሌ ያስቆጠሩት አቶ እየቆ ለጨቦ ከነሚስታቸው ቅቤ ሲቀቡ፣

የተነጠረ ቅቤ በማንኪያ ማቅመሳቸው ቅቤ እንደተነጠረ በተለያዩ የማስቀመጫ እቃዎች ሲቀመጥ ይረጋል እንደዚሁም አንተ በርካታ ፈተናዎችን ያሳለፍክ በመሆንህ የረጋህ ሁን እንደማለት ነው፡፡

በሚስትየው ደረት ላይ የሚያለብሷት ሞራ (ሞቻ) የከብት ሆድ ዕቃ ውስጥ ጨጓራው ላይ ተሸፍኖ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ሞራ ወጥቶ ተዘርግቶ ሲታይ ዳንቴል የሚመስል ቅርጽ አለው፡፡ ጌጥ ስለሚመስልም ደስ ይላል፡፡ ሞራው ለበርካታ ቀናት ቢቀመጥ እንደሌሎቹ የስጋ ብልት ዓይነቶች አይሸትም፡፡ ሰውዬው ከብቶቹን አርብቶ ለዚህ ክብርና ዝና ሲበቃ ሚስቱ ስንቅ በማቀበል አብራ ለፍታለች፡፡ ስለዚህም ምስጢር ጠባቂ፣ ድጋፍ ሰጪ፣ ሽፋን በመሆንሽ ክብርና ጌጥ ላንቺ ይገባሻል በማለት ነው ሞራውን የሚያለብሷት፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ታህሳስ፣ 26/2005) ፡፡

የሚስቱ ሚና ምን እንደሆነ ለአበጋዝ ሰዪም ደሪሎ እንስቄላቸው ሲገልፁም "ሚስቱ በመኖሪያ ቤት ማንኛዋም የብሄረሰቡ ሴት የምታደርጋቸውን ተግባራት ትፈጽማለች፡፡ ነገር ግን ከዚህ በተጨማሪ ባለቤቷ ግጦሽ ፍለጋ ከብቶቹን ይዞ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ስንቅ ታቀብላለች፡፡ የተጠራቀመውን ወተት በመናጥ ወይም በማስናጥ አይብ፣ ቅቤ በማዘጋጀት አገልግሎት ላይ ታውላለች፡፡ አዲስ የተወለዱ ጥጆችን ትንከባከባለች፡፡ ባለቤቷን የማገዝ ሚና አላት፡፡ ስለዚህም ነው (ጊፍቴ) የሚለው የክብር ስም የሚሰጣት፤" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 25/2005) ፡፡

አበጋዞቹ ስርዓቱን ከፈፀሙ በኋላ ጥሪ ተደረጎላቸው የመጡት ቤተ ዘመዶች እንደአመጣጣቸው በቡድን በቡድን በመሆን ልክ አበጋዞቹ እንደፈጸሙት አይነት ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡ በ 4.3.2 ላይ በዋዜማው እለት ስርዓቱን ለማክበር ሲመጡ በየወገናቸው በመሆን ለደስታ መገለጫ የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው እንደመጡ ተገልጿል፡፡ ካረዱት በሬ ስጋ ብልቶች ውስጥ ለስርዓቱ ማካሄጃ በማለት ከሻኛው፣ ከፍርንባውና ከጎድኑ ያስቀሩትና ሀንጬፋውን አንድ ላይ አድርገው በመያዝ፣ ማር ከነእንስራው ጨምረው ወንዶቹ ይሸከማሉ፡፡ ሴቶቹ ደግሞ ወጪታ፣ ዳቦ እና የአናት ቂቤ በመያዝ በጋራ ሆነው እየጨፈሩ አስቆጣሪው ሰውዬና ሚስቱ ወደ ተቀመጡበት ቤት ይመጣሉ፡፡ ከመጡም በኋላ ልክ አበጋዞቹ ወይፈን አርደው እንደ ከወኑት ስርዓት አደረጉ፡፡ ምክንያቱም ለሰውዬውም ሆነ ለሚስቱ የተሰጣቸውን ባህላዊ ስያሜ፣ ክብርና ዝና በአጠቃላይ የተደረገውን ስርዓት መቀበላቸውን፣ ማክበራቸውን፣ ማፅደቃቸውንና እነሱም መመረቃቸውን ለመግለፅ ነው፡፡




ፎቶ 16. ቤተ ዘመዶች ለሰውዬውና ለሚስቱ የተሰጣቸውን ማዕረግ ለማጽደቅ ሲመጡ ፣

አመጣጣቸው በቅደም ተከተል ነው፡፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ መምጣት አይችሉም፡፡ መቅደም የሚገባው ወገን እያለ የማይገባው አይቀድምም፡፡ በዚህ ጉዳይ ያነጋገርኳቸው አበጋዝ አየለ አለሙ "አስቆጣሪውና ሚስቱ ወዳሉበት ሲመጡ በቅደም ተከተል ነው፡፡ ቅደም ተከተሉ በመጀመሪያ የሰውዬው ወገኖች የጎሳ መሪዎችና ቤተዘመዶች፣ በመቀጠል የሚስት ወገኖች፣ ከዚያም የወንድ ልጅ ሚስት ወገኖች፣ የሴት ልጅ ባል ወገኖች (ካሉ) እያለ እንደሚቀጥል፣" ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ጥር፣ 5/2005 ዓ.ም) ፡፡

በመስክ ቆይታዬ መረጃ ለመሰብሰብ በተሳተፉኩባቸው በጎምቦራ ወረዳ አዴአና ቀበሌ በአቶ ላምባሞ ሚጦሬ የቆጠራ ስርዓት ላይ የሰውዬው ቤተዘመዶች እኛ መቅደም ሲገባን የሚስትየው ቤተዘመዶች ቀድመው ሊገቡ ነው፤ በማለት እንዳይገቡ ለማድረግ በተደረገው እንቅስቃሴ ባለመግባባት ከፍተኛ ብጥብጥ[15] ተፈጥሮ የቀበሌ ታጣቂዎች እንዳረጋጉ ተመልክቼያለሁ፡፡

---

[15] አበጋዝ ስዩም ደሪሎ እና አቶ አበበ ጊቻሞ እንዳጫወቱኝ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት በተፈጸመ ስርዓት ላይ እኛ ነን መቅደም የሚገባን እኛ ነን በሚለው ግጭት ተፈጥሮ አንድ ሰው ተደብድቦ እንደተጎዳ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፤ ጥር፣7/2005)፡፡

እያንዳንዱ ቡድን በቅደም ተከተል ስርዓቱን የሚፈጽሙበትን ቁሶችን ይዘው «ሸንበለላዮኔ» እና «ማኸር ኢዮና» የሚለውን እየጨፈሩ ቤቱ በር ላይ ሲደርሱ ከጎሳው ሽማግሌዎች አንድ ወንድና ሴት እና ቁሶቹን የያዙት ብቻ ይገባሉ፡፡ ከዚያም ከላይ እንደተገለጸው ልክ አበጋዞቹ ወይፈን አርደው እንደፈፀሙት ስርዓት ይፈፅማሉ፡፡ በዋናንት ግን ስርዓቱ ተረጋግጦ የሚፀድቀው አበጋዞቹ ወይፈን አርደው በፈፀሙት ስርዓት ከዋኔ ነው፡፡

በባህሉ የወገና ስርዓት ተፈጽሞለት ባህላዊ የማዕረግ ስያሜ የተሰጠው ግለሰብ በፊት ከነበረበት ማህበራዊ ደረጃ በወግ ማዕረግ ወደ ሌላኛው ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ይላል፣ ይሸጋገራል፡፡ የሚሰጠው የማዕረግ ስያሜ ከተግባሩና ከህብቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከብቶችን ሲያረባ የገጠሙትን ፈተናዎች ሁሉ ተጋፍጦ በድል አድራጊነት አላማውን ያሳካ በመሆኑ፣ ጥንካሬውን፣ ጀግንነቱና ወንድነቱን ለመግለጽ "አበጋዝ" የሚል የማዕረግ ስያሜ፣ ብዙ ከብት በማርባቱ ሀብት የተረፈው መሆኑን ለመግለፅ ደግሞ "ጥባሞ" የሚል ስያሜ ይሰጠዋል፡፡ ሚስቱም የጠንካራ ጀግና፣ የሀብታምና የተከበረ ሰው ሚስት በመሆኗ በፈጸመችው ተግባር የተለየች፣ የቀደመች በማለት "ጊፍቴ" የተሰኘ ባህላዊ ማዕረግ ታገኛለች፡፡

በዚህ አይነት ክብር የተሰጠው ግለሰብ "የወገና ስርዓት ተፈጽሞለት ማዕረግ ያገኘ ብሔሩ በሚያደርገው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ምርቃት፣ ቡራኬ በማድረግ ስብሰባ ሊከፍት ይችላል፡፡ በማህበረሰብ ከሚጠሉና ከሚወገዙ ጉዳዮች እራሱን ያርቃል፡፡ ሚስቱም ባላት ማዕረግ በአካባቢዋ ካሉ የቤት እመቤቶች በተለየ ሁኔታ ትከበራለች" በማለት አበጋዝ ዱባን ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠየቅ፣ ታህሳስ፣ 24/2005) ፡፡

ምልከታ ባደረኩባቸው ቦታዎች ስርዓቱ ከተደረገላቸው ሰዎች ውስጥ የተሰማቸውን እንዲነግሩኝ ከጎንቦራ ወረዳ አቶ ላምባሞ ሚጠሬ እና ከሶሮ ወረዳ አቶ ደስታ ጎቦሮን ጠይቄያቸው ነበር፡፡ አቶ ላምባሞ ሲነግሩኝ "በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ደረጃ እንዲሁ አልበቃሁም፣ ብዙ ወጣ ውረዶችን አሳልፌ ነው፡፡ ለዚህ ወግ ማዕረግ በመድረሴ ተደስቻለሁ፤" ብለውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 4/2005) ፡፡ እንዲሁም አቶ ደስታ "ደስ ብሎኛል፡፡ ይሄ እኮ በባህላችን ትልቅ ነገር ነው፡፡ ቤተሰቤ ሁሉ ደስተኛ ነው፡፡

ከአበጋዝ ጊንታሞ ሀሳብ መረዳት እንደቻልኩት አስቆጣሪው የወበጣ ስርዓት እስኪፈፀምለት ከራሱ ድንበር አልፎ የማይንቀሳቀስበት ምክንያት የተከበረ ትልቅ ሰው በመሆኑ ምናልባት የሚፃረረው ክፉ ነገር እንዳያጋጥመው ከመስጋት ነው፡፡ እንዲሁም በራሱ ድንበር ሲንቀሳቀስ ወዳጁ አብሮት የሚሆነው የሚያጋጥመው ነገር ስለማይታወቅ ለመጠንቀቅና መከበሩን ለማሳየት ነው፡፡

የገላ ማጠቡ ስርዓት ለምን እንደሚደረግ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ "ወበጣ የሚፈጸመው የወገና ስርዓትን ለማክበር ዝግጅቱን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ስርዓቱ እስከ ተፈፀመበት ባሉ ጊዜያት ያጋጠሙ ችግሮችን ለማስወገድ፣ ለማንፃት" ሲሉ ገልጸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ታኅሳስ 25/2005) ፡፡

የገላ ማጠቡ ስርዓት መፈጸሙ በአንድ በኩል ክፉ ነገር በቤተሰቦቹ፣ በከብቶቹ በንብረቶቹ ላይ ችግር እንዳይደርስ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለወደፊት መልካም ነገር እንዲገጥመው፣ ያገኘው ክብርና ዝና እንዲጸና ለማድረግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

የገላ ማጠቡን ስርዓት የሚከውኑት ከሰውዬው እህቶች መካከል በእድሜ የገፋችና አክስቱ (የአባቱ እህት) እህት ከሌለው የአክስቱ ሴት ልጅ እና በጎረቤት እጁ በረከት አለው ከምትባለው ጋር የወበጣውን ስርዓት ይፈፅማሉ፡፡ ስርዓቱን ለመከወን እህትና አክስት የሆኑበት ምክንያት አቶ አበበ ጊቻሞ ሲነግሩኝ "እህት ምስጢር ጠባቂ በመሆኗ፣ አክስት ደግሞ ምቀኝነት ስለሌለባት ብትመርቅ፣ ብትረግም ይደርሳል ተብሎ በመታመኑ እንደሆነ" ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 5/2005) ፡፡

ስርዓቱን የሚከውኑት ሴቶች መከወኛ ቁሶችን ለማምጣት በጠዋት እንስራ ይዘው ወደ ወንዝ ይሄዳሉ፡፡ እንደ አበጋዝ ጊንታም ወዕልገኖ ገለጻ፡-

> *…ሴቶቹ ወደ ወንዝ ሲሄዱ በመንገዳቸው እባብ፣ ዝንጀሮ ውሻ እና ጅብ እንዳያቋርጧቸው ይጠነቀቃሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ጎደሎ፣ ገድ የላቸውም በማለት ነው፡፡ ምናልባት እንኳን ድንገት አንዱ ካቋረጣቸው አይሄዱም፣ ይመለሳሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በመንገዳቸው አንበሳ፣ ነብር ቢያጋጥሟቸው ደስ ይላቸዋል፣ አይመለሱም፡፡ ምክንያቱም ጥሩ ገድ ናቸው በማለት ነው፡፡ ወንዝ ደርሰው ሲመለሱ ግን ምንም ጥንቃቄ አያደርጉም፡፡ ምክንያቱም የሚፈልጉትን ነገር ስለያዙ ነው፡፡"* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 5/2005) ፡፡

ወንዝ ከደረሱ በኋላ ሴቶቹ ገላቸውን ይታጠባሉ፡፡ መታጠባቸው ከእኛ ክፉ ነገር ይራቅ፣ በወንዙ ውሃ ታጥቦ ይውረድ በማለት ነው፡፡ ከዚያም ለማጠቢያ የሚሆኑ ቅጠሎችን ለቅመው በእንስራ ውሃ በመቅዳት ይመለሳሉ፡፡ ስለ ሚለቀሙት የቅጠል ዓይነቶች ወ/ሮ በቀለች አንሼቦ ሲጠቅሱ "ቅጠሎቹ የሚለቀሙት ከጫካና የጓሮ ተክሎች ሲሆን አይነታቸውም በተፈጥሯቸው መልካም መዓዛ፣ ሽታ ያላቸው ናቸው፡፡ ለአብነትም ጤጅ ሳር፣ አርቲ፣ ጤናዳም እና ከሴ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ፍሬ ሊያፈሩ የሚችሉ ሲሆኑ ለአብነትም ዶቅማ ፤" ሲሉ ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 5/2005) ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ያሉትን የቅጠል አይነቶች ሊነግሩኝ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ምክንያቱም ከቅጠሎቹ አይነት ውስጥ መድኃኒትነት ያላቸው ሊኖሩ ስለሚችሉና ምስጢር በመሆናቸው ነው፡፡ ከተነገሩ ይረክሳሉ ወይም መድኃኒት አይሆኑም ተብሎ ስለሚታመንበት ነው፡፡

በእንስራ ያመጡትን ውሃ ሞቅ በማድረግ ቅጠሎቹን ጨምረው ሰውዬውንና ሚስቱን ገላቸውን በቅጠሎቹ እያሻሹ ያጥቧቸዋል፡፡ በቅጠሎቹ ሲያሻሹም "ክፉ ይራቅ፣ ይጥፋ" እያሉ ነው፡፡ በመቀጠልም የሰውዬውን ቤትና ዕቃዎቹን ሁሉ ይረጫሉ፡፡" (አበጋዝ ደሳለኝ አንሼቦ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት፣ 5/2005) ፡፡ የገላ ማጠብ ስርዓቱን ለመከታተል እንደማይፈቀድልኝ ስለነገሩኝ መመልከት አልቻልኩም፡፡ የገላ ማጠቡ ስርዓት ከተከወነ በኋላ በግ ይታረዳል፡፡ የበጉን ስጋ ቤተሰቦች ብቻ በልተው መርቀው ይለያያሉ፡፡ በጉ የታረደበት ምክንያት "ስርዓቱ ማብቃቱን ለመግለጽ" እንደሆነ ገልፀውልኛል፡፡ (አበጋዝ ጊንታሞ ወዕልገኖ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 25/2005) ፡፡

በጥቅሉ የወገና ስርዓት በመፈጸሙ ሚያበረክታቸው ፋይዳዎች አሉ፡፡ እነሱም፡- ማህበራዊ ኑሮን ከማጠናከር አንጻር ሚና አለው፡፡ ይህም ስርዓቱ በሚፈጸምበት ወቅት የሚገኙት የብሔሩ አባላት የእርስ በርስ ግንኙነታቸው፣ ማህበራዊ ትስስራቸው እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡ ሌላው የወገና ስርዓት መተግበሩ በሕብረተሰቡ ላይ አዎንታዊ ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም በባህሉ ህገ ደንብ መሰረት ስርዓቱ የተፈጸመላቸው በተሻለ ሁኔታ ቤተሰባቸውን ከማኖራቸው አልፈው ጀግና ሀብታም፣ ተብለው የማዕረግ ስያሜ ሲሰጣቸው ሲያዩ ሌሎች ይነሳሳሉ፡፡ ስለዚህም እነሱ የደረሱበት ለመድረስ በከብት እርባታ ተግባር

ላይ በመሰማራት፣ ኑሮዋቸውን በተሻለ ሁኔታ መምራት፤ ኢኮኖሚያቸውን በማሻሻል ባህላዊ ማዕረግ ለማግኘት መነሳሳትን፣ ፉክክር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም አበጋዞቹ ባላቸው የተሻለ ኢኮኖሚ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት አለ፡፡ ስለሚሰጡት አገልልሎት አቶ አበበ ጊቻሞ "ባፈሩት ሀብት ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ተግባራትን የሚያከናውኑ አሉ፡፡ ለምሳሌ በአካባቢያቸው የእህል ወፍጮ መትከል፣ የሽቀጣ ሸቀጥ ሱቅ መክፈት እና የእህል መጋዘን መክፈትን መጠቀስ ይቻላል፡፡[16] በዚህም ህብረተሰቡን ይጠቅማሉ፤ ኢኮኖሚያቸውንም ያሳድጋሉ፤" በማለት ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 30/2005) ፡፡

---

[16]የወገና ስርዓት አካሂደው ማዕረግ ካገኙት አበጋዞች ውስጥ በሀብታቸው የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ የሚያገለግሉ ተግባራትን አየፈጸሙ ካሉት ውስጥ መስከ በቆየሁበት ጊዜ ካጣራሁት ለአብነት ያህል ለመጥቀስ አበጋዝ ስዩም ደሪሎ የሽቀጣ ሸቀጥ ሱቅ፣ አበጋዝ ማትዮስ ፎርሲዶ የእህል ወፍጮና የእህል መጋዘን በጊምቢቹ ከተማ ከፍተው ለህብረተቡ አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ በተጨማሪም አቶ አበበ ጊቻሞ እንደነገሩኝ "አበጋዝ ፊታሞ ጎኔ፣ አበጋዝ ጸደቀ ከወና ሱቅ ያላቸው፤ እንዲሁም አበጋዝ አጣሞ አጋፋሪ የእህል ወፍጮ እንዳላቸው" ነግረውኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት 5/2005) ፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሀድያ ብሔር "ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ከዋኔ" ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የብሔሩ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት አለመጠናቱ ያነሳሳኝ አንድ ምክንያት ነው፡፡ ጥናቱም ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ስርዓት ማህበራዊ ፋይዳውን ማሳየት አላማው ነው፡

ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ምልከታ (አስተውሎት)፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በመስክ ቆይታ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) ሲከወን አምስት የተለያዩ ቦታዎች በአውዱ በመገኘት ምልከታ ተደርጓል፡፡ መረጃው ከሰላሳ አራት ሰዎች ሲሰበሰብ አስራ አራቱ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ሆነው አገልግለዋል፡፡

የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑ ሲሆን የትንተናውም ውጤት በሚከተለው መልኩ ተጠቃሏል፡፡

ጥናቱ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ ወገና ስርዓት የአጀማመር ሁኔታ ታሪክ ምን እንደሚመስል አይቷል፡፡ ይህም በብሔረሰቡ ከብት ማርባት የቆየ ልማድ እንደሆነና ብዙ ከብቶችን ያረባ ሀብታም፣ ተብሎ ክብር ይሰጠው እንደነበር ተነስቷል፡፡ በባህሉ ህገ ደንብ መሰረት ከብቶች አርብቶ መቶና ከዚያ በላይ ያደረሰ የወገና ስርዓት ይካሄድልኝ ብሎ እንዲጠይቅ አይፈቀድለትም፡፡ ይልቁንም የወገና ስርዓት ሲፈፀም ሊሟሉ የሚገቡ ዋና ዋና መሰረታዊ ነጥቦች እንዳሉና እንኝህን መሰረታዊ ጉዳዮች በባህሉ መሰረት የሚያጣሩ ሰዎች መኖራቸው በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡

የወገና ስርዓት ለማካሄድ በዋናት የሚያረባቸው ከብቶች ቁጥር የትልልቆቹ ከመቶ ሰላሳ እስከ መቶ ሀምሳ መሆን፤ በተያያዥነት ከሚታዩት ውስጥ አርቢው የሚኖርበት ቤት ይዘት፣ በምግብ ቤተሰቡን ማጥገቡ፣ ሚስቱን ጭምሮ የሚቀመጡበት በቅሎ እና ፈረስ እንዳለው፣ ከከብት እርባታው ጎን ለጎን በእርሻ ስራ ያለው እንቅስቃሴ የሚጣሩ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ሰውዬው ከነሚስቱ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መግባባት፣ በባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ፣ የሰው ንብረት አለመፈለጋቸውና አስተዋይነታቸው ከግምት እንደሚገባ በጥናቱ ተዳሷል፡፡

ስርዓቱ በሚከወንበት ጊዜ ቤተ ዘመዶች በባህሉ መሰረት የደስታ መግለጫቸውን ይዘው እንደሚመጡ ተጠቅሷል፡፡ ስርዓቱን የሚፈጽሙትና የሚያረጋግጡት «አበጋዞች ፣ጢባሞች» እንደሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ስርዓቱን ለመከወን በሌሊት ከብቶቹን ከበረት አውጥተው በአቅራቢያው ወዳለ ወንዝ ይወስዳሉ፡፡ ወንዙን በግራ በኩል በማሻገርና ቀጥሎም በቀኝ ተመልሰው እንዲሻገሩ ይደረጋል፡፡ አስቆጣሪው ከባለቤቱና ከእህቱ ጋር በመሆን ማር፣ ውሃና ወተት በማቀላቀል በዝግባ ቅጠል ከብቶቹ ላይ እንደሚረጩ፣ የሰውዬው እህት ከሚሻገሩት ከብቶች ውስጥ በመጨረሻ ከሚሻገሩት የአንዱን ከብት ጭራ ይዛ እንደምትሻገርና እንደምትወስድ ከጥናቱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ከወንዝ መልስም አስቆጣሪው ከነሚስቱ በቤቱ ምሰሶ አጠገብ ይቀመጡና አበጋዞቹ ወይፈን አርደው ከስጋው አይነቶች ውስጥ (በሻኛ፣ በፍርንባ፣ በጎድን፣ በሞቅና በህንጨፋ) ስርዓቱን እንደሚፈፅሙ በጥናቱ ተገልጿል፡፡

በዚህም ለሰውዬው "አበጋዝ፣ ጥባሞ"፣ ለሚስትየው "ጊፍቴ" የሚሉ ማዕረግን የሚገልፅ ስያሜ ይሰጣቸዋል፡፡ በስርዓቱም ላይ የሚቀርቡት ትዕምርቶች በባህሉ ትርጓሜ እንዳላቸው ተተንትኗል፡፡ የስርዓቱ የመጨረሻ ማሳረጊያ የወበጣ ስርዓት እንደሚፈፀምና ይህም የማንፃት ክፉን የመከላከል እንደሆነ በጥናቱ ቀርቧል፡፡

የወገና ስርዓት የተፈፀመለት ሰው በባህሉ መሰረት በተሠጠው ባህላዊ የማዕረግ ስያሜ የተነሳ ማህበረሰቡ በተግባሩ ጀግና፣ ጠንካራ እና ሀብታም በመሆኑ ክብርና እውቅና ይሰጠዋል፡፡ የወገና ስርዓት ላይ ለመሳተፍ የሚመጡት ሰዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንደሚጠናከር፣ እንዲሁም ስርዓቱ የተፈፀመላቸው ሰዎች የደረሱበት ወግ ማዕረግ ላይ ለመድረስ እንዲጥሩ እንደሚያደርጋቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

በሌላ ጎኑ ደግሞ የወገና ስርዓት የተፈፀመለት ሰውዬ ወግ ማዕረግን በማግኘቱ ማህበራዊ ደረጃው ከፍ ይላል፡፡ ሀብት የሞላው፣ የተረጋጋ፣ እውነት ተናጋሪ ስለሚባል በማህበረሰቡ ውስጥ የተለየ ቦታ እንደሚሠጠው ተገልጿል፡፡ ቢመርቅ ቢረግም ይደርሳል ተብሎ እንደሚፈራ፣ ለተቸገሩ እንደሚረዳ፣ አካባቢውን በባህሉ መሰረት እንደሚያስተዳድር፣

ግጭቶች ቢነሱ እንደሚፈታ፣ ተሰሚነት እንዳለው በጥናቱ ታይቷል፡፡ ባለው ሀብትም ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሠጡ ድርጅቶችን ከፍቶ እንደሚጠቅም በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊ የከብቶች ቆጠራ (ወገና) በሀድያ ብሔር ለዘመናት ሲከወን የቆየ እና አሁንም ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ባህላዊ ስርዓት ነው፡፡ የወገና ስርዓት ከማህበረሰቡ ኑሮ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፣ ለተከታዩ ትውልድ ስለ ባህሉ ግንዛቤ እንዲተላለፍ የማድረግ ሚናን ይጫወታል፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመተላለፍ የተለያዩ መንገዶች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ክዋኔ ተጠቃሽ ነው፡፡ ሲከወን በመነገር፣ በመዜም በድርጊት ወዘተ በመሳሰሉት በመተላለፍ ከዘመን ዘመን ሊሻገር ይችላል፡፡ ስለዚህም ስርዓቱ በሚከወንበት ወቅት የተገኙ የብሄሩ ተወላጆች ስርዓተ ክዋኔው ላይ በመሳተፍ፣ በመመልከት ባህላቸውን ተገንዝበው ከመፈፀም እና ከማስቀጠል አንፃር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ በብሄሩ የሺህ (ኩማ) ስርዓት አለ፡፡ ይህም በአዲስ አቅጣጫ እራሱን ችሎ መጠናት የሚችል ይመስለኛል፡፡

በመጨረሻም ከጥናቱ የመረጃ ትንተና እና ድምዳሜ በመነሳት የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ይህ ባህላዊ ስርዓተ ክዋኔ ሂደትን በመቅረፅ ዶክመንተሪ ፊልም ቢያዘጋጅና ቢያስተዋውቅ፤ እንዲሁም ስርዓቱ በሚከወንበት አጋጣሚ ስርዓቱን ጎብኚዎች ተገኝተው እንዲመለከቱት ቢደረግ የሚሉ የይሁንታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ሀድያ ዞን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ስነህዝብ *መምሪያ የስነ ሕዝብና ልማት ትስስር፣ አመታዊ መጽሔት* ቅጽ 1፣ ቁጥር 2፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ሻውል በቀለ፡፡ "የሀድያ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅ የዘፈን ግጥሞች ጥናት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ለባችለር ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጽሁፍ (ዲማጽ)፣ 1989 ዓ.ም፡፡

ቀለመወርቅ ተክሌ፡፡ "የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ቆጠራ ዮሐንስ፡፡ "የሀድይኛ ተረትና ምሳሌዎች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ የቀረበ ዲማጽ፣ 1975 ዓ.ም፡፡

በብሔረሰቦች ምክርቤት በባህል ቋንቋና ታሪክና ቅርስ ጥናት፡፡ *የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል፤* ሀዋሳ፣ ፍቅረ ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001 ዓ.ም፡፡

ተሰፋዬ ሊሞሬ፡፡ "የሀድይኛ ተረቶች ይዘት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ የቀረበ ዲማጽ፣ 1993 ዓ.ም ፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ፡፡ "የባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የእርሻ መሳሪያዎች ስያሜ በሀድያ ብሔረሰብ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ የቀረበ ዲማጽ፣ 1993 ዓ.ም፡፡

አዳነች ካሳ፡፡ "የሀድያ ሴቶች ቡድን በሚከውኗቸው ተግባራት ላይ የተመሰረቱ ቁሳዊ ባህላዊ ጥናት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2002 ዓ.ም፡፡

አስቴር ሳሙኤል፡፡ "የሀድያ ብሔረሰብ የዘፈን ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ የቀረበ ዲማጽ፣ 1974 ዓ.ም፡፡

ኤርሲዶ ኢንታሴ፡፡ *የሀድያ ሕዝቦች የባህል መሠረታዊያን፡፡* ሆሳዕና፡፡ Print and Design Shoa P.P. 1999 ዓ.ም፡፡

ግርማ ሱልደሎ፡፡ *የሀድያ ብሔረሰብ በቋንቋ በታሪክ በባህልና በስነ ቃሎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች፡፡* ሆሳዕና፡፡ ሶፍ. ሚክ ማተሚያ ቤት፤ 1998ዓ.ም፡፡

ዝናሽ ሰለሞን፡፡ "የሀድያ ብሔር ባህላዊ ጋብቻና የሰርግ ስነ ስርዓት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የስነቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፤ 1991 ዓ.ም፡፡

Bauman, R *Folklore and Folk life*. Chicago: University of Chicago Press, 1973.

--------------. *Verbal Art as Performance. Indiana* University: Waveland Press, 1977.

--------------. "The Field Study of Folklore in Context." *In Hand book of American Folklore.* Richard M. Dorson (ed.) Bloomington; Indiana University press, 1983. pp 362-368

------------- (ed.). *Folklore Cultural Performances and Popular Entertainments*. New York: Oxford University Press.1992.

Bell, Catherine. *Ritual: Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University press, 1997.

Ben- Amos, Dan. "'Context' in Context" *Western* Folklore. Vol. 52, No, 2/4, Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture (Apr. - Oct., 1993), PP 209-226.

Braukamper, U. "The Correlation of Oral Traditions and Historical Records in Southern Ethiopia: A Case Study of the Hadiya/ Sidamo Past." Journal Ethiopian Studies. Vol. XI. No2, Haile sillasi Univrsity Institute of Ethiopian studies, pp 29-50, 1973.

Braukamper, U and Tilahun Mishago. *Praise and Teasing. Narrative songs of the Hadiya in Southern Ethiopia*. Frankfort: Forbenius Institute, 1999.

Dorson, R.M. (ed.) *Folklore and Folk life, An Introduction*, Chicago; Chicago University Press, 1972.

Finnegan, Ruth. *Oral Tradition and the Verbal Arts*, A Guide to Research practices, London: Alan Barnard and Anthony Good Academic press, 1992.

Goldstein, K. *A Guide for Field Workers in Folklore*. Hatboro, PA: Folklore Association, 1964.

Gruenwald, Ithamar. *Rituals and Ritual Theory in Ancient Israel:* Printed in the Netherlands, 2003.

Hadiya Zone Finance and Economic Development. *Hadiya Zone Statistical Abstract.* Hosana, Printed by Godson Printing Ent, 2003E.C.

Joubert, Annekle. *The Power of Performance,* Germany. Published by Die Deutsche, Bibliothek, 2004.

Rappaport, Roy A. *Ritual and Religion in the Making of Humanity.* Cambridge; Cambridge University Press, 1999.

Hill, R. Donald. *Caribbean Folklore,* A hand book: New York: Green Wood Press, 2007.

Sims, M. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the study of people And Their Traditions.* Utah State; Utah State University Press, 2005.

## አባሪ 1 የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

1. የቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል


| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | ስራ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አበጋዝ ስዩም ደሪሎ | ወ | 59 | ከብት፣እርባታ እርሻና ንጋዴ | ሶሮ |
| 2 | አቶ አበበ ጊቻሞ | ወ | 58 | የመንግስት | ሶሮ |
| 3 | አቶ አበበ አቡኔ | ወ | 59 | የመንግስት | ሶሮ |
| 4 | ገራድ ኤርቃሎ ሚኮሬ | ወ | 79 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 5 | ዳኛ ደሳለኝ ሱጌቦ | ወ | 72 | እርሻ እና ንግድ | ሶሮ |
| 6 | አበጋዝ ጊንታሞ ወልገኖ | ወ | 63 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 8 | አበጋዝ ተሻለ ሉሳ | ወ | 75 | ከብት እርባታ እርሻ | ሶሮ |
| 9 | አቶ እሸቱ ጡሚሶ | ወ | 55 | የመንግስት ሰራተኛ | ሆሳዕና |
| 10 | ዳዳቾ ለጫሞ ባፊቾ | ወ | 71 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ጎምቦራ |
| 11 | አቶ ታምራት ቂንጣሞ | ወ | 56 | የመንግስት | ሶሮ |
| 12 | አበጋዝ ዴቴቦ ሺሾሬ | ወ | 85 | ከብት እርባታና እርሻ | ጎምቦራ |
| 13 | ዳኛ አቤቦ ለሴሶ | ወ | 79 | ከብት እርባታና እርሻ | ሶሮ |
| 14 | አበጋዝ ዮናስ ላምቦሬ | ወ | 63 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |

2. የንዑስ የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | ስራ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አበጋዝ ሊሬ ደሪሎ | ወ | 63 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 2 | አበጋዝ አለየ አለሙ | ወ | 50 | ከብት እርባታ | ጎምቦራ |
| 3 | አበጋዝ አለሙ ቡፌቦ | ወ | 65 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 4 | አበጋዝ ሊሬ ጎረዶ | ወ | 64 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 5 | አበጋዝ ኤሪሶ ተበሌ | ወ | 83 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 6 | አበጋዝ አጭቆ ኦርጂኖ | ወ | 80 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 8 | አበጋዝ ዱባን ለሌሶ | ወ | 65 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 9 | አበጋዝ ዲጌቦ ሚኮሬ | ወ | 68 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 10 | አበጋዝ ሱላሞ አቢዮ | ወ | 61 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 11 | አበጋዝ አያኖ ጀካሞ | ወ | 67 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 12 | አበጋዝ ደሳለኝ አንሼቦ | ወ | 71 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 13 | አበጋዝ ኤርደዶ ሱጌቦ | ወ | 70 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ሶሮ |
| 14 | አቶ ብርሃኑ ወልደየስ | ወ | 60 | የመንግስት | ሶሮ |
| 15 | አቶ ተሰማ ወዕላሞ | ወ | 52 | ገበሬ | ሶሮ |
| 16 | አበጋዝ ሎጂሶ ዶዮሬ | ወ | 69 | ከብት እርባታ እና እርሻ | ጎምቦራ |
| 17 | አቶ ተስፋዬ ወ/መስቀል | ወ | 52 | የመንግስት | ሆሣዕና |
| 18 | አቶ ታደሰ ሀምባሞ | ወ | 49 | የመንግስት | ሆሣዕና |
| 19 | አቶ አበበ ሞሻጎ | ወ | 48 | የመንግስት | ሆሣዕና |
| 20 | ወ/ሮ በቀለች አሻሞ | ሴ | 55 | የቤት እመቤት | ሶሮ |

# አባሪ 2

የወገና ስርዓት ሲከወን ዋና ዋና ነገሮች የሚያሳዩ ፎቶዎች



ወጪታ



ጮጮ



ቤተ ዘመዶች ዳቦና ወጪታ ይዘው መጥተው፤



ቤተ ዘመዶች በሬ ይዘው ሲመጡ፤



ቤተ ዘመዶች በተዘጋጀላቸው ድንኳን ውስጥ፣



በጎንቦራ ወረዳ ስርዓቱ ሲካሄድ ጎንቦራ ወንዝ ላይ የታደሙ ሰዎች፣




በጎንቦራ ወረዳ አንጋፋው አበጋዝ ለአስቀጣሪው ለአቶ ላምባሞና ሚስታቸው ማር እያቀመሱ ፣



በጎንቦራ ወረዳ አጥኚው ስርዓቱ ከተፈጸመላቸው አቶ እየቆ ለጩቦ ጋር ሀንጩፋ በእጃቸው ጠልቆላቸው ፣



አጥኚው ከአስቆጣሪው ከአቶ ላምባሞ ሚጦሬ ሚስትና እህት ጋር ጎንቦራ ወንዝ ስርዓቱን ከከወኑ በኋላ ፣





አጥኚው ለመረጃ አቀባዮች ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ፣





አጥኚው በሶሮ ወረዳ ጊምቢቹ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ፣


ሶሮ ወረዳ ወረዳ ለአቶ ደስታ ኀቦሮ በተዘጋጀ ስርዓት
ላይ እንግዶች በምሽት በተዘጋጀላቸው ድንኳን ውስጥ ሆነው፣





በሶሮ ወረዳ ለአቶ ደስታ ኀቦሮ በተዘጋጀ ስርዓት ቤተ
ዘመዶች ሆነው እራሳቸውን ሲያስተናግዱ፣

በሶሮ ወረዳ ለአቶ ደስታ ኀቦሮ ወንዝ በተካሄደ ስርዓት ላይ
ከታደሙት ውስጥ የጨፈሩ ወደ ቤት ሲመለሱ፣





በጎንቦራ ወረዳ ለአቶ ላምባሞ ሚጦሬ ቤተ ዘመዶች ወደ እስቶጣሪው ቤት
ሲመጡ የደስታ መግለጫ ማርና እህል ጭነው ሲመጡ፣

ይህ ጥናት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት በእኔ የተሠራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡